ግርማዊ ቀዳማዊ አምሃ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

ለኢትዮጵያ ኅብረተ ዘፈር (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ የዘውድ መንግሥት

የበላይ ጠባቂ

መልዕክት ፡

መብት

አንድነት

SOLIDARITY

Liberty In Our Nation

RIGHT

ለኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት።

የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ።

የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ አንድነት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት።

ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡፡

<u>መግለጫ፡፡</u>

የቀድሞው፡ የኢትዮጵያ፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡ መንግሥት፡ አልጋ፡ ወራሽ፡ ልዑል፡ መርድ፡ አዝማች፡ አስፋ፡ወሰን፡ ኃይለ፡ሥላሴ፡

ከዚህ፡ በፊት፡ ከብዙ፡ ውስጣዊ፡ የአርበኞች፡ ኃይል፡ አንቅስቃሴዎች፡ ጋር፡ በተለይም፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ሕገ፡ መንግሥታዊ፡ የዘውድ፡ ኅብረት፡ ተብለው፡ በብዙ፡ መልክ፡ በመጠራት፡ በኅቡዕ፡ ከሚሠሩት፡ ከሃገር፡ ወዳድ፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኞች፡ ንቅናቄዎች፡ ጋር፡ ካደረጉት፡ ግንኙነቶች፡ ሌላ፡

በዘውድ፡ ምክር፡ ቤታቸው፡ መሥራች፡ አባሎች፡ ከፍተኛ፡ ጥናትና፡ አሳሳቢነት፡ አማካኝ፡ "ለኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ብሔራዊ፡ የትብብር፡መልዕክታቸውን"፡ያስተላለፉበትን፡የመጋቢት፡፳፮፡ቀን፡ ፲፱፻፹፫ ዓ፡ም፡ የጥሪ፡አዋጃቸውን፡በማስታወስ፡ለዋናው፡ ዓላማ፡ ግብ፡ ማለትም፡

መብት

አንድነት

SOLIDARITY

Liberty In Our Nation

RIGHT

ለኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት።
የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ።
የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ አንድነት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት።
ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡፡

የኢትዮጵያን፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት፡ በሕዝባችን፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ ሙሉ፡ ተሳትፎ፡ በሚገኘው፡ ቋሚና፡ ሕጋዊ፡ ነፃ፡ የጠቅላላ፡ የሕዝብ፡ ምርጫ፡ ውጤት፡ መሠረት፡ በከፍተኛ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የክብር፡ ሥርዓት፡ ለማቆም፡ ወተቀዳሚ፡ የሕዝባችንን፡ "ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ ወአንድነት፡" የተቀደሰ፡ ዓላማ፡ በግልጽና፡ በጉልህ፡ በማንፀባረቅ፡ "የተባበሩት፡ የኢትዮጵያን፡ አርበኞች፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ የኅብረት፡ እንቅስቃሴን"፡ በማስተባበር፡ የነፃነት፡ ትግሉን፡ በመቀየስና፡ በመምራት፡ የኢትዮጵያን፡ ሕዝብ፡ መሠረታዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ ለማስከበርና፡ በሕዝቡ፡ ነፃ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ ቋሚ፡ ኑባሬዎች፡ (እኒስቲትዩሽኖች) ልዕልና፡ በኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የሕዝብ፡ ሸንጎ፡ (ፓርላማ) እግዝዕና፡ ሰላማዊና፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የሕዝብ፡ መንግሥቱን፡ በነፃነቱ፡ መብት፡ ሕጋዊ፡ ሥርዓት፡ በአንድነቱ፡ ለማፅናት፡ እንዲቻል፡ ለማድረግ።

እንዲሁም፡ የእያንዳንዱ፡ ብሔር፡ የውስጥ፡ አስተዳደር፡ ነፃነቱ፡ በግል፡ የባህሉ፡ ታሪካዊ፡ ይዘት፡ ትይዩ፡ ከበሬታ፡

RIGHT

ለኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት፤
የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፤
የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ አንድነት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት፤
ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡፡

በኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የሕዝብ፡ ሸንጎ፡ ውሳኔ፡ መሠረት፡ ሕጋዊ፡ ሁኖ፡ ለኢትዮጵያ፡ የአንድነት፡ ሕልውና፡ በኅብረት፡ አቋሙ፡ ዘለዓለማዊ፡ በመሆንና፡ በመጽናት፡ ለጠቅላላው፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔረሰብ፡ የጋራ፡ ጥቅም፡ እድገት፡ ደህንነትና፡ ማንናቸውንም፡ ኅብረሰብአዊ፡ ግንኙነት፡ በኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የሕዝብ፡ ሸንጐ፡ ውሰኔ፡ እግዝዐና፡ ዲሞክራሲያዊት፡ ኢትዮጵያችንን፡ በአንድነቷና፡ በመሠረታዊ፡ ታሪኳ፡ ታላቅ፡ ከበሬታ፡ ፀንታ፡ በመቆም፡ በነፃነቷና፡ በሰላም፡ እንድትመሠረት፡ በማለት፡

፩ኛ፡ በመጀመሪያ፡ አስተባባሪ፡ በመሆን፡ ተከፍቶ፡ በቅርብ፡ እንዲሠራ፡ የተደረገውን፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ መሸጋገሪያ፡ ብሔራዊ፡ የትብብር፡ (መብት) ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት፡ ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤታቸው፡ ከዚህ፡ በፊት፡ በተለያዩ፡ መንገድ፡ ሲያካሄድ፡ የቆየውን፡ የምስጢር፡ አመራር፡ በመጥቀስ፡ በአርበኞቹ፡ የትግል፡ መሰዋዕትነትና፡ በማስተባበር፡ ተግባሩም፡ የተገኘውን፡ ታላቅ፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኞች፡ የኅብረት፡ ስምምነት፡ ውሎችን፡ በማስታወቅ፡

RIGHT

ለኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት፤
የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፤
የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ አንድነት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት፤
ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡፡

ሀ) የጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤቱ፡ መንግሥታዊ፡ አካል፡ በተግባር፡ በልዩ፡ ካቢኔ፡ ደረጃ፡ ሙሉ፡ ሥርዓቱን፡ ይዞ፡ እንዲሠራ፡ በዘውድ፡ ምክር፡ ቤታቸው፡ ጠቅላላ፡ ድምጽ፡ ያለፈውን፡ ውሳኔ፡ አጽድቀው፡ በኃላፊነት፡ የተመረጡትን፡ የተባበሩትን፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ ርዕሳነ፡ መማክርትና፡ በልዩ፡ እንደራሴአቸው፡ አቅራቢነት፡ የልዩ፡ ካቢኔው፡ አባሎችንና፡ የበላይ፡ ሹማምንቶችን፡ ሹመው፡ ሥራቸውን፡ በታላቅ፡ ኃላፊነትና፡ በምስጢር፡ ስትራተጂ፡ እንዲካሄድ፡ በጥብቅ፡ በማሳሰብ፡ ባስፈላጊና በአመች፡ ሥፍራዎች፡ ሁሉ፡ የርዕሰ፡ ብሔሩ፡ ተጠሪ፡ እንደራሴዎች፡ የልዩ፡ ካቢኔው፡ ተወካይ፡ አምባሰደሮችና፡ የቆንሲላ፡ ጽሕፈት፡ ቤቶች፡ እንዲሁም፡

ለ) የንቅናቄው፡ "ዲሞክራሲያዊ የነፃነት፡ መብት፡ በአንድነት፡" የኅብረት፡ ዓላማ፡ ደጋፊዎች፡ "የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፡ የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ አንድነት፡ ምክር፡ ቤት፡" አምዶች፡ በማህፀረ፡ ቃል፡ "የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ አንድነት፡ ምክር፡ ቤት" አምድ፡ በመፈክረ፡ ቃል፡ "መብት"፡ ተብለው፡ በመጠራት፡

RIGHT

ለኢትዮጵያ: ኅብረተ: ብሔር: (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ: የዘውድ: መንግሥት:
የኢትዮጵያ: ሕዝብ: ዲሞክራሲያዊ: የነፃነት: መብት: መሸጋገሪያ:
የተባበሩት: የኢትዮጵያ: ብሔሮች: አንድነት: ጠቅላይ: ምክር: ቤት:
ልዩ: ጽሕፈት: ቤት::

ተደራጅተው: በሕግ: በመቋቋም: በጠቅላይ: ምክር: ቤት: የ"መብት": ልዩ: ጽሕፈት: ቤት: በመመዝገብ: እንዲታወቁና: በመመሪያቸው: ዲሲፕሊን: እውነተኛ: ዲሞክራሲያዊና: ብሔረ: ሰብዓዊ: የኢትዮጵያን: አንድነት የፖለቲካ: መሠረታዊ: እምነታቸውን: ፊት: ለፊት: በማንፀባረቅ: እንዲሠሩ: በማድረግ:

ሐ) ለኢትዮጵያ: ሕዝብ: መሠረታዊ: የነፃነት: መብት: ዲሞክራሲያዊ: ልዕልና: በተባበሩት: የኢትዮጵያ: አርበኞች: አንድነት:የጦር: ኃይል: ሕዝባዊ: ሠራዊት: ኅብረት: የነፃነት: ትግሉ: በመላው: የኢትዮጵያ: ሕዝብ: ተሳትፎ: በሰፊው: በሃገራችን: ውስጥ: በመዘርጋት: ተደራጅቶ: እንዲዛመት: ለማድረግ:

የኢትዮጵያ: ሕዝብ: የነፃነት: መብት: መሸጋገሪያ: "የተባበሩት: የኢትዮጵያ: አርበኞች: አንድነት: የጦር: ኃይል: ሕዝባዊ: ሠራዊት:" በማህፀረ: ቃል: "የኢትዮጵያ: አርበኞች: አንድነት: የጦር: ኃይል:" በመፊከረ: ቃል: "አንድነት:" ተብሎ: በመጠራት: በልዩ: ካቢኔው: ጠቅላይ: የጦር: መምሪያ: ትዕዛዝ: በሙሉ: ትጥቅ: ሥርዓት: ተደራጅቶ: እንዲቋቋምና: በሃገራችንም: ውስጥ: የ"አንድነት:" የጦር:

መብት

አንድነት

SOLIDARITY

Liberty In Our Nation

RIGHT

ለኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት፤
የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፤
የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ አንድነት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት፤
ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡፡

ኃይል፡ አምዶችም፡ በአንድ፡ የጦር፡ ኃይል፡ መመሪያ፡ ትዕዛዝ፡ እንዲተዳደሩና፡ እንደሁኔታው፡ አስፈላጊነት፡ ተገቢውን፡ የጦር፡ ስልት፡ በመምሪያና፡ በዘውድ፡ ምክር፡ ቤት፡ የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ ርዕሳነ፡ መማክርት፡ ብሔራዊ፡ የጦር፡ አዛዦች፡ ጋር፡ በማስተባበር፡ ኅቡዕ፡ የነበረውን፡ የተቀደሰ፡ የትግል፡ እንቅስቃሴያቸውን፡ ተግባር፡ በተመቸበት፡ መንገድ፡ ሁሉ፡ በግልጽ፡ እየመሩ፡ እንዲሠሩ፡ የተወሰነውን፡ የዘውድ፡ ምክር፡ ቤት፡ ስምምነት፡ በከበሬታ፡ በማጽደቅ፡

መ) በብዙሃን፡ የሃገራችን፡ ባሕሎች፡ ሃይማኖቶች፡ ጐሣዎች፡ ቋንቋዎች፡ ለረጅም፡ ዘመን፡ በሰላም፡ ብሔረሰብአዊነት፡ በአንድነትና፡ በነፃነት፡ ታሪኳ፡ ተመሥርታ፡ እንደሚያምሩ፡ እቅፍ፡ አበባዎች፡ ደምቃ፡ የኖረችው፡ ኢትዮጵያ፡ እንዲሁም፡ የወደፊቱ፡ ነፃና፡ ዲሞክራሲያዊት፡ ኢትዮጵያችን፡ በሕዝባችን፡ መሠረታዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፡ በተባበሩት፡ አርበኞችዋ፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ ሕዝባዊ፡ ሠራዊት፡ የኅብረት፡ ትግል፡ መስዋዕትና፡ ድል፡ "ብዙሃን፡ የፖለቲካ፡ ፓርቲዎች"፡ በነፃ፡ በመደራጀት፡ "በሕጋዊና፡ በሰላማዊ፡ ቋሚ፡ የእምነት፡ ጉርብትና፡ ከበሬታ"፡ በኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ ዲሞክራሲያዊ፡ ሸንጎ፡ እግዝዕና፡ ቀጥተኛ፡ የኢትዮጵያን፡ ሕዝብ፡ አስተዳደር፡ የበላይ፡ ሃላፊዎቿን፡ በሕጋዊ፡ የሥልጣን፡

መብት

አንድነት

SOLIDARITY

Liberty In Our Nation

RIGHT

ለኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት፣
የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፣
የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ አንድነት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት፣
ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡፡

ሽግግር፡ ዲሞክራሲያዊ፡ ሥርዓት፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል)፡ መንግሥቷን፡ ትመሠርታለች፡ በማለት፡ ሙሉ፡ እምነታቸውን፡ ለኢትዮጵያውን፡ ወገኖቻችን፡ ሁሉ፡ በማሳሰብ፡ በተለይ፡

ለዲሞክራሲያዊት፡ ኢትዮጵያችን፡ በነፃነቷ፡ መብት፡ ከበሬታ፡ በአንድነቷ፡ ፀንታ፡ በሰላም፡ የሕዝብ፡ መንግሥቷን፡ ለማቆም፡ የሚታገሉትን፡ ድርጅቶችና፡ ኢትዮጵያውያን፡ ግለሰቦች፡ ሁሉ፡ የግል፡ ወይም፡ የኅብረት፡ የፖለቲካ፡ አቋማቸውንም፡ ሆነ፡ ማንናቸውንም፡ የሕዝብ፡ አስተዳደር፡ የፍልስፍናቸውን፡ ልዩነት፡ በኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ ንቃተ፡ ሕሊና፡ "ነፃ፡ ጠቅላላ፡ የሕዝብ፡ ምርጫ፡" ዳኝነት፡ ላይ፡ እምነታቸውን፡ በመጣል፡ በቅድሚያ፡ የነፃነቱን፡ መሠረታዊ፡ መብት፡ ለተነፈገውና፡ በዳግማዊ፡ ፋሽስት፡ የጭቆና፡ ኃይል፡ በግዴታና፡ በግድያ፡ የብቸኝነት ርዕዮተ፡ ዓለም፡ በፀረ፡ ሃይማኖት፡ ትምክህተኝነትና፡ በከሠረ፡ የኢኮኖሚ፡ ይዘት፡ በረሃብ፡ አለንጋ፡ ለሚሠቃየው፡ ወገናችንና፡ በተለይም፡ ለሚሰዉት፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኖቻችን፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ ሕዝባዊ፡ ሠራዊት፤ በኅብረት፡ ተግተንና፡ ተባብረን፡ እንድረስለት፡ በማለት፡ ለመላው፡ የኢትዮጵያ፡ ወገናቸው፡ በሃገር፡ቤትና፡ በስደት፡ዓለም፡ ላይ፡ በታላቅ፡ ስቃያና፡ ችግር፡ ለሚገኘው፡ ጀግና፡ ሕዝባቸው፡ በሙሉ፡ "በተቀደሰ፡ ልዩ፡ የጥሪ፡ መልዕክት፡ አዋጃቸው"፡ ሲያሳውቁ፡

መብት

አንድነት

SOLIDARITY

Liberty In Our Nation

RIGHT

ለኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት፤
የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፤
የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ አንድነት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት፤
ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡፡

ሠ) <u>እንዲሁም፡ የኢትዮጵያን፡ ሕዝብ፡ ወዳጆችና፡ ተቆርቋሪዎችን፡ በሙሉ</u>፡ በተለይም፡ ለኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ መሠረታዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ ልምላሜ፡ ሲል፡ የቆመውን፡ የተባበሩትን፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኞች፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ ሕዝባዊ፡ ሠራዊት፡ ደጋፊ፡ ግለሰቦች፡ ድርጅቶችና፡ የመንግሥት፡ ኃላፊዎች፡ ሁሉ፡ ሙሉ፡ የፖለቲካ፡ የሞራልና፡ የዲፕሎማሲ፡ ትብብርና፡ በተለየም፡ ተጨባጭ፡ የማቴሪያል፡ እርዳታቸውን፡እንዲያበረክቱ፡በከበሬታ፡በመጠየቅ፡አመልክተዋል፡፡

ረ) <u>ልዩ፡ ካቢኔውም፡ በውጭ፡ ጉዳይ፡ መመሪያው</u>፡ ከመሠረቱ፡ ለጠቅላላውና፡ ለዘላቂ፡ የኢትዮጵያ፡ ነፃነትና፡ የአንድነቱን፡ ጥቅም፡ የሚያስገኙትን፡ ግንኙነትና፡ አቋሙን፡ ከማይፃረሩ፡ ነፃ፡ ዲሞክራሲያውያን፡ ኃይሎች፡ ጋር፡ እንደሚተባበርና፡ ንቅናቄውን፡ ማካሄጃ፡ ማንኛቸውንም፡ አይነት፡ እርዳታና፡ ድጋፍ፡ በትጋት፡ ለማስገኘት፡ ይጥራል፤ እንዲሁም፡ በኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ፈቃድ፡ በሕግ፡ ተቋቁሞ፡ በሕዝብ፡ ምክር፡ ቤቶች፡ ጸድቆ፡ ይሠራበት የነበረውን፡ ከውጭ፡ ሃገር፡ መንግሥታትና፡ ከሌላም፡ ድርጅቶች፡ ጋር፡ የተደረገውን፡ ውል፡ ስምምነቱ፡ ተጠብቆ፡ ከኖረ፡ እንደሚከበር፡ ሲያረጋግጡ፡

RIGHT

ለኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት፤
የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፤
የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ አንድነት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት፤
ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡፡

በውንብድና፡ ሥልጣን፡ ዘርፎ፡ የቆየው፡ የአምባ፡ ገነኑ፡ የጭቆና፡ ኃይል፡ ሥርዓት፡ የገባቸውን፡ ግዴታዎች፡ ያደረጋቸውን፡ ውሎችና፡ ስምምነቶች፡ ግን፡ በኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ነፃ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ ፈቃድ፡ ያልተቋቋሙ፡ በመሆናቸው፡ በሕዝቡ፡ ላይ፡ ተፈጻሚነት፡ ሊኖራቸው፡ ስለማይችሉ፡ በሙሉ፡ ውድቅ፡ ይሆናሉ፡ በማለት፡ አስታውሰዋል፡፡

ዲሞክራሲያዊት፡ ኢትዮጵያችን፡ የአፍሪካን፡ ድርጅትና፡ የዓለም፡ መንግሥታት፡ ማኅበርን፡ ቻርተር፡ አክብራ፡ በኮሌክቲቭ፡ ሴኩሪቴ፡ ዓላማ፡ ፀንታ፡ የአባልነት፡ ግዴታዋን፡ እንደምትፈጽም፡ የጐረቤት፡ ወዳጅ፡ ሃገሮችን፡ ሰላምና፡ ትክክለኛውን፡ብሔራዊ፡ድንበር፡በማክበር፡ በመልካም፡ ጉርብትና፡ በወንድማማችነት፡ ለመኖር፡ ዋና፡ አላማዋ፡ መሆኑንና፡

በዓለም፡ ላይ፡ የኢሰብዓዊና፡ የጭቆና፡ ኃይል፡ ወንጀሎችን፡ በማውገዝ፡ በነፃ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ ሥርዓት፡ የተመሠረቱትን፡ መንግሥታት፡ ወዳጅነት፡ ግን፡ በግልፅ፡ በማጠናከር፡ የእድገት፡ ቴክኖሎጂንና፡ መሠረታዊ፡ ኢኮኖሚያችንን፡ መገንቢያ፡ የሚሆኑትን፡ የኢንዱስትሪና፡ የንግድ፡ ካፒታልና፡ ሎጂስቲክስ፡ እቃዎችን፡ በጥሩ፡ ስምምነት፡ በማስገኘት፡ ዋና፡ የእድገት፡ መሣሪያዎችንና፡ የትምህርት፡ የእርሻና፡ የሕክምና፡ ቁሳቁስ፡

መ ብ ት

አንድነት

SOLIDARITY

Liberty In Our Nation

RIGHT

ለኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት፣
የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፣
የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ አንድነት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት፣
ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡፡

እጥረት፡ ያለበትን፡ ሁሉ፡ በቶሎ፡ እንዲሟላ፡ በትጋት፡ ትጥራለች በማለት፡ በከበሬታ፡ አስታውቀዋል፡፡

፩ኛ፡ ዛሬ፡ በኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ላይ፡ በደረሰበት፡ ከፍተኛ፡ የጦርና፡ በጣም፡ የሚያሰቅቀው፡ የተደጋገመ፡ የረሃብና፡ የድርቀት፡ አደጋ፡ ከመሠረቱ፡ ሁኔታው፡ ሳይሻሻል፡ በተጨማሪ፡ አስከፊ፡ የግፍና፡ የጭቆና፡ ጭፍን፡ የኮሚኒስት፡ ኢምፔሪያሊስት፡ አምባ፡ ገነናዊ፡ የከሠረ፡ የሰሻል፡ የኢኮኖሚና፡ የግዴታ፡ ሥሬት፡ ይዘት፡ ችግሩን፡ በትምክህተኝነትና፡ ይሉኝታ፡ በሌለው፡ ማናአለኝህነት፡ ከማባባሳቸውም፡ በላይ፡ በጣም፡ የሚመሰገኑና፡ የሚያኮሩትን፡ የዓለም፡ ሰብአዊ፡ እርዳታ፡ ድርጅቶችን፡ ጥረትና፡ ለዚሁም፡ የተቋቋመውን፡ ኮሚሽን፡ ታላቅ፡ ሥራውንና፡ የተወሰነ፡ ጉልበቱን፡ በማደናቀፍ፡ ሀ) ረሃቡ፡ ጋብ፡ ሳይልለት፡ ከትውልድ፡ ሃገሩ፡ ካለውዴታው፡ በተንኰል፡ የሠፈራ፡በሚባል፡ የፖለቲካ፡ ቁጥጥር፡ የፋሽስቶች፡ ፕሮግራም፡ በግፍ፡ የተፈናቀለውና፡ በየውጭ፡ ሃገሩ፡ የተሰደደው፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ቁጥር፡ ብዛት፡ በየግዜው፡ እየባሰና፡ እየጨመረ፡ ከአፍሪካ፡ ምናልባትም፡ ከዓለም፡ ታዳጊ፡ መንግሥታት፡ ውስጥ፡ በድህነትም፡ ጭምር፡ ኢትዮጵያን፡ ለአንደኛ፡ የውድመት፡ ደረጃ፡ ከማብቃታቸውም፡ በላይ፡

RIGHT

ለኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት፣
የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፣
የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ አንድነት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት፣
ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት::

ለ) በከሰረው፡ የኢኮኖሚና፡ የፖለቲካ፡ አመራር፡ ጭራሽ፡ውድቀት፡ የተነሳ፡ ሠራተኛው፡ ፍሬ፡ ካለው፡ የሥራ፡ ገበታው፡ ከንብረቱና፡ ከርስቱ፡ ተፈናቅሎ፡ ጭራሹንም፡ የደኸየው፡ የተራበውና፡ የታረዘው፡ የውድ፡ ሃገራችን፡ የጐበዝ፡ ሥራ፡ አጡና፡ ስርዓቱ፡ አውቆ፡ በፈጠረው፡ በማያቋርጥ፡ የጦርነት፡ ዘመቻ፡ ይሚማገደው፡ ሕዝባችን፡ ብዛት፡ ይህ፡ ነው፡ የማይባልና፡ እንኳንስ፡ ለጦር፡ ኃይሉ፡ ለሰላማዊ፡ ሕዝባችንም፡ ጭምር፡ ያልሆነ፡ ካለዕድሜው፡ አዛውንቱ፡ ከሥራ፡ ገበታው፡ ተገዶ፡ በጡረታ፡ የባከነው፡ እንኳንስ፡ በሽተኛው፡ ጤናማው፡ በጭንቀት፡ ሰላምና፡ ዕረፍት፡ ያጣው፡ ኮብልሎ፡ በበረሃ፡ የቀረው፡ ከሞቀ፡ ቤቱ፡ ተሰዶ፡ በጐረቤት፡ ሃገሮች፡ ሥራና፡ ጠለላ፡ እያጣ፡ የውርደት፡ ማቅ፡ ለብሶ፡ የሚንገላታው፡ ወጣቱና፡ ሽማግሌው፡ በማያቋርጥ፡ የጦር፡ አለንጋ፡ በቀበሮ፡ ጉድጓድ፡ ውስጥ፡ አካለ፡ ጐደሎ፡ ሆኖ፡ ለቀረው፤ ለፈረደበት፡ ጀግናው፡ የሃገራችን፡ ጐበዝ፡ ወገናችን፡ በሙሉ፡ የሚቻለውንና፡ የሚያስፈልገውን፡ ማንኛቸውንም፡ ዓይነት፡ ስትራተጂክ፡ እርዳታ፡ ሳይቋረጥ፡ ለማድረግና፡ ሕዝባችን፡ ራሱን፡ በራሱ፡ ለማስቻልና፡ ሰላሙን፡ ለማስገኘት፡ የሚያበቃውን፡ እርምጃዎች፡ ሁሉ፡ ለመፈጸም፡

መብት
አንድነት
SOLIDARITY
Liberty In Our Nation

RIGHT

ለኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት፣
የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፣
የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ አንድነት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት፣
ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡፡

ሐ) ልዩ፡ ካቢኔአችን፡ በቀጥታና፡ በቅርንጫፍ፡ ድርጅቶቻችን፡ አማካኝ፡ በተለይም፡ በ"አንድነት፡" የጦር፡ ኃይላችን፡ የአምድ፡ ሕዋሳት፡ ድርጅቶች፡ ተገቢውን፡ ስትራተጂካዊና፡ ሰብአዊ፡ እርዳታ፡ እያደራጀ፡ በጦርና፡ በረሃብ፡ የተፈናቀሉትን፡ ወገኖቻችን፡ በሙሉ፡ እንዲረዱ፡ ይጥርበታል፡ ካሉም፡ በኃላ፡ የውድ፡ ሃገራችንን፡ ሕዝብ፡ ስቃይና፡ የፋሽስቶቹን፡ የከፋትና፡ የጥፋት፡ መጠን፡ መዘርዘር፡ በቀላሉ፡ ስለማይቻልና፡ በቆሰለውና፡ በተቃጠለው፡ ወገናችን፡ ጥልቅ፡ የሃዘን፡ ቁስል፡ ላይ፡ ማሾፍ፡ ስለሚመስል፡ ሁሉንም፡ ቤት፡ ይቁጠረው፡ በማለት፡ ኢትዮጵያውያን፡ ወገኖቻችንን፡ በሙሉ፡ ኃያሉ፡ አምላክ፡ ያጽናናቸው፡ በማለት፡ አስተዛዝነዋል፡፡

መ) ስለዚህም፡ ማንናችንም፡ ኢትዮጵያውያን፡ በደረሰብን፡ የቤተሰብና፡ የሥራ፡ ችግር፡ በገጠመን፡ የኑሮ፡ ጉስቁልና፡ የመንፈስና፡ የናፍቆት፡ ጭንቀት፡ ሃዘንና፡ ፀፀት፡ ፈጽሞ፡ ሳንዳከም፡ ለውድ፡ ሃገራችን፡ ለተረፋት፡ ትውልዶቻችን፡ በዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነታችን፡ መብት፡ ልዕልና፡ ከበሬታ፡ በአንድነታችን፡ ለመመሥረት፡ ተባብረን፡ ለእውነተኛ፡ ታሪካችን፡ ለመልካም፡ ብሔረሰብነታችን፡ ክብር፡ ለሃገራችን፡ ፍቅር፡ በየቤታችን፡ መብታችንን፡ ጥሶ፡ የገባብንን፡

RIGHT

ለኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት፣
የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፣
የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ አንድነት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት፣
ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡፡

የምንወዳትን፡ ሃገራችንና፡ ወገኖቻችንን፡ ያቃጠለብንን፡ አምባ፡ ገነናዊ፡ የጭቆናና፡ የግድያ፡ ሥርዓት፡ ፈጽሞ፡ እንዲጠፋ፡ የጐበዝ፡ ያለህ፡ እየተባባልን፡ ጠንካራ፡ አለቆቻችንን፡ በሥርዓት፡ በማቆም፡ ተባብረን፡ ቀንና፡ ሌሊትም፡ ተደራጅተን፡ ዛሬ፡ በቆራጠኛነትና፡ በአምነታችን፡ አንፃር፡ ተግተን፡ ለመሥራት፡ ከመቼውም፡ ግዜ፡ በተጠናከረ፡ ኅብረትና፡ ጉልበት፡ መነሳትና፡ መሟሟት፡ አለብን፡ በማለት፡

ሠ) ጥራት፡ ባለው፡ በሃዲስ፡ የአንድነት፡ ኅብረት፡ ኃይል፡ በታመነ፡ አመራርና፡ ግልጽ፡ በሆነ፡ የዲሞክራሲያዊ፡ መብት፡ ልዕልና፡ አቋም ፡ እስከዛሬም፡ ድረስ፡ የነፃነት፡ ትግሉ፡ በዲሞክራሲያዊ፡ የኅብረት፡ ግንባር፡ እርምጃ፡ የትም፡ ይልደረሰበትን፡ የውድቀት፡ ሁኔታን፡ አውቆና፡ ለይቶ፡ አውጥቶና፡ አጋልጦ፡ በቶሎ፡ ማስወገድና፡ በኅብረት፡ አድሶ፡ መገንባት፡ የማይታለፍ፡ ግዴታችን፡ ነውና፡ ምንም፡ እንኳን፡ በወደቀብን፡ የአረመኔዎችና፡ የጥቅም፡ አሳሄ፡ መሲኾችና፡ ደርሶ፡ አለሁ፡ ባዮች፡ የሸር፡ ውዝግብን፡ ፈተን፡ በግፈኛ፡ የግድያና፡ የግዴታ፡ ኃይል፡ ተጽእኖ፡ የተነሳ፡ ለጊዜው፡ ቁጥራችን፡ ያነሰ፡ ቢመስልም፡ ነገ፡ በእውነትና፡ በብልህነት፡

መብት

አንድነት

SOLIDARITY

Liberty In Our Nation

RIGHT

ለኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት፣
የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፣
የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ አንድነት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት፣
ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡፡

በጀግኖቻችን፡ መስዋዕትነት፡ እንሰበሰባለን፡ እንበዛለን፡ ለሃገራችንም፡ ለኢትዮጵያ፡ አለኝታ፡ እንተርፋለን፡ ተዚያም፡ ሕዝባችን፡ በነፃነቱ፡ እውን፡ ከበሬታ፡ በዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነቱ፡ መብት፡ በአንድነቱ፡ ጠንካራ፡ መሠረት፡ የወደፊት፡ እድሉን፡ ለትውልዳችን፡ የዘለቄታ፡ ጥቅም፡ በስርአትና፡ በጀግንነት፡ የጐበዝ፡ አለቃውን፡ በማቆም፡ እራሱን፡ በራሱ፡ በሰላም፡ ለወደፊት፡ ይመራል፡ በማለት፡

"ለእውነት፡ ለነፃነታዊ፡ መብት፡ ለዲሞክራሲያዊ፡ ልዕልና፡ ለአንድነት፡ለኢትዮጵያዊነት፡ ክብር፡ ለሚያኮራን፡ ታሪካችንና፡ ወገናችን፡ አንተም፡ ስደተኛው፡ ወገኔ፡ በአለህ፡ ኃይል፡ ባገኘኸው፡ መለስተኛ፡ የነፃነትህ፡ እድል፡ አይዞህ፡ ተባበር፤ ሠልፍህም፡ ይመር"፤ በማለትና፡ በማበረታታት፡ ሁሉንም፡ ኢትዮጵያውያን፡ ወገናቸውን፡ በከበሬታ፡አሳስበዋል፡፡

፫ኛ ሀ) በተለይም፡ ለዚሁ፡ ተግባር፡ ለሚውሉት፡ ቆንሲላዎችና፡ በልዩ፡ ካቢኔአችን፡ ግንባር፡ ቀደም፡ አስተባባሪነት፡ <u>በኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ "ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ በአንድነት"፡ አቋም፡ የጠቅላይ፡ምክር፡ ቤት፡ አምዶቻችሁን፡ እያቆማችሁ</u>፡ ድጋፋችሁንና፡ የተቀደሰውን፡

RIGHT

ለኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት፣
የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፣
የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ አንድነት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት፣
ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡፡

ኢትዮጵያዊ፡ ተግባራችሁን፡ እንድታስተባብሩ፡ በልጆቻችን፡ ፍቅርና፡ የደም፡ መስዋዕትነት፡ በዲሞክራሲያዊት፡ ኢትዮጵያ፡ ስም፡ በገናናው፡ የታሪካችን፡ ከበሬታ፡ ሥርዓት፡ የኅብረት፡ መስዋዕታችሁን፡ እንድትፈጽሙ፡ የአክብሮት፡ ጥሪያችን፡ ለወገኖቻችን፡ ኢትዮጵያውያን፡ ሁሉ፡ ይድረሳችሁ፡በማለት፡ መልዕክታቸውን፡ በከበሬታ፡ አስተላልፈዋል፡፡

ለ) ለዚሁም፤ በበጐ፡ሥራ፡ ተግባር፡ መሰባሰቢያ፡ ዓላማ፡ መንደርደሪያ፡ ፕሮግራም፡ በስደት፡ ላይ፡ ያሉትን፡ ኢትዮጵያውያን፡ ወገኖቻቸውንና፡ የኢትዮጵያ፡ ወዳጆችና፡ ደጋፊዎች፡ የሆኑትን፡ ሁሉ፡ በበጐ፡ሥራ፡ አገልግሎት፡ በፈቃደኝነት፡ ማንናቸውንም፡ የትብብር፡ ተግባራቸውን፡ "ታቀፍ፡" ተብሎ፡ በመሰየም፡ የተቋቋመውን፡ "የኢትዮጵያ፡ ልጆች፡ ድርጅት፡" ሰብዓዊ፡ ፋውንዴሽን፡ ለመርዳትና፡ እንዲሁም፡ የ"ታቀፍ"ን፡ ቅርንጫፍ፡ አምዶቹን፡ በአባሎች፡ ድጋፍና፡ በራሳቸው፡ የኅብረት፡ ኃይል፡ በማቋቋም፡ ታላቅ፡ የተቀደሰ፡ መስዋዕታቸውንና፡ መስተዋፅኦቻቸውን፡ እንዲያበረክቱ፡ በማክበር፡ አሳስበዋል፡፡

RIGHT

ለኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት።
የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ።
የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ አንድነት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት።
ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡፡

ሐ) ለዚሁም፡ ግብ፡ **ቋሚ፡ የሕዝብ፡ ድርጅታዊ፡ አካሎች፡** በአንድ፡ ዲሲፕሊን፡አመራር፡ ስልት፡ ተዋህደው፡ እንዲቀናበሩ፡ ትክክለኛ፡ የጽሕፈት፡ ቤቶቹን፡ መታወቂያ፡ አርማቸውንና፡ ቁሳቁሶች፡ እንዲሁም፡ የውስጣዊ፡ አስተዳደርና፡ የሥራ፡ አፈፃፀም፡ መመሪያዎችንና፡ የንብረትና፡ የእርዳታ፡ ምንጮች፡ የሚቀናበሩበተን፡ አንድ፡ ዓይነት፡ አመራርን፡ የያዘ፡ ሥነ፡ ሥርዓትና፡ በዋናው፡ አካል፡ የ"መብት"፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ቤት፡ ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡ አማካኝ፡ "አምዶቹ"፡ ባሉበት፡ ሃገሮች፡ ሕግና፡ በኅብረት፡ ኦዲተሩ፡ የቁጥጥር፡ ስርዓት፡ ዲሲፕሊን፡ አክብረው፡ እንዲተዳደሩ፡ የድርጅታዊ፡ አካሎችን፡ በከበሬታ፡ አሳስበዋል፡፡

መ) የውስጥ፡ አስተዳደር፡ የሥርዓትና፡ የዲሲፕሊን፡ ጥበቃ፡ የኃይላችን፡ የክብር፡ ኮከብ፡ ሕግ፡ አስተናባሪዎች፡ "የጥቁር፡ አንበሳ፡"___ አምድ፡ ባልደረቦችን፡ በማቋቋም፡ ሕጋዊ፡ ግልጋሎታቸውን፡ በምስጢር፡ ስትራተጂ፡ በመቀየስና፡ በማቀናበር፡ በጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት፡ ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡ ቁጥጥር፡ ሥራውን፡ በመምራት፡ "የጥቁር፡አንበሳ"፡ የልዩ፡ ቴክኒክ፡ አምድ፡ ክፍል፡ የንቅናቄውን፡ ንብረቶችና፡

RIGHT

ለኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት፣
የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፣
የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ አንድነት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት፣
ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት::

ማመላለሻዎች፡ መሰብሰቢያ፡ አዳራሽና፡ ሎጂስቲክስ፡ በሙሉ፡ በመቆጣጠርና፡ በተጨማሪ፡ የድርጅቱን፡ እድገትና፡ ደህንነቱን፡ በማንኛቸውም፡ ግዜ፡ በመጠበቅ፡ ሰላሙን፡ ያስከብራል፡ ብለዋል::

፲፩ና፡ እንዲሁም፡ የዘውድ፡ ምክር፡ ቤቱ፡ ባስተላለፈው፡ ታላቅ፡ ውሳኔ፡ መሠረት፡ በበላይ፡ ጠባቂው፡ የጸደቀው፡ "የኢትዮጵያ፡ አርበኞች፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ የሕዝብ፡ ሠራዊት፡" በተቀዳሚ፡ ተግባሩ፡ የኢትዮጵያን፡ ሕዝብ፡ መሠረታዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ በታላቅ፡ ደረጃና፡ በታሪኩ፡ ባሕላዊ፡ ከበሬታ፡ ፍፁም፡ ዲሞክራሲያዊ፡ በሆነ፡ አላማ፡ አቋሙን፡ በግልጽ፡ በመከተል፡ ወደፊት፡ እንዲራመድና፡ ለኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ተጨባጭ፡ መተማመና እንዲሆነው፡ ዋስትና፡ ለማስገኘት፡ የሚያበቁትን፡ ዋና፡ ዋናዎቹን፡ የነፃነቱን ዲሞክራሲያዊ፡ ኑባሬዎቹን፡ ለመመሥረትና፡ የሰላም፡ ኑሮውን፡ በነፃነቱ፡ መብት፡ ከበሬታ፡ በራሱ፡ ኃላፊነት፡ ለማስተዳደር፡ ያበቃው፡ ዘንድ፡ ባጭሩ፡ ከዚህ፡ የሚቀጥለውን፡ የተቀደሰ፡ የጥሪ፡ መልዕክት፡ አዋጃቸውን፡ አስተላልፈዋል፤

RIGHT

ለኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት፣
የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፣
የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ አንድነት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት፣
ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡፡

ሀ) "ለመላው፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ በሃገራችንና፡ በስደት፡ ዓለም፡ በታላቅ፡ ስቃይና፡ ችግር፡ ላይ፡ ለሚገኘው፡ ጅግናው፡ ወገናችን፡ በሙሉ! የኢትዮጵያን፡ ሕዝብ፡ መሠረታዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ በተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኞችህ፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ ሕዝባዊ፡ ሠራዊትህ፡ የኅብረት፡ ትግል፡ ለማስገኘትና፡ በዲሞክራሲያዊ፡ ኑባሬዎችህ፡ ልዕልና፡ የኅብረተ፡ ብሔር፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የሕዝብ፡ ሸንጎ፡ እግዝዕናህን፡ አጽድቀህ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል፡) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥትህን፡ ለማቆም፡ የተሰለፈውን፡ ጀግናው፡ የኢትዮጵያን፡ ሕዝብ፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ ሠራዊት፡ በመደገፍ፡ የወገኖቻችንን፡ መስዋዕትነት፡ በሃገራችን፡ ታሪካዊ፡ ክበሬታ፡ ስም፡ በሚቻልህ፡ ሁኔታ፡ ሁሉ፡ አብረህ፡ በመካፈል፡ ተባብረህ፡ ተነስ! ይህንን፡ የጥሪ፡ መልዕክት፡ አዋጃችንን፡ እያስተጋባህ፡ ላልሰማው፡ አሰማ"፡ በማለት፡

RIGHT

ለኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት፣
የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዴሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፣
የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ አንድነት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት፣
ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡፡

ለ) "እያንዳንዱ፡ የኢትዮጵያ፡ **ዜጋ**፡ **በሙሉ**፡ በሰብአዊ፡ ክበሬታው፡ ሰላሙንና፡ ነፃነቱን፡ በመሠረታዊ፡ መብቱ፡ ልዕልና፡ በኅብረተ፡ ብሔሩ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ ሸንጎ፡ እግዝዕና፡ የሕዝብ፡ መንግሥቱን፡ በሰላምና፡ በፍጹም፡ ዲሞክራሲያዊ፡ ሂደት፡ ብዙሃን፡ የፖለቲካ፡ ፓርቲዎቹን፡ አቁሞ፡ ለሃገሩና፡ ለሕዝቡ፡ ብልጽግና፡ በመልካሙና፡ በገናናው፡ ተቆርቋሪና፡ አዛኝ፡ ጥሩ፡ ባሕርይው፡ ለታሪኩ፡ ክበሬታ፡ ለሃይማኖቱ፡ ቅድስና፡ የትውልዱን፡ ሙሉ፡ የትምህርትና፡ የጤናማ፡ እድገት፡ የተሟላ፡ የወደፊት፡ እድሉን፡ የአዛውንቱንና፡ የጀግኖቹን፡ ብቁ፡ ኑሮ፡ ንብረቱንና፡ እርስቱን፡ በጥንቃቄ፡ አስከብሮ፡ ጠብቆና፡ አሟልቶ፡ ለማስከበር፤

በራሱ፡ ኃይልና፡ በራሱ፡ ፈቃድ፡ በነፃ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የሕዝብ፡ ጠቅላላ፡ ምርጫ፡ ውሰኔ፡ ሰላማዊ፡ መንግሥቱን፡ በእውን፡ እስከ፡ እስካገኘና፡ የሃገሩን፡ ድንበርና፡ አንድነት፡ በቆራጥነትና፡ በመስዋዕትነት፡ ነፃነቱን፡ እስከ፡ አስከበረ፡ ድረስ፡ ህሊናው፡ እንደማያርፍና፡ ምንጊዜም፡ እንደማይቸነፍ፡ አኩሪ፡ የታሪኩ፡ ጠባይ፡ መስከሩ፡ ነው"፡ በማለት፡ ሲያረጋግጡ፡

መብት

አንድነት

SOLIDARITY

Liberty In Our Nation

RIGHT

ለኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት፤
የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፤
የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ አንድነት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት፤
ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡፡

ከአንግዲህ፡ ወዲህ፡ ኢትዮጵያችን፡ ለምንም፡ ዓይነት፡ የብቸኝነትና፡ የኮሙኒስት፡ ጭቆና፡ ስርዓት፡ ጊዜያዊም፡ ሆነ፡ ወታደራዊ፡ ወይም፡ ነጠላ፡ ብሔራዊ፡ የአምባ፡ ገነኖችና፡ የባዕድ፡ ስውር፡ የቅኝ፡ ግዛት፡ ቅጥረኞች፡ ኃይል፡ ብዝበዛና፡ ጭፍን፡ የአረመኔዎችና፡ የነፍሰ፡ ገዳዮች፡ የፋሽስት፡ ይዘት፡ እንዳትመች፡ የግልና፡ የኅብረት፡ የሕሊና፡ መሀላ፡ በማድረግ፤ ሐ) የተቀደሰውን፡ ብሔራዊ፡ ግዳጃችንንና፡ ግዴታችን፡ ተገንዝበነው፡ የዛሬውን፡ የውል፡ ቀን፡ ለኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ ልዕልና፡ በተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኞች፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ ሕዝባዊ፡ ሠራዊት፡ የኅብረት፡ ትግል፡ እዮሀ፡ የድል፡ ችቦ፡ የበራበት፡ አዲስ፡ ምዕራፍ፡ ሆኖ፡ በመቆጠር፡ "የኅብረት፡ ቀን፡" ተብሎ፡ በመጠራት፡ መጋቢት፡ ፳፱ ቀን፡ በየዓመቱ፡ በታላቅ፡ ሥርዓት፡ እንዲከበርና፡ እንዲሁም፡ በየወሩ፡ የዘወትር፡ ስብሰባ፡ ፕሮግራም፡ በማካሄድ፡ ብሔራዊ፡ የነፃነት፡ ትግሉን፡ ኢትዮጵያውያን፡ በሙሉ፡ በያሉበት፡ በሃዲስ፡ የኅብረት፡ መንፈስ፡ እንዲመሩት፡ ሲያሳስቡ፡ ጥልቅ፡ የሆነ፡ ደስታና፡ ኩራት፡ እንደሚሰማቸው፡ አረጋግጠዋል፡፡

መ ብ ት

አንድነት

SOLIDARITY

Liberty In Our Nation

RIGHT

ለኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት፣
የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፣
የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ አንድነት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት፣
ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡፡

የምሥራቹንም፡ ዜና፡ በያለበት፡ ለኢትዮጵያውያን፡ ወገኖቻችን፡ ሁሉ፡ እንዲደርሳቸው፡ ያህል፡ በሃገራችን፡ ዘዴና፡ ልማድ፡ መሠረት፡ እንዲነገርና፡ እንዲታወቅ፡ ሲፈቅዱ፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኞች፡ የአንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ ጀግኖች፡ ሁሉ፡ በበኩላቸው፡ ያልተቆጠበ፡ ትብብራቸውን፡ በተቀደሰው፡ ብሔራዊ፡ ግዳጃቸውና፡ መስዋዕትነታቸው፡ በገናናው፡ የኢትዮጵያ፡ ታሪካችን፡ ስም፡ እንዲፈጽሙ፡ በኃያሉ፡ የኢትዮጵያ፡ አምላካችን፡ ረዳትነት፡ እናሳስባችኃለን፡ በማለት፡
"ለኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ ልዕልና፡ ለተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኞች፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ ሕዝባዊ፡ ሠራዊታችን፡ የድል፡ ቀን፡ ከገናናው፡ ወገናችን፡ ጋር፡ ሁላችንንም፡ እንዲያበቃን፡ የክብር፡ ኃይል፡ ኮከብ፡ የጦር፡ ባልደረባችን፡ ቅዱስ፡ ጊዮርጊስ፡ ኃይልና፡ መከታ፡ ይሁናችሁ"፡ ብለው፡ ከመረቁ፡ በኃላ፡ "ኃያሉ፡ እግዚአብሔርም፡ በግፍ፡ የፈሰሰውን፡ ደም፡ ቆጥሮ፡ እንደሚረዳን፡ እንጠራጠርም!" በማለት፡ አስተማምነዋል፡፡

RIGHT

ለኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት፤
የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፤
የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ አንድነት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት፤
ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡፡

፩ኛ፡ ለኢትዮጵያ፡ የጦር፡ኃይልና፡ የፖሊስ፡ሠራዊት፡ ባልደረባ፡ ሁሉ፡ የተቀደሰ፡ የጥሪ፡ መልዕክት፡አዋጃቸውን፡ ሲያስተጋቡ፡ ከሁሉ፡ አስቀድሞ፡ የውድ፡ ሃገራችንን፡ አንድነት፡ የወሰንዋን፡ ከበሬታና፡ የሕዝባችንን፡ ደህንነት፡ ጠንክረው፡ በተለይ፡ ባሁኑ፡ ጊዜ፡ እንዲጠብቁ፡ ታላቅ፡ አደራቸውን፡ በማሳሰብ፡ አስከፊውን፡ የዳግማዊ፡ ፋሽስት፡ የጥፋት፡ ሁኔታን፡ ካለ፡ አንዳች፡ ጥርጥር፡ በኀሊናቸው፡ እንዲረዱትና፡ የተቀደሰ፡ ብሔራዊ፡ ግዳጃቸውን፡ ለዲሞክራሲያዊት፡ ኢትዮጵያችን፡ ሰላምና፡ ነፃነት፡ ለኅብረተ፡ ብሔራችን፡ አንድነትና፡ ብልጽግና፡ በቆራጥነት፡ የኅብረትና፡ የኢትዮጵያዊ፡ የነፃነት፡ ተግባራቸውን፡ በታወቁት፡ ጀግኖች፡ ወገኖቻችን፡ ገናና፡ ስም፡ በትጋትና፡ በቆራጥነት፡ ለመፈፀም፡ ይረዳቸው፡ ዘንድ፡ ያስተላለፉትን፡ ንጉሣዊ፡ ምክራቸውንና፡ ትዕዛዛቸውን፡ ከዚህ፡ ቀጥሎ፡ ባጭሩ፡ እንጠቅሳለን፤ ይኸውም፡ እንዲህ፡ ይላል፤

ሀ) **የኢትዮጵያ፡ የጦር፡ ኃይልና፡ የፖሊስ፡ ሠራዊት፡ ባልደረባ፡ ሁሉ!**

"ዛሬ፡ በአደባባይ፡ እራሳቸውን፡ በበላይህ፡ ተሿሹመው፡ ወደ፡ የማይጠፋ፡ እሳት፡ የሚነዱህ፡ ጥቂት፡ አምባ፡ ገነን፡ ወንበዴዎች፡ በግዜያዊ፡ ብለውም፡ በጉልታዊ፡ የሥልጣን፡ ጥቅም፡ ሸሚያ፡ ውድ፡ ሃገራችንን፡ በከባድ፡ ፋሽስታዊ፡

RIGHT

ለኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት፣
የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፣
የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ አንድነት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት፣
ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡፡

የባርነት፡ ቀንበር፡ በእጅ፡ አዙር፡ የባዕድ፡ ቅኝ፡ ግዛት፡ የኮሚኒስት፡ ወጥመድ፡ ስር፡ በመጣል፡ የምትክላትን፡ ውድ፡ ሃገርህንና፡ የነገይቱን፡ የኢትዮጵያ፡ ትውልድህን፡ የነፃነት፡ እድልና፡ ሰላማዊ፡ ሕይወት፡ ጭምር፡ በግፍና፡ በአረመኔ፡ ይዘት፡ አፍነው፡ ወገንህንና፡ እራስህንም፡ ስለጨፈጨፉት፡

በተለይም፡ በገናናው፡ የታሪክህ፡ ባሕልና፡ በግል፡ ሃይማኖትህ፡ ይዘት፡ እያፌዙ፡ እምነትህን፡ በማራከስና፡ ብሔራዊ፡ ንቃተ፡ ሕሊናህን፡ በማቃለል፡ የኢትዮጵያን፡ ሕዝብ፡ በሙሉ፡ የሕይወቱን፡ አለኝታና፡ ሕጋዊ፡ ይዘቱን፡ በማጥፋት፡ መሠረታዊ፡ የነፃነቱን፡ መብት፡ በማፈንና፡ ሰብዓዊ፡ የግል፡ ክበሬታውንና፡ ሰላማዊ፡ ኑሮውን፡ ጭራሹኑ፡ በመንሳት፡ ፈጽመው፡ ስላደኸዩት፤

ለ) አንተንም፡ ከኋላህ፡ በሃሴት፡ መለከት፡ ወደ፡ ጥፋት፡ የሚገፋፉህ፡ እጅህ፡ ውስጥ፡ ያሉት፡ ጥቂት፡ ወንበዴዎች፡ ዘላቂውን፡ የኢትዮጵያን፡ ሕዝብ፡ የጋራ፡ ጥቅምና፡ እድገት፡ በከሰረ፡ የኢኮኖሚ፡ ፕሮግራምና፡ በከረረ፡ የርዕዮት፡ ሂደት፡ እብሪተኝነትና፡ ማንአለኝህነት፡ ጭፍን፡ የበቀልና፡ የጥፋት፡ ማዕበል፡ ውስጥ፡ በመጣል፡ የአንድ፡እናት፡ ልጆች፡ የሆኑትን፡

RIGHT

ለኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት፣
የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፣
የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ አንድነት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት፣
ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡፡

ኢትዮጵያውያን፡ ወገኖቻችንን፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ አፍነው፡ የሃገራችንን፡ ብሔረሰቦች፡ ታላቅ፡ የታሪክና፡ የአንድነት፡ ሕልውና፡ በማቍሰል፡ መንፈሱን፡ አውከው፡ የሕዝባችንን፡ የግል፡ ይዞቱንና፡ ሰላሙን፡ በኃይልና፡ በግዴታ፡ እያደሙ፡ ጤና፡ በማሳጣት፡ ከፋፍለው፡ ለመግዛት፡ ሲሉ፡ በሰላምና፡ በግል፡ ባሕሎቻችን፡ ነፃነታዊ፡ መብት፡ በዲሞክራሲያዊ፡ ልዕልና፡ ከበሬታ፡ አንድ፡ አትዮጵያችን፡ በፍቅርና፡ በመተማመን፡ በኅብረት፡ ተመሥርታ፡ ከፍተኛ፡ የእድገት፡ እርምጃዋን፡ እንዳትይዝ፡ ለአስራ፡ አምስት፡ አመታት የጭለማ፡ ዘመን፡ በከፋትና፡ ጭራሹንም፡ በማያልቅ፡ የውሸት፡ ሰበባቸው፡ ፈጽሞ፡ ያገዱዋት፡ የመጀመሪያው፡ ትልቁ፡ አጥፊዎችህና፡ ጠላቶችህ፡ እነሱው፡ ናቸውና፤

ሐ) ከቅጥር፡ የግድያ፡ የባዕድ፡ ግብረ፡ አበሮቻቸው፡ ጋር፡ አንተው፡ እራስህ፡ የምታውቃቸው፡ እስከአሁንም፡ ዋናው፡ የኃይላቸው፡ ምንጭ፡ ሆነህ፡ ባንተው፡ ትከሻ፡ ያቆየሃቸው፡ ስለሆነ፡ የሃገሬ፡ ጐበዝ፡ በኢትዮጵያ፡ ትልቅ፡ የውስጥ፡ ጠላትና፡ በሽብርና፡ በግድያ፡ መሣሪያ፡ ባድር፡ ባዮች፡ አጥፊዎችህ፡ ፈጽሞ፡ አትመራ! ሳትጠራጠር፡ በቆራጥነትና፡ በጥንታዊው፡ የኢትዮጵያ፡ ገናና፡ ታሪክህ፡ ከበሬታ፡

መብት

አንድነት

SOLIDARITY

Liberty In Our Nation

RIGHT

ለኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት፣
የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፣
የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ አንድነት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት፣
ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡፡

በታላቁ፡ ስምህ፡ ተነስ! ትከሻህን፡ አዙር!

ኢትዮጵያ፡ ሃገርህን፡ ለማን፡ ፋሽስታዊ፡ የእጅ፡ አዙር፡ የባእድ፡ ቅኝ፡ ግዛት፡ ዳረግሀት? እንግዲህ፡ ሕዝባችንስ፡ ለማን፡ አቤት፡ ይበል? ወዴትስ፡ ይድረስ፡ ትላለህ? በማለት፤

መ) እውነት፡ እውነት፡ እልሃለሁ፡ የሃገራችንን፡ ውርደትና፡ መለያየት፡ እንጂ፡ ክብሯንና፡ አንድነቷን፡ ታሪካዊና፡ ገናና፡ ሕዝባችንን፡ ሞቱንና፡ ውእድቀቱን፡ እንጂ፡ ሰላሙንና፡ እድገቱን፡ ከአንጀቱ፡ የሚያስብና፡ የሚመኝ፡ ቃልኪዳናዊና፡ ጽኑ፡ የባዕድ፡ ወዳጅ፡ ካለራሱ፡ ጥቅም፡ በስተቀር፡ ምንግዜም፡ ስለሌለ፤ ማንኛቸውም፡ ታላላቅም፡ ሆኑ፡ ታናናሽ፡ የውጭ፡ ሃገር፡ መንግሥታቶች፡ እስከአሁንም፡ ድረስ፡ በአጥጋቢ፡ ደረጃ፡ እራስህ፡ የዲሞክራሲያዊ፡ ክንድህን፡ ካላሳየህ፡ ፈጽሞ፡ እንደማይረዱህ፡ አሳውቀውናልና፡ ሲሆን፡ እንደ፡ ጀግኖቹ፡ አባቶችህና፡ልጆችህ፤ ወይንም፡እንደ፡ ዛሬው፡ የአፍጋኒስታን፡ ሕዝብ፡ ወንድሞችህ፡ ከሕዝባችን፡ ጋር፡ ተባብረህ፡ "ለተቀደሰው"፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ በአንድነት፡ ትግል፡ ተነስ!

መብት

አንድነት

SOLIDARITY

Liberty In Our Nation

RIGHT

ለኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት፤
የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፤
የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ አንድነት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት፤
ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡፡

የኮሙኒስቶቹ፡ ወገንማ፡ ከሃገራችን፡ አጥፊዎች፡ ከፋሽስቶቹ፡ጠላቶችህ፡ጋራ፡ በሃሰት፡ እያደነፉ፡ ኢትዮጵያችንን፡ በእዳ፡ ደፍቀዋት፡ ያው፡ እንዳጥንቱ፡ ኮሎኒይሊስቶች፡ ያላትን፡ አብረው፡ በመዝረፍ፡ በገናናው፡ ታሪክህ፡ በጽኑ፡ ሃይማኖትህ፡ በጥንታዊ፡ ባህልህና፡ በታወቀው፡ ጀግንነትህ፡ ያፌዛሉ፡እንጂ፡ አይምሰልህ! እንኪንስ፡ ላንተና፡ ለምትወዳት፡ ሃገርህ፡ሊቆረቆሩ፡ ቀርቶ፡ ለራሳቸውም፡ አልሆኑምና፡ ለግልህም፡ ሆነ፡ ለትውልድህ፡ ቋሚና፡ ሰላማዊ፡ ጥቅምና፡ ብልጽግና፡ እርስትና፡ ንብረት፡ እንዳልሆኑህ፡ እራስህ፡ ፍረድ! የጭንቀትና፡ የመከራ፡ የሞትና፡ የድህነት፡ ማቅ፡ እነኝህ፡ ጠባብ፡ አብሪተኞችና፡ አረመኔ፡ ፋሽስቶች፡ በግዴታ፡ የኢትዮጵያን፡ ሕዝብ፡ ወገንህንና፡ እራስህንም፡ አያከናንቡህ፡

ሠ) <u>በታሪኳና፡ በነፃነቷ፡ ለአፍሪካና፡ ለዓለም፡ የጥቁር፡ ሕዝብ፡ በሙሉ፡ ጭምር፡ መኩሪያና፡ መከበሪያ፡ የነበረችውን፡ ታላቋ፡ ኢትያጵያችንን</u>፡ ፈሪሃ፡እግዚአብሔር፡ያደረበትን፡ ሃይማኖተኛና፡ ትልቅ፡ ሕዝብ፡ በአስተዳደጉ፡ ስርዓት፡ ታላቁን፡ አክባሪ፡ ምን፡ ግዜም፡ ወገኑንና፡ ሃገሩን፡ አፍቃሪ፡ በባሕሉ፡ የይሉኝታ፡ ጠባዩና፡ በፍትህ፡ እምነቱ፡ የተደነቀው፡ ለማወቅና፡ ለመበልጸግ፡ ፍጹም፡ ታታሪ፡ የሆነውን፡ <u>የጀግናውን፡</u>

ግርማዊ ቀዳማዊ አምሃ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ¤

ለኢትዮጵያ ኅብረተ ብሔር (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ የዘውድ መንግሥት

የበላይ ጠባቂ

መግቢያ

በየካቲት፡ ወር፡ ፲፱፻፷፮ ዓ፡ም፡ በተነሳው፡ ሁከት፣ የምንወደው፡ የኢትዮጵያ፡ ወገናችን፡ በድርቀትና፡ በረሃብ፡ አለንጋ፡ በመሰቃየትና፡ በሃገራችን፡ ላይ፡ የነዳጅ፡ ዋጋ፡ መናር፡ ያስከተለው፡ የኤኮኖሚ፡ ውድቀትና፡ የሰላሙ፡ መናጋት፡ ምክንያት ወዘተ ... አነሳስቶት፣ ከመሠረቱ፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ በሕጋዊ፡ ሂደት፡ የጊዜውን፡ የአስተዳደር፡ ጉድለትና፡ ተገቢውን፡ ነፃ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የሕዝብ፡ አስተዳደር፡ ሥልጣን፡ የሚመሠረትበትን፡ ሥርዓተ፡ ለውጥ፡ እንዲፈጸምለት፡ የሰነበቱት፡ ጥያቄዎቹ፡ በአደባባይ፡ ጎልተው፡ በተንጸባረቁበት፡ እለት፣

የሕዝባችንን፡ ብሶት፡ ለማሟላትና፡ ለጠቅላላው፡ የኢኮኖሚና፡ የፖለቲካ፡ የለውጥ፡ ይዘት፡ መሠረታዊ፡ መፍትሄውን፡ ለማስገኘት፡ በተደረገው፡ ጥረት፣ ከትክክለኛው፡ የሕዝባችን፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብቶች፡ ጥያቄዎች፡ ጋር፡ በመሰባጠር፣ የኮሚኒስት፡ ኢምፔሪያሊስትን፡ አቋም፡ አጥባቂዎች፡ የጦር፡ ኃይላችንን፡ ያስተዳደር፡ ጉድለት፡ ጥያቄዎች፡ ለማሰማት፡ በተወካይነት፡ ጊዜያዊ፡ ተጠሪ፡ በመሆን፡ ከተላኩት፡ ባልደረቦች፡ ውስጥ፡ ከጥቂቶቹ፡ ጋር፡ በስውር፡

በማደም፡ የመፈንቅለ፡ መንግሥት፡ ሴራ፡ በወታደሩ፡ ክፍል፡ ድጋፍ፡ ተካሔደ። በዚህም፡ የተነሳ፡ በሃገራችን፡ ላይ፡ እነኚሁ፡ ፋሺስታዊ፡ አምባ፡ ገነኖች፡ ባደረሱት፡ ሕገ፡ ወጥና፡ በታሪካችን፡ ታይቶ፡ ባልታወቀ፡ ደረጃ፡ በጣም፡ አሰቃቂ፡ የጭቆናና፡ የግድያ፡ የኮሚኒስት፡ ኢምፔሪያሊስቶች፡ ሰውር፡ የኰሎኒያሊስት፡ ሥርዓት፡ ታላቅ፡ ጥፋትና፡ ውርደት፡ በኢትዮጵያችን፡ ላይ፡ ሊያደርሱባት፡ ቻሉ። በተለይም፡ በሐሰት፡ ፕሮፓጋንዳ፡ ውርጅብኝ፡ የሕዝባችንን፡ ጥንታዊ፡ የታሪክ፡ የባሕልና፡ የሃይማኖቱን፡ ቅርስ፡ ከበሬታ፡ በማጥላላት፡ እንዲሁም፡ ሕጋዊ፡ ይዘቱን፡ ከመሠረቱ፡ በወንጀለኞቹ፡ አላማ፡ ጭራሹን፡ ለማውደም፡ በማያቋርጥ፡ አረመኔ፡ ተንኰል፡ ለማጥፋት፡ ይገዘግዙታል። የሕዝባችንን፡ መሠረታዊ፡ ብሶት፡ መፍትሔውን፡ ከማስገኘት፡ ይልቁንስ፡ የነበረውን፡ የሕዝቡን፡ መለስተኛ፡ ነፃነታዊ፡ አቋሙንና፡ በታሪኩ፡ ሥርዓት፡ በብዙ፡ ጊዜ፡ ድካም፡ መስዋዕትነትና፡ ልፋት፡ የተገኘውን፡ ኅብረቱን፡ ሰላማዊ፡ የአንድነት፡ ሕልውና፡ ሕጋዊ፡ ይዘቱንና፡ ውህደቱን፡ በማናጋት፡ በተንኰልና፡ በምቀኝነት፡ ቂም፡ በቀል፡ በመፈጸም፡ በጥቅምና፡ በሥልጣን፡ ጉጉት፡ እሽቅድምድም፡ የኢትዮጵያችንን፡ ታሪካዊ፡ የሰላምና፡ የብሔረ፡ ሰቡን፡ የእድገት፡ ገበታ፡ በቅዳሚያ፡ ደፍተው፡ ሕዝባችንን፡ የድህነተ፡ ማቅ፡ አለበሱት።

ሰላማዊ፡ ኅብረተሰቡንም፡ ባልተመሳከረ፡ የሐሰት፡ ፕሮፓጋንዳ፡ ወንጀል፡ ሆነ፡ ብለው፡ በማናከስ፡ በማጋጨትና፡ ካለፍርድ፡ በግፍ፡ በመግደል፡ ለብዙ፡ ጊዜ፡ የማይጠፋ፡ ያለመተማመንንና፡ የእርስ፡ በርስ፡ የጠላትነትን፡ የጠብና፡ የጦርነት፡ ቅርስ፡ በመፍጠር፡ የሰብአዊና፡ የፖለቲካ፡ ወንጀሎች፡ እንዲሁም፡ የከሰሩ፡ የኢኮኖሚ፡ ሂደት፡ ተግባሮችን፡ በኢትዮጵያ፡ ኅብረተ ሰቦች፡ ላይ፡ ፈጽመዋል፡፡ የሲቪሉን፡ ወገኖቻችንን፡ የኅብረት፡ ኃይላቸውንና፡ ትጥቃቸውን፡ በቅድሚያ፡ አስፈትተዋቸው፡ ንብረታቸውን፡ ዘርፈው፡ በሽብርና፡ በግድያ፡ ወንጀል፡ ተወጥረውና፡ ታፍነው፡ አካላታቸውና፡ መንፈሳቸው፡ አልቆ፡ በኀሊና፡ ሥቃይ፡ አሁንም፡ ጭራሹን፡ እየባሰ፡ በመሄድ፡ ሁኔታ፡ ውስጥ፡ ይገኛሉ፡፡ የነፃነት፡ ግንባር፡ ብለው፡ የታጠቁትም፡ አብዛኞቹ፡ ክፍል፡ በዛው፡ የኮሚኒስት፡ ኢምፔሪያሊስቶች፡ የብቸኝነት፡ ሂደትና፡ በጠባብ፡ ብሔረተኝነት፡ ተከፋፍለው፡ ዲሞክራሲያዊና፡ ሰፊ፡ የኅብረት፡ ግንባር፡ ሆነው፡ ለመቋቋም፡ ባለመፍቀዳቸውና፡ ነፃ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የሕዝቡን፡ እምነት፡ ባለማቀፋቸው፡ የሕዝባችን፡ ኃይልና፡ ኑሮ፡ ተመሰቃቅሎ፡ የተረፈው፡ ሃገሬው፡ በሙሉ፡ ሽማግሌው፡ አዛውንቱና፡ ወጣቱ፡ የጉበዝ፡ በር፡ በማጣት፡ ከዚህ፡ በፊት፡ ጭራሽ፡ በታሪካችን፡ በኢትዮጵያ፡ እምድር፡ ላይ፡ ደርሶባት፡ በማያውቀው፡ መጠን፡ ኑሮውና፡ ሕሊናው፡ በሞት፡ በስቃይና፡ በችግር፡ ማዕበል፡

በመጉላላቱ: ተፈናቅሎና: ከቤቱ: በብዛት: ተሰዶ: በዓለም: ላይ: ሁሉ: ተበትኖ: ይገኛል:: የተረፉት: ወገኖቻችን: ኢትዮጵያውያንም: በአረመኔው: የኮሚኒስት: ኢምፔሪያሊስቶች: የባርነት: ቀንበር: ስር: በደረሰባቸው: የችግርና: የሞት: አለንጋ: ገጻቸው: በልዞ: የወገን: ያለህ: የሚል: ጩኸታቸው: ከዳር: እስከዳር: እያስተጋባ: አሁንም: ይማቅቃሉ::

ይህንን: የጥፋት: ማዕበል: ከመሠረቱ: ነቅሎ: ፈጽሞ: ለማጥፋትና: በቦታውም: የኢትዮጵያን: ሕዝብ: ቋሚ: መሠረታዊ: የነፃነቱ: መብት: ልዕልና: የሚከበርበትን: የኅብረት: አላማ: በባለቤቱ: በሕዝቡ: ቁጥጥር: በተጨባጭ: ሥርዓቱ: እጁ: ለማስገባትና: ለማስረከብ: የኢትዮጵያን: አንድነትና: ኅብረተ: ብሔር: ሕጋዊ: አቋማችንን: በማንጸባረቅ: ለሕዝባችን: አለኝታ: በመቆም: እያንዳንዱ: ብሔረሰባችን: በእኩል: ኢትዮጵያዊነቱ: ከበሬታ: በኢትዮጵያ: ሕዝብ "ዲሞክራሲያዊ: የነፃነት: መብት: በአንድነት:" መሠረታዊ አላማ: በተባበሩት: "የኢትዮጵያ: አርበኞች: አንድነት የጦር: ኃይል: ሕዝባዊ: ሠራዊት:" አባልና: ግንባር: ቀደም: ሁኖ: የኅብረት: ትግሉን: በችሎታውና: ባለበት: ሁኔታና: ሥፍራ: ሁሉ: ተግባሩንና: ድጋፉን: በማሳየት: መሳተፍ: ይኖርበታል::

ከዚህም፡ በፊት፡ በተደረገው፡ ጥረትና፡ መስዋዕትነት፡ ብቁ፡ እርዳታ፡ ባለመገኘቱና፡ እንዲሁም፡ አልፎ፡ አልፎ፡ በነበረው፡ የመሪዎች፡ ተመሳሳይ፡ የሥልጣን፡ እሽቅድድም፡ ፉክክርና፡ የሥራ፡ አፈጻጸም፡ ጉድለትና፡ ውድቀት፡ ደጋግሞ፡ ስላገኘው፡ በተለይም፡ የቆዩ፡ ብዙሃን፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የፖለቲካ፡ ባሕሎችና፡ ልምዶች፡ ተጠናክረው፡ በኢትዮጵያ፡ ባለመኖራቸውና፡ ባለመመሥረታቸው፡ ታዳጊው፡ የሕዝባችን፡ ወገን፡ አቅም፡ አብዛኛውን፡ በብቸኝነት፡ የኮሚኒስት፡ ፍልስፍና፡ ወጥመድ፡ ስሪት፡ በመጠለፍ፡ እንዲሁም፡ በመጠኑ፡ በተለያዩ፡ የአመራር፡ ሂደቶች፡ ስልት፡ በተግባር፡ ተከፋፍለው፡ አንድ፡ በአንድ፡ በዛው፡ በፋሺስታዊው፡ የኮሚኒስት፡ ኢምፔሪያሊስት፡ የደርግ፡ የጭቆናና፡ የሽብር፡ የግፍ፡ ግድያ፡ ማዕበል፡ ስለተመቱ፡ ጠቅላላውን፡ ብሔረሰቡን፡ አቀፍ፡ "ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ በአንድነት፡" የትግል፡ ግንባርና፡ በሃገር፡ ውስጥ፡ በብቃት፡ ተደራጅተው፡ ለመሥራት፡ የተደራረቡ፡ የችግር ሁኔታዎች፡ ከልክለውት፡ የተወሰኑ፡ ብሔረተኛ፡ ስሪቶች፡ ብቻ፡ በማየል፡ ለኖሩ፡ ችለዋል፡፡

በሌላውም፡ በኩል፡ ነፃ፡ የዲሞክራሲያዊ፡ የኅብረት፡ አማኞችንና፡ ሌሎችንም፡ መሠረታዊ፡ የብሔረሰቡን፡ የባሕል፡ እምነት፡ የሚያንጸባርቁ፡ ጠንካራና፡ ነባር፡ የሃገሬው፡ ሕዝብ፡ ክፍል፡ "ሁሉን፡ መሰል፡" አጥፊ፡ ሰርጎ፡ ገቦች፡ በጥቅም፡

ተደራጅተው፡ ለነፃነቱ፡ ትግል፡ የቆመውን፡ ቆራጡ፡ ጀግና፡ ሕዝባችን፡ ጋር፡ በመሰባጠርና፡ ካለኅብረታዊ፡ እቅድ፡ በማጋፈጥ፡ ታላላቅ፡ ጀግኖቹንና፡ ጕበዞቹን፡ በማስጠለፍና፡ በማዳከም፡ የትግል፡ እርምጃቸውን፡ በማሰናከል፡ ውህደታቸውንና፡ ታሪካዊ፡ ሕልውናቸውን፡ ለማደፍረስ፡ ቢጥሩም፡ ታማኙና፡ ጠንካራው፡ ወገናችን፡ በየሃገራቸው፡ በአርበኝነት፡ ሥራ፡ ተሰማርተው፡ በግላቸው፡ ይዞት፡ ደጀናቸውን፡ አቁመው፡ በጀግንነት፡ ወንዛቸውን፡ ያስከብራሉ፡፡

ሆኖም፡ በዚሁ፡ የተዳከመ፡ አንፃር፡ በውጭ፡ ሃገሮችም፡ ያሉት፡ የትግሉ፡ ክፍሎች፡ በአንድ፡ መሠረታዊ፡ "ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ በአንድነት፡" አቋም፡ መተባበር፡ እስከአሁን፡ ድረስ፡ አቅቷቸው፡ በየአለቆቻቸው፡ ትንሽ፡ በተለየ፡ አቋምና፡ ልዩነት፡ የተነሳ፡ ለጊዜው፡ ሳይተባበሩ፡ በመቅረታቸው፡ እያዘንን፡

እኛም፡ ፍጹም፡ ነፃ፡ የዲሞክራሲያዊ፡ እምነታችንና፡ ዘላቂውን፡ የኢትዮጵያን፡ ሕዝብ፡ ብሔራዊና፡ መሠረታዊ፡ መብት፡ ጥቅም፡ እንጂ፡ ለግልና፡ ለሥልጣን፡ ሽሚያ፡ የማንሽቀዳደም፡ መሆኑን፡ ለሕዝባችን፡ ቀደም፡ ሲል፡ የታወቀ፡ ቢሆንም፡ በ፲፱፻፷፰ ዓ፡ም፡ የኀብረት፡ መልዕክታችንን፡ ለኢትዮጵያ፡ አርበኞች፡ እንዲተባበሩ፡ በኅቡዕ፡ አስታውቀነው፤

የሕዝባችንን፡ ቁርጠኛ፡ አቋምና፡ ፍላጎት፡ በሥርዓት፡ እስኪንጸባረቅ፡ ድረስ፡ በትዕግስትና፡ በጭንቀት፡ መንፈስ፡ ለብዙ፡ ጊዜ፡ ስንጠብቀው፡ የነበረውን፡

አሁን፡ የሕዝባችንን፡ መሠረታዊ፡ የነፃነቱን፡ መብት፡ በነፃ፡ የዲሞክራሲያዊ፡ ሥርዓት፡ ልዕልናው፡ በኅብረተ፡ ብሔሩ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የሕዝብ፡ ሸንጎ፡ ውሳኔ፡ እግዝዕና፡ ብዙሃን፡ ዲሞክራሲያዊ፡ ፓርቲውቹ፡ "በነፃ፡ ጠቅላላ፡ የሕዝብ፡ ምርጫ፡" ዳኝነት፡ ውሳኔ፡ ፀንተው፡ ከፍተኛ፡ የሕዝብ፡ ሰላማዊ፡ መንግሥቱን፡ አቁሞ፡ በአንድነቱ፡ የኅብረቱ፡ ኃይል፡ የሚከበርበትን፡ ሂደት፡ የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኞች፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ ሕዝባዊ፡ ንቅናቄን፡ በማስተባበርና፡ ለጀግናው፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ወገናችን፡ በሙሉ፡ የተቀደሰ፡ የጥሪ፡ መልዕክት፡ አዋጃችንን፡ በማሳወቅ፡ የኢትዮጵያን፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ መንግሥታችንን፡ ለማቋቋም፡ በስደተኛ፡ መንግሥት፡ አካል፡ የሕዝባችንን፡ ልዩ፡ የጦር፡ ካቢኔ፡ አቁመንለት፡ "ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነቱን፡ መብት፡ በአንድነቱ፡" የሚያስገኝበትን፡ የእምነት፡ አቋሙን፡ በማንጸባረቅ፡ በተበበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኞች፡ የጦር፡ ኃይል፡ ሕዝባዊ፡ ሠራዊት፡ የኅብረት፡ ትግል፡ በልጆቻችን፡ ፍቅርና፡ የደም፡ መስዋዕትነት፡ ድል፡ በታሪኩ፡ ክብር፡ መሠረት፡ ለማስገኘት፡ እንመራው፡ ዘንድ፡ በተጠየቅነው፡ በተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡

ብሔሮች፡ ርዕሳነ፡ መማክርት፡ አሳሳቢነትና፡ በዘውድ፡ ምክር፡ ቤታችን፡ ከፍተኛ፡ ውሳኔ፡ መሠረት፣ ተፈላጊውን፡ ዝግጅት፡ ለማከነውንና፡ የሚቻለውን፡ የአዛውንቱን፡ ምክር፣ የሕዝባችንን፡ የኅብረት፡ ኃይልና፡ ብቁ፡ የወገኖቻችንና፡ የወዳጆቻችን፡ ድጋፍ፡ ሁሉ፡ ለማስገኘትና፡ ለማሟላት፡ በከበሬታ፡ በመጠየቅ፣ ዛሬ፡ የካቲት፡ ፳፯ ቀን፡ ፲፱፻፹ ዓ ም፡ ውሳኔውን፡ በታላቅ፡ አክብሮት፡ ተቀብለን፡ የተጀመረውን፡ የተቀደሰ፡ የሕዝባችንን፡ የትግል፡ ሂደት፡ በብልህነት፣ በትጋትና፡ በቆራጥነት፡ ተግባርና፡ መስዋዕት፡ በእያንዳንዱ፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ወገናችን፡ ኅብረት፣ ለመሠረታዊ፡ መብቱ የነፃነት፡ ትግሉን፡ እንዲያካሄድ፡ በኃያሉ፡ አምላካችን፡ ረዳትነትና፡ ፍጹም፡ እምነት፡ ቆመን፡ የከበሬታ፡ አዋጃችን፡ ለጀግናው፡ ለኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ወገናችን፡ እንዲተላፍ፡ አዘናል፡፡

ግርማዊ፡ ቀዳማዊ፡ አምሃ፡ ሥላሴ፣

ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ዘኢትዮጵያ፡፡

ግርማዊ፡ ቀዳማዊ፡ አፄ፡ ኃይለ፡ ሥላሴ፣
ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ዘኢትዮጵያ፡፡

መመሪያ፡ አዋጅ፡፡

በተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ ርዕሳነ፡ መማክርት፡
ከፍተኛ፡ አሳሳቢነት፣
የኢትዮጵያን፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡
የዘውድ፡ መንግሥት፣ በሥርዓት፡ ለማቋቋም፡ የቀረበውን፡
የዘውድ፡ ምክር፡ ቤት፡ ታላላቅ፡ ውስኔዎች፣ በርዕሰ፡ ብሔሩ፡
በከበሬታ፡ የፀደቁበት፡ መመሪያ፡ የጥሪ፡ አዋጅ፡
ቋሚ፡ ሕግና፡ ትዕዛዞች፡፡

ቁጥር፡ ፳፯/፲፪/፯/፲፱፻፹
ከተራ፡ ቁጥር፡ ፩ እስከ፡፳
ከሹመት፡ ፩/፪/፫/ ቁጥር፡
ቃል፡ ውሳኔዎች፡ ጋር፡፡

የኢትዮጵያን፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት፤ በሕዝባችን፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ ሙሉ፡ ተሳትፎ፡ በሚገኘው፡ ቋሚና፡ ሕጋዊ፡ ነፃ፡ የጠቅላላ፡ የሕዝብ፡ ምርጫ፡ ውጤት፡ መሠረት፤ በከፍተኛ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የክብር፡ ሥርዓት፡ ለማቆም፤ በተቀዳሚ፡ የሕዝባችንን፡ "ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ በአንድነት፡" የተቀደሰ፡ ዓላማ፤ በግልጽና፡ በጉልህ፡ በማንፀባረቅ፤ የተባበሩት፡ የኢትዮጵያን፡ አርበኞች፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ የኅብረት፡ እንቅስቃሴን፡ በማስተባበር፡ የነፃነት፡ ትግሉን፡ በመቀየስና፡ በመምራት፤ የኢትዮጵያን፡ ሕዝብ፡ መሠረታዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ ለማስከበርና፡ በሕዝቡ፡ ነፃ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ ቋሚ፡ ኑባሬዎች፡ (እኒስቲትዩሽኖች) ልዕልና፤ በኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የሕዝብ፡ ሸንጎ፡ (ፓርላማ) እግዝዕና፤ ሰላማዊና፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የሕዝብ፡ መንግሥቱን፡ በነፃነቱ፡ መብት፡ ሕጋዊ፡ ሥርዓት፡ በአንድነቱ፡ ለማፅናት፡ እንዲቻል፡ ለማድረግ፤

እንዲሁም፡ የእያንዳንዱ፡ ብሔር፡ የውስጥ፡ አስተዳደር፡ ነፃነቱ፤ በግል፡ የባህሉ፡ ታሪካዊ፡ ይዘት፡ ትይዩ፡ ከበሬታ፡

በኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የሕዝብ፡ ሸንጎ፡ ውሳኔ፡ መሠረት፡ ሕጋዊ፡ ሁኖ፤ ለኢትዮጵያ፡ የአንድነት፡ ሕልውና፤ የኅብረት፡ አቋሙ፡ ዘለዓለማዊ፡ በመሆንና፡ በመጽናት፤ ለጠቅላላው፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔረሰብ፡ የጋራ፡ ጥቅም፤ እድገት፤ ደህንነትና፡ ማንኛቸውንም፡ ኅብረሰብአዊ፡ ግንኙነት፡ በኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የሕዝብ፡ ሸንጎ፡ ውሰኔ፡ እግዝዕና፤ ዲሞክራሲያዊት፡ ኢትዮጵያችንን፡ በአንድነቷና፡ በመሠረታዊ፡ ታሪኳ፡ ታላቅ፡ ከበሬታ፡ ፀንታ፡ በመቆም፤ በነፃነቷና፡ በሰላም፡ እንድትመሠረት፡ በማለት፤

ቀደም፡ ሲል፡ በጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤታችን፡ አማካኝ፤ በምስጢራዊ፡ ስትራተጂ፡ ታማኙ፡ ሕዝባችንን፡ በማስተባበር፡ ትግሉን፡ እየመራን፤ ኢትዮጵያችን፡ በዲሞክራሲያዊ፡ መብት፡ ልዕልና፡ በአንድነቷ፡ ፀንታ፤ በአርበኞቻችን፡ ጥረት፡ ነፃነቷን፡ ለማስገኘት፤ በ፲፱፻፸፯ ዓ፡ም፡ ያቆምነው፡ የዘውድ፡ ምክር፡ ቤታችን፤ በየካቲት፡ ፲፭ ቀን፡ ፲፱፻፹ ዓ፡ም፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ ርዕሳነ፡ መማክርት፡ ያሳሰቡትን፡ ከፍተኛ፡ የኅብረት፡ ጥያቄዎች፡ በማስተባበር፡ የኢትዮጵያን፡ ሕዝብ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፤ የተባበሩትን፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኞች፡

የትግል፡ ሠራዊት፡ በአንድ፡ መሠረታዊ፡ ዓላማ፡ በማስማማትና፡ በማሰባሰብ፡ እንመራው፡ ዘንድ፡ በተቀዳሚ፡ ባስተላለፈው ከፍተኛ፡ ውሳኔዎች፡ መሠረት፡ የኢትዮጵያ፡ ቆራጥ፡ ሕዝብና፡ ጀግናው፡ የአርበኞቹ፡ የትግል፡ መስዋዕትነት፡ ያፈራውን፡ የተቀደሰ፡ ወጤትና፡እንዲሁም፡ ርዕሳነ፡ መማክርቱ፡ በኅብረት፡ ተግባራቸው፡ ያስገኙትን፡ ታላቅ፡ የአርበኞቹ፡ የአንድነት፡ ኃይል፡ የውል፡ ስምምነት፡ መነሻና፡ መሠረት፡ በማድረግ፡ የሕዝባችንን፡ "ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ በአንድነት፡" የትግል፡ ዓላማ፡ ተገቢውን፡ ከፍተኛ፡ የክብር፡ ደረጃ፡ ለማስያዝ፡

በመጀመሪያ፡ በአልጋ፡ ወራሽነታችን፡ ከዚህ፡ በፊት፡ በጥቅምት፡ ፳፫ ቀን፡ ፲፱፻፳፫ ዓ፡ም፡ በቅባ፡ መንግሥት፡ ቁርባን፡ መሀላ፡ የፈጸምንበትን፡ የዘውድ፡ ወራሴነታችንን፡ ታሪካዊ፡ ሕግ፡ መንግሥታዊና፡ የተቀደሰ፡ ብሔራዊ፡ ተግባራችንን፡ በክብር፡ ሥርዓት፡ እንፈጽም፡ ዘንድ፡ የተጠየቅነውን፡ ሃላፊነታችንን፡ እኛም፡

የቀድሞው፡ አልጋ፡ ወራሽ፡
ልዑል፡ መርድ፡ አዝማች፡ አስፋ፡ ወሰን፡ ኃ፡ ሥ፡፡
የዛሬው፡ ጃንሆይ፡፡

የቀድሞዋ፡

ልዕልት፡ መድፈሪያሽ፡ ወርቅ፡ አበበ።

ለተወለድንባት፡ ላደግንባት፡ ለተሾምንባት፡ ዳግም፡ ለተሰደድንላት፡ ለተዋረድንላት፡ ለሞትንላትና፡ ወደፊትም፡ ለምንሞትላት፡ እጅጉን፡ በጣም፡ ለምንወዳት፡ ለምንናፍቃት፡ ለምንኰራባት፡ ለምናከብራት፤ ለኢትዮጵያችን፡ አንድነት፡ ለሕዝባችን፡ ነፃነትና፡ ለወገናቻን፡ ደህንነት፡ በምንም፡ የማንለውጠው፡ ብሔራዊና፡ የሚያኰራን፡ ምን፡ ጊዜም፡ ግዳጃችንና፡ ታሪካዊ፡ ኃላፊነታችን፡ መሆኑን፡ በጣም፡ ለምንወደው፡ ሕዝባችን፡ እያረጋገጥን፡

ከረጅም፡ ባጭሩ፡ ከብዙ፡ በጥቂቱ፡ የነፃው፡ ዓለም፡ መኩሪያ፡ የአፍሪካ፡ ነፃነት፡ መዳበሪያ፡ የጥቁር፡ ሕዝብ፡ ታሪክ፡ ማስከበሪያ፡ የነበረችውን፡ ጥንታዊት፡ ኢትዮጵያችንን፡ አንድነቷን፡ ነፃነቷንና፡ ሰላማዊ፡ የእድገት፡ እርምጃዋን፡ በብልህነት፡ በታላቅ፡ ትዕግሥትና፡ መሥዋዕት፡ ያቆዩልን፡ ጀግና፡ ወገኖቻችን፡ በቀድሞውም፡ የፋሽስት፡ የጦርና፡ የስደት፡ ግዜም፡ሆነ፡ በሰላሙ፡ ረጅም፡ ዘመን፡ ኢትዮጵያን፡ በአንድነቷ፡ ኃይል፡ የመሯትና፡ እንዲሁም፡ ለአፍሪካውያን፡ ትውልድ፡ በሙሉ፡ የሰብአዊነት፡ መሠረታዊ፡ መብቱንና፡ የእኩልነት፡ ክብሩን፡ በተለይም፡ የአፍሪካን፡ የነፃነትና፡ የአንድነት፡ ፀረ፡ ኮሎኒያሊስት፡ የትግል፡ ብሔራዊ፡ ንቅናቄዎች፡ ሁሉ፡



ግርማዊ፡ ቀዳማዊ፡
ታላቁ፡ ኃይለ፡ ሥላሴ፡፡

ቀደምተኛ፡ አጋርና፡ መመኪያ፡ በመሆንና፡ ከዚህም፡ አልፎ፡ ለዓለም፡ ፀጥታ፡ ለተባበሩት፡ መንግሥታትና፡ ለአፍሪካ፡ አንድነት ድርጅት፡ በኮሌክቲቭ፡ ሴኩሪቲ፡ ትልቅ፡ መስተዋጽዖ፡ በማድረግ፡ እኩል፡ ድርሻችንን፡ ከመክፈላችን፡ ሌላ፡ በተለይ፡ ኢትዮጵያችንን፡ በነፃነቷና፡ በአንድነቷ፡ ያስከበሩልን፡ እጥፍ፡ ድርብ፡ መስዋዕት፡ የሆኑትን፡ ጀግኖች፡ እውነተኛ፡ የኢትዮጵያ፡ ልጆች፡ ወገኖቻችን፡ ወንድምና፡ እህቶቻችን፡ እንዲሁም፡ ታላቅ፡ አባት፡ አስተዋይ፡ መሪና፡ አስታራቂ፡ ሽማግሌ፡ ከነበሩት፡ በጣም፡ ከምናከብራቸውና፡ ከምንወዳቸው፡ የኢትዮጵያን፡ ውለታቸውን፡ ፈጣሪ፡ አምላክ፡ እንጂ፡ ከእንግዲህ፡ ወዲህ፡ ሰው፡ የማይከፍላቸው፡ ከውድ፡ አባታችን፡ ከግርማዊ፡ ቀዳማዊ፡ "ታላቁ፡" ኃይለ፡ ሥላሴ፡ ሞዓ፡ አንበሳ፡ ዘእምነገደ፡ ይሁዳ፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ዘኢትዮጵያ፡ በሚተላለፈው፤

፩ኛ፡ ሲወርድ፡ ሲዋረድ፡ በመጣው፡ በኢትዮጵያ፡ አኩሪ፡ የጥንት፡ ታሪካችን፡ ቅርስ፡ የባሕላችን፡ ሕጋዊ፡ ሥርዓት፡ እንዲፈጸም፡ በማለት፡ በኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የሕዝብ፡ ሸንጎ፡ እግዝዕና፡ ተሻሽሎ፡ በተሀድሶ፡

የአባት፡ ለልጅ፡፡

መብት

አንድነት

Liberty In Our Nation

እናት፡ ወሎ፡፡

ግርማዊት፡ እቴጌ፡ መነንና፡ አሸብር፡፡

የሚጸናው: የኢትዮጵያን: ሕዝብ: መሠረታዊ: የነፃነት: መብቶቹንና: ዲሞክራሲያዊ: ኑባሬዎቹን: በራሱ: ታሪክ: አንፃር: በቀጥተኛ: የሚያንጸባርቅ: ሕግ: መንግሥታችን: በሕዝባችን: ነፃ: የጠቅላላ: ምርጫ: ቋሚ: ሆኖ: እስቲመረቅ: ድረስ: ለብዙ: ግዚያቶች: ሕጋዊ: በመሆን: በተሠራበት: አሁንም: ቋሚ: በሆነው: ሕግ: መንግሥታችን: ምዕራፍ: ፩: አንቀጽ: ፩: እስከ: ፳፫: መሠረት:

ሀ) ንጉሠ: ነገሥታዊ: ቅባ: መንግሥት: በመቀባት:
ግርማዊ: ቀዳማዊ: አምሃ: ሥላሴ:
ሞዓ: አንበሳ: ዘእምነገደ: ይሁዳ:
ንጉሠ: ነገሥት: ዘኢትዮጵያ።
በመባል: በንግሥና: ስማችን: ተሰይመን: በመጠራት: ዘውድ: እንድንቀዳጅና:

ለ) በደስታና: በመከራችንም: ግዚያቶች: ሁሉ: እኩል: የተካፈለችው: የምናከብራትና: የምንውዳት: ባለቤታችን:
ልዕልት: መድፈሪያሽ: ወርቅ: አበበን: በእቴጌነት: ሙሉ: ከበሬታ: ማዕረግ: እንድትሰየምና:

በቋሚው፡ ሕገ፡ መንግሥት፡ አንፃር፡ ምዕራፍ፡ ፩፡ እስከ፡ ፳፫፡ አንቀጽና፡ በተለይም፡ ስለዘውዱ፡ የዘውድ፡ አወራረስ፡ በወጣው፡ የግርማዊ፡ ቀዳማዊ፡ ኃይለ፡ ሥላሴ፡ አዋጅ፡ ትዕዛዝ፡ ቁጥር፡ ፺፩/፲፱፻፷፯፡ መሠረት፡ ልዑል፡ ዘርአ፡ ያዕቆብ፡ አስፋ፡ ወሰን፡ የአልጋው፡ ተጠባባቂነት፡ የፀደቀላቸው፤ ዛሬ፡ መጋቢት፡ ፳፮፡ ቀን፡ ፲፱፻፹፡ ዓ፡ ም፡ በአባታቸው፡ በግርማዊ፡ ቀዳማዊ፡ አምሃ፡ ሥላሴ፡ መልካም፡ ፈቃድ፡ በሙሉ፡ የአልጋ፡ ወራሽነት፡ ሥልጣን፤

በ "ልዑል፡ ዘርአ፡ ያዕቆብ፡ አምሃ፡ ሥላሴ"፡

ሥያሜ፡ ስርዓተ፡ መኃላቸውን፡ በመፈጸም፡ በክብር፡ ተሹመዋል፡፡

ሐ) እንዲሁም: በሕገ: መንግሥታችን: ምዕራፍ: ፩: አንቀጽ: ፩: እስከ: ፳፫: መሠረትና: በተለይም: ስለዙፋኑና: ስለዘውድ: አወራረስ: በወጣው: የውድ: አባታችን: የግርማዊ: ቀዳማዊ: "ታላቁ:" ኃይለ: ሥላሴ: አዋጅ: ትዕዛዝ: ቁጥር: ፯፩/፲፱፻፳፯: መሠረት: ተጠባባቂ: አልጋ: ወራሽነቱ: የፀደቀለት: በጣም: የምንወደውን: ወንድ: ልጃችን:

ልዑል: ዘርአ: ያዕቆብ: አስፋ: ወሰን: በሙሉ: የአልጋ: ወራሽነት: ሥልጣን: በመሾምና:

ተገቢውን: ቃለ: መሃላችንን: በኢትዮጵያ: ታሪካችን: ሙሉ: ከበሬታ: ሥርዓት: ሁላችንም: እንድንፈጽም: የተወሰነውን: ሕጋዊ: ታሪካዊና: ብሔራዊ: ግዳጃችንን: በታላቅ: አክብሮትና: ደስታ: በኢትዮጵያ: የኦርቶዶክስ: ተዋህዶ: ሃይሞኖት: ሙሉ: እምነት: ጸንተን: በከበሬታ: መሃላችንን: በመጋቢት: ፳፯: ቀን: ፲፱፻፹ ዓ: ም: ተቀብለን: ስናጸድቅ: የዚህንም: መለስተኛ: ክብረ: በዓል: በተወሰነ: የሚያመች: ጊዜና: ሥፍራ: በኦፊሴል: እንድናከብር: ሲሆን:

መ) የንግሥና፡ ሥርዓታችን፡ ግን፡ በተቀዳሚ፡ ዛሬ፡ በጭቆናና፡ በግድያ፡ በአምባገነኑ፡ ወታደራዊ፡ ሴረኞችና፡ በባዕድ፡ የኮሚኒስት፡ ኢምፔሪያሊስቶች፡ ኃይል፡ ሕገወጥ፡ ጣልቃ፡ ገብነት፡ በእጅ፡ አዙር፡ የቅኝ፡ ግዛት፡ ወረራ፡ ሂደትና፡ ድጋፍ፡ ኢሰብዓዊ፡ ፀረ፡ ዲሞክራሲያዊና፡ ፀረ፡ ሃይማኖት፡ ይዘት፡ በብቸኝነትና፡ በግዴታ፡ ርዕዮተ፡ ዓለም፡ በግፍና፡ በግድያ፡ የሽብርና፡ የጭንቀት፡ ሥርዓት፡ ውስጥ፡ በእርዛት፡ በረሃብና፡ በሞት፡ የሚሰቃየውን፡ ጀግናውን፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ወገናችንን፡ ለማዳን፡

በአርበኞቻችን፡ የኅብረትና፡ የአንድነት፡ ኃይል፡ ቋሚ፡ የሚሆነውን፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነቱን፡ ድል፡ በሚያስገኘው፡ የመሠረታዊ፡ መብቱ፡ ልዕልና፡ ዲሞክራሲያዊና፡ ነፃ፡ የሆኑትን፡ ብዙሃን፡ ኑባሬዎቹን፡ በኅብረት፡ አቁሞ፡ በሰላሙ፡ ሕጋዊ፡ ከበሬታ፡ በሕዝባችን፡ ነፃ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ ጠቅላላ፡ የሕዝብ፡ ምርጫ፡ ውሳኔ፡ የኢትዮጵያን፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት፡ ሕጋዊ፡ ሥልጣን፡ በየተወሰኑት፡ ግዚያቶች፡ አቸናፊ፡ የሚሆኑት፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የፓለቲካ፡ ፓርቲዎች፡ በሰላም፡ ሲረካከቡና፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ የነፃነቱን፡ አርማ በሚቀዳጅበት፡ ዕለት፡

እኛም፡ የንግሥና፡ ሥርዓታችንን፡ በምንወዳትና፡ በምንናፍቃት፡ በሃገራችን፡ በኢትዮጵያ፡ መሬት፡ ላይ፡ በኃያሉ፡ የኢትዮጵያ፡ አምላካችን፡ ፈቃድና፡ ቸርነት፡ ብሔራዊ፡ ተግባራችንን፡ በሙሉ፡ ከበሬታ፡ እንፈጽማለን፡፡

ሠ) እስከዛሬውም፡ ድረስ፡ ግን፡ ለኢትዮጵያ፡ ሕዝብና፡ ለአርበኞቻችን፡ የአንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ ከፍተኛ፡ የትግል፡ ንቅናቄዎች፡ ሥራና፡ ጥቅም፡ ሙሉ፡ የንግሥና፡ የማዕረግ፡ ስማችንን፡ ከዛሬው፡ አዋጅ፡ ቀን፡ ጀምሮ፡ በፕሮቶኮል፡ በከበሬታ፡ ሥርዓት፡ በታሪካችንና፡ በሕግ፡ መንግሥታችን፡ ትይዩ፡ ለኢትዮጵያ፡ የአንድነት፡ አርማ፡ ሆኖ፡ እንዲሠራበት፡ በታላቅ፡ አክብሮት፡ ወደን፡ ፈቅደናል፡፡

እንግዲህ፡ ለታላቁ፡ እውነተኛ፡ የኢትዮጵያ፡ ታሪክህ፡ ክብር፡ ለሕዝባችን፡ የነፃነት፡ ዲሞክራሲያዊ፡ መብት፡ ልዕልና፡ ለተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኞቻችን፡ የአንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ የተቀደሰ፡ መስዋዕትነት፡ ጀግናው፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ወገናችን፡ ሆይ፡ የአንድነትህ፡ ምሶሶህ፡ እነሆ፡ ቆሞልሀል፡ ለዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነትህ፡ መብት፡ ልዕልና፡ የአንድነትህንና፡ የኅብረትህን፡ የተቀደሰ፡ የትግል፡ ዓላማ፡ ፈጽም፡፡

የምሥራቹንም፡ ለወገኖቻችን፡ ለኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ሁሉ፡ አሰማ፡ ታሪክህን፡ አስከብር፤ ፈቃድህም፡ ይፈጸም፡ ፈጣሪ፡ አምላካችን፡ ክብሩ፡ ይስፋ፡ የተቀደሰ፡ ኅብረትህ፡ ኃይልና፡ ክብርህ፡ ነው፡፡ አይዞህ፡ በርታ፤ በእውነት፡ ሕልውናህ፡ ለሰላማዊ፡ የእድገት፡ ኑሮህ፡ ለቤተሰብህ፡ ክብርና፡ ደህንነት፡ ለሃይማኖትህና፡ ለዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መሠረታዊ፡ መብትህ፡ ልዕልና፡ ለሕዝባችንና፡ ለውድ፡ አገራችን፡ አንድነት፡ ክብርና፡ ብልጽግና፡ ለመጪው፡ ትውልድህ፡ የእኩልነት፡ እድል፡ በልጆችህ፡ ፍቅርና፡ የደም፡ መስዋዕትነት፡ ለፍትህ፡ ታጠቅ፡፡

እንኳንስ፡ የቤትህን፡ ጠላት፡ ቀርቶ፡ የውጭ፡ ጠላትህንም፡ በታሪክህ፡ ረጅም፡ ዘመን፡ ከአንዴም፡ ሁለት፡ ሦስቴ፡ በጀግንነት፡ ተቋቁመህል፡ እውነተኛው፡ ኢትዮጵያዊ፡ ወገናችን፡ ምን፡ ጊዜም፡ አይተኛም፡ አይቸነፍምም፡፡ አሁንም፡ ድልና፡ ክብር፡ የጀግናው፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ የገናናው፡ ወገናችን፡ እንደሚሆን፡ ጥርጥር፡ የለውም፡፡

ዲሞክራሲያዊት፡ ኢትዮጵያችን፡ ታቸንፋለች፡፡

ይህንኑም፡ ለመፈጸም፡ እግዚአብሔር፡ ይርዳን፡፡
ዲሞክራሲያዊ፡የነፃነት፡ መብት፡ በአንድነት፡፡

ግርማዊ ቀዳማዊ አምሃ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

ለኢትዮጵያ ኅብረተ ብሔር (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ የዘውድ መንግሥት

የበላይ ጠባቂ



ግርማዊ፡ ቀዳማዊ፡ አምሃ፡ ሥለሴ፣
ሞዓ፡ አንበሳ፡ ዘምነገደ፡ ይሁዳ፣
ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ዘኢትዮጵያ፡፡

፲፫ኛ፡ የዘውድ፡ ምክር፡ ቤታችንም፡ የኢትዮጵያን፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ ጠቅላላ፡ ብሔረሰቦችና፡ የኢትዮጵያን፡ ርዕሰ፡ ብሔር፡ ተግባር፡ በሚመለከት፡ ዓቢይ፡ ጉዳዮች፡ ሁሉ፡

ሀ) ታሪካዊ፡ ሕጋዊና፡ ባሕላዊ፡ የሆነውን፡ የንጉሠ፡ ነገሥቱን፡ ተገቢ፡ ግንኙነቶች፡ ሕገ፡ መንግሥታዊውን፡ አቋምና፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ በአንድነቱ፡ ፀንቶ፡ የነፃነቱን፡ መብቶች፡ ለማስከበር፡ እንዲችል፡ የበላይ፡ ጠባቂነቱን፡ ተግባር፡ ለብሔረሰቡ፡ የእኩልነት፡ ጠቅላላ፡ ጥቅምና፡ በአንድነት፡ ህልውና፡ ሚዛን፡ ባሕላዊ፡ አክብሮቱ፡ በሥርዓት፡ ተሟልተው፡ የሚውሉበትንና፡ የሚያበቁትን፡ መልካም፡ አርዐያነትን፡ የሚያስገኙ፡ ተግባሮችን፡ ታሪካዊ፡ ቅርስን፡ የተመረኰዘ፡ ብልህነትንና፡ አርቆ፡ አስተዋይነትን፡ የሚያንፀባርቁ፡ ብቁና፡ ወቅታዊ፡ የሃገር፡ ሽማግሌ፡ ምክሮችን፡ በመስጠት፡ ማንኛቸውንም፡ የኅብረተ፡ ብሔሩን፡ ታላላቅ፡ ጉዳዮች፡ ሁሉ፡ ወጉንና፡ ሕዝባዊ፡ ተገቢ፡ የከበሬታ፡ ሥርዓቱን፡ ማስያዝ፡ የዘወትር፡ አንደኛው፡ ተግባራቸው፡ እንዲሆን፡ ለማድረግና፡

ለ) በተቀዳሚም፡ የዘውድ፡ ምክር፡ ቤታችን፡ በልዩ፡ ጥሪያችን፡ መሠረት፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ በነፃነቱ፡ መብቶች፡ ዲሞክራሲያዊ፡ ልዕልና፡ ከበሬታ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡የዘውድ፡መንግሥታችንን፡እስከ፡አቆመ፡ ድረስ፤ ለተባበሩት፡የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ የአርበኞቹ፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ ሕዝባዊ፡ ሠራዊት፡ ስትራተጂካዊ፡ ሂደት፡ የተረጋገጠ፡ የድል፡ ውጤት፡ የሚያስገኘውን፡ አጠቃላይ፡ ፖሊሲ፡ በልዩ፡ ካቢኔው፡ ጠቅላይ፡ የጦር፡ መምሪያችን፡ የበላይ፡ ዕቅድና፡ ፕሮግራም፡ መሠረት፡ በትብብር፡ እንዲቀናበር፡ የሚያስችሉትን፡ ሙሉ፡የትግሎቹን፡ንቅናቄዎችና፡ የውህደት፡ እርምጃዎች፡ ሁሉ፡ በኅብረት፡ ይቀይሳል፡፡ በክፍለ፡ ሃገሮቹም፡ ውስጥ፡ አመቺውን፡ ቦታዎች፡ የጦሩ፡ ኃይል፡ ንቅናቄዎች፡ የሚሠማሩበትንና፡ ግዚያዊና፡ስትራተጂካዊ፡ጣቢያዎችን፡ በማስናዳት፡ የሎጂስቲኩ፡ ደጃኖቹ፡ተጠናክረው፡እንዲመሠረቱና፡እንዲስፋፉ፡ ማንኛቸውንም፡ ዕርዳታና፡ መረጃዎችን፡ በወቅቱ፡ በማከማቸት፡ ከጀግናው፡ የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡ ጐን፡ አብሮ፡ በመሠለፍ፡ በታሪኩ፡ ከበሬታ፡ ብሔራዊ፡የተቀደሰ፡ተግባሩንና፡የአንድነት፡መሥዋዕቱን፡ይፈጽማል፤ በማስተባበርም፡ የአርበኞቹን፡ የአንድነት፡ ጦር፡ ኃይል፡ በኅብረት፡ ያዘምታል፡፡

ሐ) እንዲሁም፡ ለካቢኔው፡ የሥራ፡ ፕሮግራም፡ ባስፈለጉበት፡ ጊዜ፡ ሁሉ፡ በቅርብ፡ በመገኘት፡ በልዩ፡ እንደራሴው፡ አቅራቢነት፡ በርዕሰ፡ ብሔሩ፡ ውሳኔ፡ የልዩ፡ ካቢኔውን፡ የተልዕኮ፡ ሚሺኖችን፡ እየመሩ፡ ተገቢውን፡ ምልአተ፡ ክብርና፡ ብሔራዊ፡ ግልጋሎታቸውን፡ ይሰጡ፡ ዘንድ፡

አሥራ፡ ሁለት፡ ቋሚ፡ ርዕሰ፡ መማክርቶች፡ በመልካም፡ አርአያነታቸው፡ ለንጉሠ፡ ነገሥቱ፡ ታማኝና፡ ለኅብረተ፡ ብሔሮቹ፡ ቀጥተኛ፡ ተጠሪ፡ በመሆን፡ ተመርጠው፡ የተወከሉትን፡ አባላት፡ ተገቢውን፡ የክብር፡ ደረጃ፡ ይዘው፡ በዘውድ፡ ምክር፡ ቤታችን፡ ተጨማሪ፡ ርዕሰ፡ መማክርት፡ ሆነው፡ እንዲሾሙ፡ ይደረግ፡ ዘንድ፡

እንዲሁም፡ የወቅቱ፡ ተጨባጭ፡ የኢትዮጵያ፡ ሁኔታ፡ እንደሚፈቅደው፡ ለዚሁ፡ ከፍተኛ፡ የክብር፡ ሃላፊነት፡ ርዕሰ፡ መማክርቶቹ፡ ለመገኘት፡ በማያመቻቸው፡ ግዜያቶች፡ ሁሉ፡ ባለሙሉ፡ ሥልጣን፡ የክብር፡ ተጠሪና፡ እንደራሴአቸውን፡ ለልዩ፡ ካቢኔው፡ በማስታወቅ፡ ሙሉ፡ የሥራ፡ ገበታቸውን፡ በከበሬታ፡ እንዲይዙ፡ ለማድረግ፡ ያህል፡ የቀረቡልንን፡ ውሳኔዎች፡ በታላቅ፡ አክብሮት፡ ተቀብለን፡ አጽድቀናል፡፡

መ) ስለዚህም፡ የዘውድ፡ ምክር፡ ቤታችን፡ ርዕሰ፡ መማክርትና፡ የልዩ፡ ካቢኔው፡ አባሎች፡ የርዕሰ፡ ብሔሩ፡ እንደራሴዎችና፡ የልዩ፡ ካቢኔው፡ ወኪል፡ አምባሳደሮች፡ እንዲሁም፡ የ"መብት"ና፡ የ"አንድነት፡" አምዶች፡ ተጠሪዎችን፡ የሚይዝ፡ ዓመታዊና፡ ቋሚ፡ የጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤታችን፡ ጠቅላላ፡ ጉባኤ፡ (ኮንግሬስ)፡ ለመጥራት፡ ይቻል፡ ዘንድ፡ በልዩ፡ ካቢኔአችን፡ አስተባባሪና፡ አቅራቢነት፡ የኢትዮጵያን፡ ሕዝብ፡ የነፃነታዊ፡ መብት፡ ሽግግር፡ እርምጃና፡ የተባበሩት፡ የኢትዮጵያን፡ አርበኞች፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ ሕዝባዊ፡ ሠራዊት፡ ግሥጋሴና፡ ሌሎችም፡ ዓመታዊ፡ ሪፖርቶችን፡ ለመስማትና፡ ተገቢውን፡ ምክርና፡ ውይይቶችን፡ በመለዋወጥ፡ ቋሚ፡ ሃላፊዎችንና፡ ብቁ፡ መሪዎችን፡ እንዲመርጥና፡ እንዲያጸድቅ፡ በምስጢራዊ፡ ስትራተጂ፡ እንዲሰበሰብ፡ የሚቻለውን፡ ለማድረግ፡ የጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤታችንን፡ ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡ አዘናል፡፡

ሠ) በክብርና፡ የማዕርግ፡ ስም፡ አሰጣጥ፡ አንፃር፡ በሕገ፡ መንግሥታችን፡ ምዕራፍ፡ ፬፡ አንቀጽ፡ ፴፩፡ መሠረት፡ እስከ፡ አሁን፡ ድረስና፡ ለወደፊቱም፡ ለንጉሠ፡ ነገሥቱ፡ በታማኝነትና፡ ለኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ በሰብአዊ፡ ክብሩ፡ በመሠረታዊው፡ የነፃነቱ፡ መብት፡ ዲሞክራሲያዊ፡ ልዕልናው፡ የሚከበርበትን፡ የኢትዮጵያን፡ አርበኞች፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ ኅብረት፡ በመደገፍ፡ የተቀደሰውን፡ የትግሉን፡ መስተዋጽዖ፡ ድርሻ፡ በኢትዮጵያችን፡ ስምና፡ ለአንድነቷና፡ ለነፃነቷ፡ ሕልውና፡ ከበሬታ፡ ለማስገኘት፡ በማንኛቸውም፡ ሁኔታ፡ በቆራጥነት፡ ላገለገሉትና፡ በተለይም፡ መስዋዕት፡ ለሆኑት፡ ጀግኖች፡ የኢትዮጵያ፡ወገኖቻችንና፡እንዲሁም፡የኢትዮጵያ፡የጭንቀት፡ ግዜ፡ ወዳጆችዋ፡ ሁሉ፡ የስም፡ ዝርዝራቸው፡ በፕሮቶኮል፡ ማዕርግ፡ በከበሬታ፡ታውቆ፡ በመመዝገብ፡ የማዕርግ፡ ስም፡ ክብርና፡ ኒሻን፡ እንዲሰጣቸው፡ ያህል፡ በልዩ፡ ከቢኔው፡ አቅራቢነት፡ "የጀግኖች፡ የክብርና፡የሹመት፡ልዩ፡ ማህደር፡" በወቅቱ፡ ተሰናድቶ፡ ለንጉሠ፡ ነገሥቱ፡በጠቅላይ፡ምክር፡ ቤት፡ ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡ አስተባባሪነት፡በወግና፡በማዕርግ፡ሙሉ፡ታሪካዊ፡ከበሬታው፡ተሟልቶ በመቅረብ፡በሥርዓት፡እንዲፈጸምና፡እንዲሠራበት፡ በማለት፤

እንዲሁም፡ ከዚህ፡ በፊት፡ ሹማምንቶችና፡ መኰንኖች፡ ሲጠሩበት፡ የነበረውን፡ የክብርና፡ የማዕርግ፡ ስም፡ እንዳያዙ፡ በመኖር፡ ለንጉሠ፡ ነገሥቱና፡ በዚሁ፡ ሥርዓት፡ ለሚቆመው፡ የኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥታችን፡ የሥራና፡ የትግል፡ ባልደረቦችና፡ አባሎችም፡ የክብርና፡ የማዕርግ፡ እድገትና፡ ሽልማት፡ እንዲሰጣቸው፡ የቀረቡልንን፡ ውሳኔዎች፡ ሁሉ፡ በታላቅ፡ አክብሮት፡ ተቀብለን፡ እንዲሠራባቸው፡ አዘናል፡፡

ለኢትዮጵያ ኅብረተ ብሔር (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ የዘውድ መንግሥት

የበላይ ጠባቂ

ግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

የዘውድ ምክር ቤት ።



ግርማዊ ቀዳማዊ አምሃ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

ለኢትዮጵያ ኅብረተ ብሔር (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ የዘውድ መንግሥት

የበላይ ጠባቂ

፫ኛ፡ ለኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነቱ፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፡ ሆኖ፡ እንዲሠራ፡ ያቆምነው፡ ጠቃላይ፡ ምክር፡ ቤታችን፡ ለብዙ፡ ግዜያት፡ በምስጢራዊ፡ ስትራተጂ፡ አመራር፡ ሲያኪያሄድ፡ የቆየውን፡ ተግባሮችና፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ የአርበኞቹ፡ የትግል፡ መስዋዕትነት፡ ያፈራውን፡ የተቀደሰ፡ ውጤትና፡ እንዲሁም፡ በማስተባበር፡ ተግባሮቹ፡ ያስገኘውን፡ ታላቅ፡ የአርበኞቹ፡ የአንድነት፡ ኃይል፡ የውል፡ ስምምነት፡ መሠረት፡ በማድረግ፤

ሀ) ለመንግሥታዊ፡ ተግባሩ፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤታችን፡ በከፍተኛ፡ ደረጃ፡ልዩ፡ካቢኔ፡በማቋቋም፡ እንዳስፈላጊነቱ፡ሁኔታና፡ ጊዜ፡ በልዩ፡ እንደራሴው፡ አቅራቢነት፡ በታላቅ፡ ኃላፊነትና፡ በምስጢራዊ፡ ስታራተጂ፡ እንዲሠራ፡ ፈቅደን፡ የሾምነውን፡ ከፍተኛ፡ ባለሥልጣኖችና፡ የልዩ፡ ካቢኔውን፡ አባሎች፡ ስም፡ ዝርዝር፡ በማጽደቅ፡

ለ) ለሃገር፡ አንድነትና፡ ለሕዝብ፡ ደህንነት፡ አስጊ፡ የሆነውን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ በተቀላጠፈ፡ ሁኔታና፡ በአንድ፡ የአመራር፡ ሥርዓት፡ አቋም፡ በኅብረት፡ ለማስወገድና፡ መከላከያውንና፡ አንድነቱን፡ ለማጠናከር፡ ያመች፡ ዘንድ፡ በዘውድ፡ ምክር፡ ቤታችን፡ የቀረበልንን፡ ታላቅ፡ ውሳኔዎች፡ በሙሉ፡ ከበሬታና፡ በሕገ፡ መንግሥታዊ፡ ሥልጣናችን፡ ምዕራፍ፡ ፪፡ አንቀጽ፡ ፳፱፡ እና፡ ፹፯፡ መሠረት፡ "በመከላከል፡ የጦር፡ አዋጅ፡ ሥርዓት፡" ልዩ፡ ካቢኔው፡ በጦር፡ ኃይላችን፡ ጠቅላይ፡ አዛዥ፡ ወይም፡ በተጠባባቂው፡ የጦር፡ ኃይል፡ጠቅላይ፡ አዛዥ፡ ሰብሳቢነት፡ በልዩ፡ እንደራሴያችን፡ የባለ፡ ሙሉ፡ ሥልጣን፡ ኃላፊነት፡ እንዲቋቋም፡ ፈቅደን፡ አዘናል፡፡

ሐ) ልዩ፡ ካቢኔው፡ ተግባሮቹን፡ ለመፈጸም፡ የሚያስፈልጉት፡ መብቶችና፡ ሥልጣኖች፡ በሙሉ፡ ይኖሩታል፤ ይኸውም፡ በጦር፡ ግዜ፡ አስተዳደር፡ የጦር፡ ሕግና፡ የሚጠቀሙበትን፡ አስቸኳይ፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ለማደራጀት፡ በማጽደቅ፡ ያውጃል፤

በኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ ውስጥ፡ ሁከት፡ ወይም፡ በአንድነቱ፡ ላይ፡ አደጋ፡ የሚያመጣውን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ለማስወገድ፡ መከላከያውንና፡ አንድነቱን፡ ለማረጋገጥ፡ አስፈላጊውን፡ እርምጃ፡ እንዲወስድና፡ እንዲሠራበት፡ በሙሉ፡ ድምጽ፡ ያለፈውን፡ የዘውድ፡ ምክር፡ ቤታችንን፡ ጠቅላላ፡ ውሳኔ፡ በታላቅ፡ አክብሮት፡ በኢትዮጵያ፡ ሃገራችን፡ አንድነት፡ ለሕዝባችን፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነቱ፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፡ የከፈለው፡ የተቀደሰ፡ መሥዋዕትነትና፡ በአርበኞቻችን፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ ሕዝባዊ፡ ሠራዊት፡ ኀብረት፡ የተረጋገጠ፡ ታሪካዊ፡ የትግላችን፡ ድል፡ ስም፡ ወደን፡ አጽድቀናል፡፡

መ) ልዩ፡ ካቢኔው፡ በውጭ፡ ጉዳይ፡ መመሪያው፡ ከመሠረቱ፡ ለጠቅላላውና፡ ለዘላቂ፡ የኢትዮጵያ፡ ነፃነትና፡ የአንድነቱን፡ ጥቅም፡ የሚያስገኙትን፡ ግንኙነትና፡ አቋሙን፡ ከማይፃረሩ፡ ነፃ፡ ዲሞክራሲያውያን፡ ኃይሎች፡ ጋር፡ ይተባበራል፡፡ እንዲሁም፡ በኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ፈቃድ፡ በሕግ፡ ተቋቁሞ፡ በሕዝብ፡ ምክር፡ ቤቶች፡ ጸድቆ፡ ይሠራበት የነበረውን፡ ከውጭ፡ ሃገር፡ መንግሥታትና፡ ከሌላም፡ ድርጅቶች፡ ጋር፡ የተደረገውን፡ ውል፡ ስምምነቱ፡ ተጠብቆ፡ ከኖረ፡ ያከብራል፡፡

በውንብድና፡ ሥልጣን፡ ዘርፎ፡ የቆየው፡ የአምባ፡ ገነኑ፡ የጭቆና፡ ኃይል፡ ሥርዓት፡ የገባቸውን፡ ግዴታዎች፡ ያደረጋቸውን፡ ውሎችና፡ ስምምነቶች፡ ግን፡ በኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ነፃ፡ዲሞክራሲያዊ፡ ፈቃድ፡ ያልተቋቋሙ፡ በመሆናቸው፡ በሕዝቡ፡ ላይ፡ ተፈጻሚነት፡ ሊኖራቸው፡ ስለማይችሉ፡ በሙሉ፡ ውድቅ፡ ይሆናሉ።

ዲሞክራሲያዊት፡ ኢትዮጵያችን፡ የአፍሪካን፡ ድርጅትና፡ የዓለም፡ መንግሥታት፡ ማኅበርን፡ ቻርተር፡ አክብራ፡ በኮሌክቲቭ፡ ሴኩሪቴ፡ ዓላማ፡ ፀንታ፡ የአባልነት፡ ግዴታዋን፡ ትፈጽማለች። የጐረቤት፡ ወዳጅ፡ ሃገሮችን፡ ሰላምና፡ ትክክለኛውን፡ ድንበር፡ በማክበር፡ በመልካም፡ ጉርብትና፡ በወንድማማችነት፡ ትኖራለች።

በዓለም፡ ላይ፡ የኢሰብዓዊና፡ የጭቆና፡ ኃይል፡ ወንጀሎችን፡ ታወግዛለች። በነፃ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ ሥርዓት፡ የተመሠረቱትን፡ መንግሥታት፡ወዳጅነት፡ግን፡በግልፀ፡ታጠብቃለች። የእድገት፡ቴክኖሎጂንና፡መሠረታዊ፡ኢኮኖሚያችንን፡መገንቢያ፡የሚሆን፡ የኢንዱስትሪና፡የንግድ፡ካፒታልና፡ሎጂስቲክስ፡እቃዎችን፡በጥሩ፡ስምምነት፡ ለማስገኘት፡ትጥራለች፡ ዋና፡የእድገት፡መሣሪያዎችንና፡ የእርሻና፡ የሕክምና፡ቁሳቁስ፡እጥረት፡ያለበትን፡ ሁሉ፡ በቶሎ፡ ታሟላለች።

ሠ) እንዲሁም፡ የልዩ፡ ካቢኔውን፡ ሥራ፡ ለማሟላትና፡ ለማጠናከር፡ ልዩ፡ እንደራሴው፡ ተፈላጊውን፡ ሌሎች፡ መሥሪያ፡ ቤቶችን፡ ለማቋቋምና፡ ኃላፊዎችን፡ በመሾም፡ የሥራና፡ የኃላፊነታቸውን፡ አኳኋን፡ ለመወሰን፡ ሥልጣን፡ እንዲኖረው፡ በማለት፡ እንዲሁም፡ የሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ ድርጅቶችን፡ ሁሉ፡ በትጋት፡ እንዲቋቋሙ፡ በማሳሰብ፡ የተላለፈውን፡ የዘውድ፡ ምክር፡ ቤታችንን፡ ውሳኔ፡ ወደን፡ አጽድቀናል፡፡

ረ) ልዩ፡ ካቢኔው፡ የራሱን፡ የሥራ፡ አፈጻጸም፡ ደንብ፡ እንዲወስንና፡

ሰ) ልዩ፡ እንደራሴው፡ እንደራሴዎችን፡ አምባሳደሮችንና፡ ልዩ፡ መልእክተኞችን፡ እንዲመርጥና፡ እንዲሾም፡ ተመራጮቹንም፡ ለንጉሠ፡ ነገሥቱ፡ አቅርቦ፡ የሹመታቸውን፡ ሥነ፡ ሥርዓት፡ እንዲያስፈጽም፡ ከውጭ፡ በተጠሪነትና፡ በተወካይነት፡ የሚመጡትንም፡ ሁሉ፡ ተቀብሎ፡ ለንጉሠ፡ ነገሥቱ፡ እንዲያቀርብ፤

ሸ) ማንኛቸውንም፡ ሕግና፡ ለሕዝብ፡ የሚገለጥ፡ የልዩ፡ ካቢኔው፡ ውሳኔዎች፡ በልዩ፡ እንደራሴውና፡ ጉዳዩን፡ በሚመለከተው፡ ከፍተኛ፡ ባለሥልጣን፡ ኃላፊ፡ ተፈርሞ፡ እንዲወጣ፡ ብቻ፡ እንዲደረግ፡ በሙሉ፡ ድምጽ፡ ያለፈውን፡ የዘውድ፡ ምክር፡ ቤታችንን፡ ውሳኔዎች፡ ወደን፡ አጽድቀናል።

ቀ) ስለዚህም፡ ልዩ፡ ካቢኔው፡ ባስፈላጊና፡ ባመች፡ ሥፍራዎች፡ ሁሉ፡ የርዕሰ፡ ብሔሩን፡ ተጠሪ፡ እንደራሴዎችን፡ የልዩ፡ ካቢኔውን፡ ተወካይ፡ አምባሳደሮችና፡ ከፍተኛ፡ ባለሥልጣኖችን፡ የያዘ፡ ቀጥተኛ፡ ቆንሲላዎችን፡ ማለት፡ ቅርንጫፍ፡ ጽሕፈት፡ ቤቶችን፡ በሃገሩ፡ ነዋሪዎችና፡ ደጋፊዎች፡ በተገኘው፡ ግለሰብአዊ፡ ድርጅታዊና፡ መንግሥታዊ፡ የኅብረትና፡ የእርዳታ፡ ኃይል፡ ተሟልቶ፡ እንዲቋቋም፡ ያልተቆጠበ፡ ጥረት፡ በማድረግ፡ ከልዩ፡ካቢኔው፡ጋር፡ማንኛቸውንም፡ሥራ፡ በማስተባበር፡ ለዋናው፡ ዓላማ፡ ለኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ የነፃነት፡መብት፡መሸጋገሪያ፡ ለተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኞች፡ አንድነት፡የጦር፡ኃይል፡ ሕዝባዊ፡ ሠራዊታችን፡ ማንኛቸውንም፡ ዓይነት፡ሙሉ፡ ድጋፍና፡ እርዳታን፡ በማስገኘትና፡ በማስተባበር፡ ተገቢውን፡ የሞራል፡ የፖለቲካ፡ የዲፕሎማሲና፡ የቁሳቁስ፡ እርዳታና፡ ምንጮችን፡

በመሻት፡ በማስገኘትና፡ በማስከበር፡ ተጨባጭ፡ ኃይሎችን፡ ያደራጃል፡፡ የተቀደሰ፡ ዓላማችንንም፡ በከበሬታ፡ ያስተዋውቃል፡፡

በ) እንዲሁም፡ የንቅናቄአችን፡ "ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ በአንድነት፡" የኅብረት፡ ዓላማ፡ ደጋፊዎቻችንና፡ ረዳቶቻችን፡ የሆኑትን፡ ኢትዮጵያውያን፡ ወገኖቻችንን፡ ሁሉ፡ የሚያሰባስብ፡ አጠቃላይ፡ የሶሺያል፡ የባሕል፡ የሃይማኖት፡ የወጣቶችና፡ የስፖርት፡ ግንኙነትንና፡ ግልጋሎቶችን፡ የሚሰጡ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የሕዝብ፡ ድርጅቶችን፡ በኅብረታቸው፡ ኃይል፡ ተከፍተው፡ ለኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፡ የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ አንድነት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤታችን፡ ቅርንጫፍ፡ ምክር፡ ቤት፡ "አምዶች፡" በመሆን፡ የቦታ፡ ወይም፡ የቁጥር፡ መለያ፡ ተሰጥቷቸው፡ በመሰየም፡ የኢትዮጵያ፡ አንበሳ፡ አርማችንና፡ የጥንታዊት፡ ኢትዮጵያ፡ ሰንደቅ፡ ዓላማችን፡ ምልክት፡ ሆ ኗቸው፡እንዲደራጁና፡

ተከፍተው፡ እውነተኛ፡ ዲሞክራሲያዊና፡ ብሔረሰብአዊ፡ የኢትዮጵያን፡ አንድነት፡ የሚያበስር፡ የፖለቲካ፡ እምነታቸውን፡ በከበሬታ፡ ፊት፡ ለፊት፡ በማንፀባረቅ፡ በሕሊና፡ ነፃነታቸው፡ ካለአንዳች፡ ተጽዕኖ፡ ማንንም፡ ሳይፈሩ፡ እንዲሠሩ፡ በማድረግ፡ የብቸኝነት፡ ርዕዮተ፡ ዓለም፡ ጠባብ፡ ብሔረተኛ፡ አቋምንና፡ የአምባ፡ ገነናውያን፡ የጭቆና፡ ሥርዓት፡ ቅጥረኞችን፡ የተጽዕኖ፡ አጀንዳ፡ በማጋለጥና፡ በማከሸፍ፡ መተማመንና፡ መተሳሰብን፡ የሚፈጥሩ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ ባሓላዊና፡ ታሪካዊ፡ ሁኔታዎችንና፡ የኢትዮጵያውያንን፡ የአንድነት፡ መንፈስ፡ የወገኖቻችንን፡ ፍቅር፡ የሚያስተጋቡ፡ ነፃነታዊ፡ የሥራ፡ ተግባሮችንና፡ መልካም፡ አርዐያነትና፡ የጋራ፡ ብልጽግናን፡ እንዲያስገኙ፡ በማለት፡ ሙሉ፡ እምነት።

የኢትዮጵያውያን፡ የአንድነት፡ መንፈስ፡ እምነታችን፡ በባሕል፡ በሃይማኖትና፡ በቋንቋ፡ የተሳሰረ፡ መልካም፡ የብሔረሰባችን፡ የቤተሰብ፡ ግንኙነት፡ በሥራ፡ ግልጋሎት፡ በፍቅርና፡ በመተሳሰብ፡ እንዲፀናና፡ እንዲዳብር፡ ማንኛቸውንም፡ የበጐ፡ ሥራና፡ በእኩልነት፡ መብት፡ የሕዝባችን፡ የአንድነት፡ ግንኙነት፡ በነፃነታችን፡ የወንድምና፡ የእህትማማች፡ መንፈስ፡ ተሀድሶ፡ እንዲመሠረት፡ ለሃገራችንና፡ ለወገኖቻችን፡ አለኝታ፡

በምንም፡ ጊዜ፡ ተቆርቋሪ፡ ብቁና፡ ለጋሥ፡ ሆነን፡ በመገኘት፡ በሥራ፡ በመተጋገዝ፡ በፀሎታችንና፡ በይቅር፡ ባይነት፡ በአምላካችን፡ ፍቅር፡ በሃይማኖታችን፡ ፀንተን፡ እንድንቀራረብና፡ እንድንተሳሰብ፡ ያህል፡ ተገቢውን፡ ነፃነታዊ፡ መብት፡ በአንድነት፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የሕዝብ፡ ድርጅቶች፡ አቋም፡ በማጽደቅ፡ ተግተው፡ እንዲደራጁና፡ በሥርዓት፡ መቋቋማቸውን፡ እንዲያሳውቁን፡ በታላቅ፡ አክብሮት፡ እናሳስባለን፡፡

ተ) ከፀረ፡ ሃይማኖት፡ የክህደትና፡ የስውር፡ ተጽዕኖ፡ የጭቆናዎች፡ ሥርዓት፡ ነፃ፡ የነበረችውን፡ ጥንታዊት፡ የኢትዮጵያ፡ ኦርቶዶክስ፡ ተዋህዶ፡ ቤተ፡ ክርስቲያናችንን፡ በተቀደሰው፡ ቋሚ፡ የመንፈሳዊ፡ ሕግጋቷ፡ ከበሬታ፡ ሥርዓት፡ በሚያከራት፡ የመንፈሳዊ፡ ባሕሎችዋና፡ በዶመቁት፡ ክብረ፡ በዓሏ፡ በወግና፡ ማዕርግ፡ ተከብራና፡ ተደራጅታ፡ ሊቃውንቷና፡ ካህናችዋ፡ በመንፈሳዊ፡ የሰበካ፡ ጉባዔ፡ ነፃነታቸው፡ ተከብረው፡ ቤተ፡ ክርስቲያናችን፡ በቋሚና፡ በአንድ፡ ሕጋዊ፡ አመራር፡ ነፃ፡ የአስተዳደር፡ ደንቦች፡ ፀንታ፡ የሃያማኖታችንን፡ ትመህርት፡ ቅዳሴና፡ ውዳሴ፡ የነፃነት፡ ሥርዓትን፡ በከበሬታ፡ መልሶ፡ አቅሟንና፡ ኃይሏን፡ አደራጅቶ፡ ለመመሥረትና፡ ለማቋቋም፡

ያህል፡ ጠንክረን፡ በመደጋገፍ፡ ሊቃውንቶቻችን፡ መሠረታዊና፡ ነፃ፡ የነበረችውን፡ ጥንታዊት፡ የኢትዮጵያ፡ ኦርቶዶክስ፡ ተዋህዶ፡ ቤተ፡ ክርስቲያናችንን፡ ጠቅላላ፡ የመንፈሳዊ፡ ሰበካና፡ የቤተ፡ ክህነት፡ ነፃና፡ ብቁ፡ የአስተዳደር፡ ይዘት፡ በአንድ፡ ቋሚ፡ መመሪያ፡ በነፃነቷ፡ ልዕልና፡ የቅዳሴና፡ የፀሎት፡ ሙሉ፡ ሥርዓተ፡ ከበሬታዋ፡ እንድትጠበቅ፡ ያህል፡ የቅዱስ፡ ሲኖዶስ፡ ነፃ፡ ጉባዔ፡ በቅርቡ፡ ተጠርቶ፡ በአንድ፡ ቋሚና፡ እውቅ፡ በሆነ፡ አመራር፡ ጠንካራ፡ ሥርዓት፡ ለማጽናት፡ የተቀደሰ፡ ሥራውን፡ እንዲያካሄድ፡ የጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት፡ ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤታችንን፡ አዘናል፡፡

በእስልምናና፡በሌላም፡ ሃይማኖት፡ አማኖች፡ ኢትዮጵያውያን፡ ወገኖቻችንን፡ ሁሉ፡ በመረዳዳት፡ ነፃ፡ የሃይማኖት፡ እኩልነት፡ መብታቸውን፡ በአክብሮት፡ እንዲጠበቅ፡ ትይዩ፡ እኩልና፡ ተመጣጣኝ፡ እንክብካቤ፡ እንዲደረግ፡ ያህል፡ በጥብቅ፡ እያሳሰብን፡ በሃገራችን፡ ላይ፡ የመጣው፡ የሃይማኖት፡ ጥቃት፡ ፈሪሃ፡ እግዚአብሔር፡ ያደረባቸውን፡ አማኞች፡ ሁሉ፡ ስለሆነና፡ በኢትዮጵያ፡ አርበኞች፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ የኅብረት፡ ትግል፡ዓላማ፡ሁሉም፡አማኞች፡እኩል፡ የእንቅስቃሴው፡ ተካፋይ፡ የአንድ፡ኃይል ፡አካል፡ እንደመሆናቸው፡ በመገንዘብ፡በኢትዮጵያ ውያን እኩልነትና፡ ብርቱ፡ የአንድነት፡ ሕሊና፡ በሃይማኖታችን፡ ጠንካራ፡ የመንፈስ፡ ኃይል፡ ብርታት፡ ተቃቅፈን፡ እንሥራ፡፡

የኢትዮጵያን: ሕዝብ: የነፃነት: መብት: ለማስከበር: የኢትዮጵያችንን: አንድነት: በደሙ: የሚገነባ: በተለይ: በጦር: ሜዳ: የተፈተነ: ሃይማኖተኛ: ኢትዮጵያዊ: ወገኖቻችን: ሁሉ: በየትም: ቦታ: በእኩልነት: መከበር: አለባቸው:: የነፃዋ: ዲሞክራሲያዊት: ኢትዮጵያችን: እኩልና: አንድ: አካል: ናቸውና: በሀሰት: ፕሮፓጋንዳ: አትወናበዱ: ሃይማኖተኛ: ኢትዮጵያውያን: ሁሉ: ጠንክራችሁ: ተባበሩ:: በአምላካችን: ኃይል: በልጆቻችን: ፍቅርና: ደም: ኢትዮጵያችን: አትገነጣጠልም: ሃይማኖት: የግል: ሃገር: የጋራ: ነው::

ቸ) በብዙሃን፡ የሃገራችን፡ ባሕሎች፡ ሃይማኖቶች፡ ጐሣዎች፡ ቋንቋዎች፡ ለረጅም፡ ዘመን፡ በሰላም፡ ብሔረሰብአዊነት፡ በአንድነትና፡ በነፃነት፡ ታሪኳ፡ ተመሥርታ፡ እንደሚያምሩ፡ እቅፍ፡ አበባዎች፡ ደምቃ፡ የኖረችው፡ ኢትዮጵያ፡ እንዲሁም፡ የወደፊቱ፡ ነፃና፡ ዲሞክራሲያዊት፡ ኢትዮጵያችን፡ ለሕዝባችን፡ መሠረታዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፡ በተባበሩት፡ አርበኞችዋ፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ ሕዝባዊ፡ ሠራዊት፡ የኅብረት፡ ትግል፡ መስዋዕትና፡ ድል፡ ብዙሃን፡ የፖለቲካ፡ ፓርቲዎች፡ በነፃ፡ በመደራጀት፡ "በሕጋዊና፡ በሰላማዊ፡ ቋሚ፡ የእምነት፡ ጉርብትና፡ ከበሬታ፡" በኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ ዲሞክራሲያዊ፡ሸንጐ፡ እግዝዕና፡ ቀጥተኛ፡ የኢትዮጵያን፡ ሕዝብ፡ አስተዳደር፡የበላይ፡ ሃላፊዎቿን፡ በሕጋዊ፡ የሥልጣን፡ ሥርዓት፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ መንግሥቷን፡ ትመሠርታለች፡ በማለት፡ ሙሉ፡ እምነት፡ ለኢትዮጵያውን፡ ወገኖቻችን፡ ሁሉ፡ የምናሳስበው፡

ለተላቋ፡ ዲሞክራሲያዊት፡ ኢትዮጵያ፡ በነፃነቷ፡ መብት፡ ከበሬታ፡ በአንድነቷ፡ ፀንታ፡ በሰላም፡ የሕዝብ፡ መንግሥቷን፡ ለማቆም፡ የምትታገሉ፡ ድርጅቶችና፡ ኢትዮጵያውያን፡ ግለሰቦች፡ ሁሉ፡ የግል፡ ወይም፡ የኅብረት፡ የፖለቲካ፡ አቋምም፡ ሆነ፡ ማንናቸውንም፡ የሕዝብ፡ አስተዳደር፡ የፍልስፍናችሁን፡ ልዩነት፡

በኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ ንቃተ፡ ሕሊና፡ "ነፃ፡ ጠቅላላ፡ የሕዝብ፡ ምርጫ፡" ዳኝነት፡ ላይ፡ እምነታችሁን፡ በመጣል፡ በቅድሚያ፡ የነፃነቱን፡ መሠረታዊ፡ መብት፡ ለተነፈገው፡ ሕዝባችንና፡ በዳግማዊ፡ ፋሽስት፡ የጭቆና፡ ኃይልና፡ በብቸኝነት፡ በግዴታና፡ በግድያ፡ ርዕዮተ፡ ዓለም፡ በፀረ፡ ሃይማኖት፡ ትምክህተኝነትና፡ በከሠረ፡ የኢኮኖሚ፡ ይዘት፡ በረሃብ፡ አለንጋ፡ ለሚሠቃየው፡ ወገናችንና፡ በተለይም፡ ለሚሰዉት፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኖቻችን፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ ሕዝባዊ፡ ሠራዊት፡ በኅብረት፡ ተግተንና፡ ተባብረን፡ እንድረስለት፡፡

በተለይ፡ ለዚሁ፡ ተግባር፡ ለሚውሉት፡ ቆንሲላዎችና፡ በልዩ፡ ካቢኔአችን፡ ግንባር፡ ቀደም፡ አስተባባሪነት፡ በኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ "ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ በአንድነት"፡ አቋም፡ የጠቅላይ፡ምክር፡ቤት፡አምዶቻችሁን፡ እያቆማችሁ፡ድጋፋችሁንና፡ የተቀደሰውን፡ ኢትዮጵያዊ፡ ተግባሮቻችሁን፡ እንድታስተባብሩ፡ በልጆቻችን፡ ፍቅርና፡ የደም፡ መስዋዕትነት፡ በዲሞክራሲያዊት፡ ኢትዮጵያ፡ ስም፡ በገናናው፡ የታሪካችን፡ ከበሬታ፡ ሥርዓት፡ የኅብረት፡ መስዋዕታችሁን፡ እንድትፈጽሙ፡ የአክብሮት፡ ጥሪያችን፡ ለወገኖቻችን፡ ኢትዮጵያውያን፡ ሁሉ፡ ይድረሳችሁ፡፡

ግርማዊ ቀዳማዊ አምሃ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

ለኢትዮጵያ ኅብረተ ብሔር (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ የዘውድ መንግሥት

የበላይ ጠባቂ



ግርማዊ ቀዳማዊ አምሃ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

ለኢትዮጵያ ኅብረተ ብሔር (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ የዘውድ መንግሥት

የበላይ ጠባቂ

፬ና፡ ለኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ መሠረታዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ ዲሞክራሲያዊ፡ ልዕልና፡ በተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኞች፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ ሕዝባዊ፡ ሠራዊት፡ ኅብረት፡ የነፃነት፡ ትግሉ፡ በመላው፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ተሳትፎ፡ በሰፊው፡ በሃገራችን፡ ውስጥ፡ ሁሉ፡ ተደራጅቶ፡ እንዲዛመት፡ ለማድረግ፤

ሀ) የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፡ ሕዝባዊ፡ ሠራዊታችን፡
"የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኞች፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡" በማህፀረ፡ ቃል፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኞች፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ በመፈክረ፡ ቃል፡ "አንድነት፡" ተብሎ፡ በመጠራት፡ በልዩ፡ ካቢኔአችን፡ ሥር፡ በጠቅላይ፡ የጦር፡ ኃይል፡ መምሪያ፡ ትዕዛዝ፡ በሙሉ፡ ሥርዓት፡ ተደራጅቶ፡ እንዲቋቋምና፡

ለ) በሃገራችንም፡ ውስጥ፡ የ"አንድነት፡" የጦር፡ ኃይል፡ አምዶችም፡ በአንድ፡ የጦር፡ መመሪያ፡ ትዕዛዝ፡ እንዲተዳደሩና፡ እንደሁኔታው፡ አስፈላጊነት፡ ተገቢውን፡ የጦር፡ ስልት፡ በማስተባበር፡ የተቀደሰ፡ ተግባራቸውን፡ እንዲፈጽሙ፡ የዘውድ፡

ምክር: ቤታችን: እንድናጸድቅ: ያቀረበልንን: ታላቅ: ውስኔዎች:ሁሉ: በተባበሩት: የኢትዮጵያ: አርበኞች: አንድነት: በገናናው: የጦር: ኃይላችን: አኩሪ: ጥንታዊ: ታሪካችን: ከበሬታ: ስም: ጸድቆ: እንዲሠራበት: ወደን: ፈቅደናል::

ሐ) እንዲሁም: በታላቋ: ጥንታዊት: ኢትዮጵያ: ገናናው: የጦር: ኃይላችን: ታሪክ: መሠረት: የክብር: ኮከብ: ምልክታችን: የነበረውን: የቅዱስ: ጊዮርጊስ: አርማችንን: ፈቅደን: በመስጠት: ለጠቅላይ: የጦር: ኃይል: መምሪያና: ለተባበሩት: የኢትዮጵያ: አርበኞች: አንድነት: የጦር: ኃይል: እንዲሁም: ለአንድነት: አምዶች: ሁሉ: መለያቸው: አርማና: የሰንደቅ: ዓላማቸው: ሆኖ: እንዲሠራበት: በከበሬታ: ፈቅደን: አዘናል::

መ) በልዩ: ካቢኔው: ጠቅላይ: የጦር: ኃይል: መምሪያችን: የበላይነት: መሠረታዊው: እቅድና: ፕሮግራም: በትብብር: እንዲቀናበር: የሚያስችሉትን: ሙሉ: የትግሎቹን: ንቅናቄዎችና: የውህደት: እርምጃዎች: ሁሉ: ከዘውድ: ምክር: ቤታችን:ርዕሰ: መማክርትና: ከተባበሩት: የኢትዮጵያ: አርበኞች: አንድነት:የጦር:ኃይል:ተጠሪዎቻችን:ጋር:በኅብረት: ይቀይሳል::

እንዲሁም፡ የጦር፡ ኃይል፡ መምሪያችን፡ ተገቢውን፡ ዝግጅት፡ የጦር፡ አቅድ፡ ትምህርቶችንና፡ የጦር፡ ጣቢያዎችን፡ በአጠቃላይ፡ በበላይ፡ ተቆጣጣሪና፡ ኃላፊነቱ፡ መሠረት፡ የጦር፡ ኃይሉን፡ የሙሉ፡ ትጥቅና፡ የሎጂስቲክስ፡ ብቃት፡ ያስተባብራል። ሌሎችንም፡ ሙሉ፡ የጦር፡ ኃይል፡ ምስጢራዊ፡ ዝግጅቶችንና፡ ተግባሮችን፡ ይመራል። እንዲሁም፡ የ"አንድነት፡" ሙሉ፡ የሥራ፡ ተግባሮችና፡ ዲሲፕሊኖችን፡ በጠቅላይ፡ የጦር፡ ኃይል፡ መምሪያና፡ ልዩ፡ ካቢኔ፡ ኃላፊነት፡ በምስጢራዊ፡ ስትራተጂ፡ ያቀናብራል።

ሠ) ስለዚህም፡ ከዚህ፡ አዋጅ፡ ግዜ፡ ጀምሮ፡ ከእንግዲህ፡ ወዲህ፡ በማንኛቸውም፡ ሥፍራ፡ የምንገኝ፡ የኢትዮጵያውያን፡ ዜጋ፡ የሆንን፡ ሁሉ፡ በኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ የነፃነት፡ መብት፡ ልዕልና፡ በከሬታ፡ ተመሥርተን፡ በዲሞክራሲያዊ፡ የሕዝብ፡ ሸንጐ፡ እግዝዕና፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡መንግሥታችንን፡እስከ፡አቆምንና፡ እስከ፡ አፀናን፡ ድረስ፡ እያንዳንዳችን፡ የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኞች፡ "አንደነት፡"የጦር፡ኃይል፡ ሕዝባዊ፡ ሠራዊት፡ ባልደረቦች፡ ነን።

ለዚህም፡ ታላቅ፡ መሥዋዕትነትና፡ ታላቅ፡ ኃላፊነት፡ የተቀደሰ፡ ብሔራዊ፡ ጥሪያችንን፡ አሟልተን፡ ግዳጃችንን፡ ለመፈጸም፡ እንበቃ፡ ዘንድ፡ ጤንነታችንን፡ በመጠበቅና፡ ሰውነታችንን፡ በማጠናከር፡ በጦር፡ ስልትና፡ በሃገር፡ ግንባታ፡ ጥበብ፡ ሁሉ፡ ሰልጥነንና፡ ተክነን፡ ከዛሬ፡ ጀምሮ፡ ሁላችንም፡ ዝግጁና፡ ብቁ፡ ሆነን፡ የ"አንድነት፡" የጦር፡ ኃይል፡ ባልደረባ፡ ለመባል፡ በቆራጥነት፡ ተሰናድተን፡ መገኘት፡ ይገባናል፡፡

ይህም፡ ስትራተጂካዊ፡ መመሪያ፡ የጦር፡ ኃይላችንን፡ ባልደረቦች፡ ሁሉ፡ ሕዝባዊነታቸውን፡ በማረጋገጥ፡ ጠንካራ፡ የጥንት፡ ባሕላችንን፡ የጦር፡ ኃይል፡ ስሪት በሕዝቡ፡ ድጋፍ፡ በመመሥረት፡ የአምባ፡ ገነናዊያን፡ የዲክታተሮች፡ የጭቆናና፡ ሕገ፡ ወጥ፡ ሥርዓት፡ የሚሊቴር፡ ሞኖፖልን፡ በመስበር፡ የተጠለፈችውን፡ የሕዝባችንን፡ የተቀደሰች፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነታችን፡ "መብት፡" በሕዝባችን፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ ሕዝባዊ፡ሠራዊት፡ለማዳንና፡ለመጪውም፡ ትውልዳችን፡ በሰላም፡ ካለ፡ማንም፡ ቅጥረኞች፡ ጣልቃ፡ ገብነትና፡ ድፍረት፡ የሕዝባችን፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ ልዕልና በአንድነታችን፡ ዘለዓለማዊ፡ ሆና፡ ለመጽናት፡ ያበቃናል፡ በማለት፡ በሕዝባችን፡ የአንድነት፡የጦር፡ኃይል፡ የሕዝባዊ፡ ሠራዊት፡ እንተማመናለን፡፡

በዚህም፡ የጦር፡ ኃይላችን፡ ሕዝባዊነት፡ ሥርዓት፡ ጥቂት፡ አምባ፡ ገነናዊ፡ ባለጠበንጃዎችና፡ ግራም፡ ሆነ፡ ቀኝ፡ ክንፍ፡ የብቸኝነት፡ ሂደት፡ አክራሪዎችም፡ ሆነ፡ ጠባብ፡ ብሔረተኞች፡ የኢትዮጵያን፡ አርባ፡ ሚሊዮን፡ ሕዝብ፡ የነፃነቱን፡ መብት፡ ዲሞክራሲያዊ፡ ልዕልና፡ ባፈሙዝ፡ ኃይል፡ አያፍኑትም። በጦር፡ ኃይላችን፡ ሕዝባዊነት፡ ሥርዓት፡ ወታደሩና፡ የሲቪሉ፡ ሠራዊት፡ የታጠቀና፡ ፅኑ፡ አንድ፡ አካል፡ ሆኖ፡ ለሰላም፡ ኑሮው፡ ግንባታና፡ ለአንድነቱ፡ የጋራ፡ መከታ፡ ደጀን፡ ሆኗት፡ በኅብረት፡ በመቆም፡ በነፃነቱና፡ በዲሞክራሲያዊ፡ ኃይሉ፡ የትውልዱን፡ የረጅም፡ ግዜ፡ ቋሚ፡ የጋራ፡ ጥቅምና፡ ብልጽግና፡ ለማስገኘት፡ ያስተማምናል።

ማንኛቸውንም፡ የሃገራችንን፡ ድንበር፡ የአንድነቷን፡ እግዝዕና፡ በቀውጢ፡ የሃገራችን፡ የችግር፡ ግዜያትና፡ ሁኔታ፡ በማንኛቸውም፡ ምክንያት፡ ለመጠቀም፡ የሚዳፈር፡ ሁሉ፡ የማይቀርና፡ የማያዳግም፡ የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኞች፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ ሕዝባዊ፡ ሠራዊት፡ መልሱን፡ አጸፋውን፡ ይሰጣል። ግዜው፡ ቢያልፍም፡ የመጪው፡ የኢትዮጵያ፡ ትውልዳችን፡ ብድሩን፡ ከነወለዱ፡ ለመመለስ፡ በደሙ፡ ይሠዋል።

የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኞች፡ የጦር፡ ኃይል፡ ሕዝባዊ፡ ሠራዊት፡ መፈክር፡ "አንድነት"፡ የኀብረተ፡ ብሔራችን፡ ዲሞክራሲያዊ፡ ዓላማ፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ የነፃነት፡ "መብት"፡ የተባለውም፡ ለዚህ፡ ነው፡፡ የኢትዮጵያ፡ ነፃነታዊ፡ ድል፡ በተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኞች፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ ሕዝባዊ፡ሠራዊት፡ቆራጥ፡ የትግል መስዋዕት፡ የተረጋገጠ፡ ነው፡፡

በተቀዳሚም፡ የተባበሩትን፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኞች፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ ሕዝባዊ፡ ሠራዊት፡ መመሪያንና፡ "የአንድነት፡" ድጋፍ፡ ጥሪን፡ አስተባብር፡፡

ተመልከት፡ ዓላማህን፡ ተከተል፡ አለቃህን!

ኃይል፡ በክብር!

ነፃነታዊ፡ መብት፡ በአንድነት!

ኢትዮጵያችን፡ በነፃነቷ፡ መብት፡ በዲሞክራሲያዊ፡ ልዕልና፡

በአንድነቷ፡ ለዘለዓለም፡ ትኑር!

ግርማዊ፡ ቀዳማዊ፡ አምሃ፡ ሥላሴ፡

ሞዓ፡ አንበሳ፡ ዘእምነገደ፡ ይሁዳ፡

ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ዘኢትዮጵያ፡፡

የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኞች፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡

ሕዝባዊ፡ ሠራዊት፡ ጠቅላይ፡ የጦር፡ አዛዥ፡፡

ፉኖ፡ የሚያስፈልገውን፡ ማንኛቸውንም፡ ተገቢ፡ እርዳታና፡ እንዲሁም፡ የሞራል፡ የፖለቲካ፡ የዲፕሎማሲ፡ የቁሳቁስና፡ በማንኛቸውም፡ መስኮች፡ ለሚገኘውና፡ ለሚደረገው፡ የትግል፡ አንድነት፡ ድጋፍን፡ በማጠናከር፡

ሀ) ልዩ፡ ካቢኔአችን፡ በሥርዓት፡ ይህን፡ ተቀዳሚ፡ ተግባር፡ ለኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ አንድነትና፡ የነፃነቱን፡ መብት፡ ለማስከበር፡ በሚያደርገው፡ ትግሎች፡ አመራር፡ ሁሉ፡ ለአርበኞቻችን፡ የትግል፡ ማስተዳደሪያና፡ለሥራ፡ ማስካሄጃ፡ በጀት፡ የሚሆኑትን፡ የገንዘብ፡ ኃይልና፡ ማንኛቸውንም፡ ተንቀሳቃሽ፡ ቁሳቁስ፡ (ማቲሪያሎች) በሙሉ፡ እንዲያስገኙና፡ እንዲያሰባስብ፡ በማለት፡ ልዩ፡ ካቢኔው፡ ከወዳጅ፡ ሃገር፡ መንግሥታትና፡ ድርጅቶች፡ በተለይም፡ ለኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነቱ፡ መብት፡ ለኢትዮጵያ፡ አንድነትና፡ ክብር፡ ከሚቆረቆሩት፡ የ"መብት"ና፡ የ"አንድነት"፡ አባሎችም፡ ሆነ፡ ሌሎችም፡ ደጋፊ፡ ግለሰቦች፡ ብሔረሰቦችና፡ ማኅበራዊ፡ ድርጅቶች፡ በሙሉ፡ ቀጥተኛ፡ ግንኙነታቸውን፡ በመዘርጋት፡ በመገናኘትና፡ በማስገኘት፡ ማንኛቸውም፡ እርዳታና፡ መዋጮ፡ ሁሉ፡ በማሰባሰብ፡

ግርማዊ ቀዳማዊ አምሃ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

ለኢትዮጵያ ኅብረተ ብሔር (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ የዘውድ መንግሥት

የበላይ ጠባቂ

አንድነት

መብት

RIGHT

SOLIDARITY

Liberty In Our Nation

POWER – WITH – HONOUR

ለ) እንዲሁም፡ የኢትዮጵያን፡ ነፃነታዊ፡ አንድነትና፡ ዘላቂ፡ ብሔራዊ፡ የእኩልነትና፡ የጋራ፡ እድገት፡ ጥቅምን፡ የሚዳብሩበትንና፡ በተለይም፡ ለማንኛቸውም፡ የጦር፡ የተፈጥሮ፡ አደጋና፡ የስትራተጂክ፡ ችግር፡ የሚቋቋሙበትን፡ ማንኛቸውንም፡ ዓይነት፡ እርዳታ፡ ሳያቋርጥ፡ ያስገኛል፡ ይሰበስባል፡፡

ሐ) የተገኘውንና፡ የሚገኘውን፡ ማንኛቸውንም፡ ዓይነቶች፡ ቀጥተኛ፡ የንቅናቄው፡ ማስካሄጃ፡ በጀትና፡ እርዳታዎች፡ በተቀዳሚ፡ ለተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኞች፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ እንቅስቃሴ፡ ተግባርና፡ ለመንግሥት፡ ኑባሬዎቹ፡ የሥራ፡ ማስካሄጃ፡ ልዩ፡ ካቢኔው፡ ባወጣው፡ የበጀት፡ መተዳደሪያና፡ የኃላፊነት፡ ተግባር፡ የጦር፡ መመሪያ፡ ፖሊሲ፡ መሠረት፡ ለተመደቡበት፡ ጉዳይ፡ ብቻ፡ በሥርዓት፡ እንዲውሉና፡ በትክክል፡ እንዲወጣ፡ የማድረጉ፡ ኃላፊነት፡ በልዩ ካቢኔው፡ ጉዳዩን፡ የሚመለከተው፡ ክፍል፡ አባልና፡ ጠቅላላ፡ የንብረት፡ ተቆጣጣሪው፡ ዋና፡ ኦዲተር፡ የጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤቱ፡ ባልደረባ፡ እንደመሆኑ፡ መጠን፡ ለዚሁ፡ የሚያበቁትን፡ ሕጋዊ፡ የጦር፡ውስጣዊ፡መመሪያና፡ የኃላፊነት፡ ሥርዓት፡ ልዩ፡ ካቢኔው፡

አሟልቶ፡ በማደራጀት፡ ከጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤታችን፡ የጠቅላይ፡ ኦዲተር፡ ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡ ጋር፡ በማስተባበር፡ እንዲሠራበት፡ የዘውድ፡ ምክር፡ ቤታችን፡ ያስተላለፈውን፡ ጠቅላላ፡ ውሳኔ፡ በማጽደቅ፡ ከጥብቅ፡ አደራ፡ ጭምር፡ በከበሬታ፡ አዘናል፡፡

መ) በተጨማሪም፡ የውስጣዊ፡ የሂሳብ፡ ኦዲተሩ፡ የግምጃ፡ ቤቱን፡ የወጪና፡ የገቢ፡ ሠነድ፡ በማየትና፡ በመመርመር፡ ትክክለኛነቱንና፡ ጠቅላይ፡ መምሪያ፡ የሰጠውን፡ ዓላማና፡ ተግባር፡ የተከተለ፡ መሆኑን፡ በጠቅላላ፡ ሪፖርት፡ በተወሰነ፡ ግዜ፡ በጽሑፍ፡ ለዋናው፡ የጠቅላይ፡ ኦዲተር፡ ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡ በማቅረብ፡ ከተመሳከረና፡ ልዩ፡ ካቢኔው፡ አይቶት፡ ከተቀበሉት፡ በኋላ፡ በጠቅላይ፡ የጦር፡ ኃይል፡ አዛዡ፡ ጸድቆ፡ መዝገብ፡ እንዲይዝ፡ ይሆን፡ ዘንድ፡ እንዲሁም፡ የውስጣዊው፡ የሂሳብ፡ ኦዲተር፡ ሪፖርት፡ ሠነድ፡ ለተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኞች፡አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ ልዩ፡ ተወካይ፡ ባልደረቦች፡ ማለት፡ አማኞች፡ ምስጢሩ፡ የተጠበቀ፡ ሆኖ፡ እንዲያውቁትና፡ እንዲረዱት፡ እንዲሆን፡ በጥብቅ፡ ስናዝ፡ አጠቃላይ፡ የጠቅላይ፡ ኦዲተሩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡ ሪፖርቶች፡ በጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤቱ፡ አማካኝ፡ በጠቅላላ፡ ዓመታዊ፡ ጉባዔ፡ እንዲጸድቅ፡ ይቀርባል፡፡

ሠ) እንዲሁም፡ እስከዛሬ፡ ድረስም፡ ሆነ፡ ለወደፊቱ፡ በልዩ፡ ካቢኔአችን፡ አስተባባሪነት፡ በኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ የነፃነት፡ ትግል፡ ስም፡ በ"መብት"ና፡ በ"አንድነት"፡ አምዶች፡ አማካኝ፡ ለሚሰበሰበውና፡ ለሚዋጣው፡ ማንኛቸውም፡ ዓይነት፡ እርዳታና፡ የሕዝብ፡ መዋጮ፡ በየአምዶቻችን፡ በሥርዓትና፡ በትክክል፡ የደረሰኝ፡ ሂሳብ፡ ሠነድ፡ (የኦፊሴል፡ሠነዶች፡) በመለየት፡ ተመዝግበው፡ የገቢው፡ ምንጮችና፡ ዓይነቶች፡ ያስገኘውን፡ ክፍል፡ እንደአስፈላጊነቱ፡ የኮድ፡ ወይም፡ ግልጥ፡ ስም፡ ዝርዝር፡ እንደረዳቶቻችን፡ ፍላጎት፡ በትይዩ፡ ታክሎበት፡ የጠቅላላ፡ ዓመታዊ፡ የወጪና፡ የገቢ፡ ዝርዝር፡ ሠነድ፡ ሪፖርት፡ ላይ፡ በመሥፈር፡ በሥርዓት፡ ለሚጠይቁት፡ አግባኦ፡ ያላቸው፡ ረዳቶቻችንና፡ ለሚመለከታቸው፡ የንቅናቄያችን፡ ተቆጣጣሪ፡ የግምጃ፡ቤት፡አባሎች፡ ክፍልና፡ ወኪሎች፡ ምስጢሩ፡ የተጠበቀ፡ ሆኖ፡ ምን፡ ሥራ፡ ላይ፡ የዋለ፡ መሆኑንም፡ የሚያስረዳ፡ የሂሳብ፡መዝገቡን፡እንዲመለከቱት፡ በተጨማሪ፡ ውሳኔ፡አዘናል፡፡

ጉልበታችንም፡ ኃይላችንም፡ አንተው፡ ባለቤቱ፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ነህና፡ የሃገሬ፡ ጐበዝ፡ በተመቸህ፡ አንፃር፡ ሁሉ፡ ተረዳድተህ፡ ጉልበትህንና፡ እርዳታህን፡ በሥርዓት፡ በማከማቸት፡ ለተቀደሰው፡ የትግላችን፡ ድጋፍ፡ እጆችህ፡ ይዘርጉ፡፡

በኅብረታችን፡ኃይል፡እራሳችንን፡በራሳችን፡ መቻል፡ ተቀዳሚ፡ የትግላችን፡ ነፃነታዊ፡ መብት፡ ቋሚ፡ ዓላማችንና፡ የተረጋገጠ፡ ጽኑ፡ መተማመኛችን፡ ስለሆነ፡ ዘላቂውን፡ የኢትዮጵያችንን፡ ጥቅም፡ ካለዲሞክራሲያዊ፡ የሕዝባችን፡ ሸንጎ፡ ውሳኔ፡ እግዝዕና፡ በስተቀር፡በምንም፡ሁኔታና፡ጊዜ፡በማንም፡ የባዕድ፡ስውር፡ ወይም፡ የግል፡ጥቅም፡ አይወሰንም፡ በማለት፡ በቅድሚያ፡ የእምነታችንን፡ መሠረት፡ በግልጽ፡ ልናረጋግጥ፡ እንወዳለን፡፡

፪) ከንቅናቄያችን፡ ውጪ፡ በኢትዮጵያ፡ ንጉሠ፡ ነገሥትና፡ በዘውድ፡ ስማችንም፡ ሆነ፡ በልዩ ካቢኔአችን፡ ስም፡ በኢትዮጵያ፡ ብሶትና፡ የነፃነትዋ፡ ትግል፡ ስም፡ ለመደለልና፡ ለመነገድ፡ የሚሠነዘሩትን፡ ሃሰተኛና፡ ስም፡ አሳሳች፡ የግል፡ ጥቅምና፡ የወንበዴዎች፡ አድማ፡ ተግባሮች፡ ሁሉ፡ ሕገ፡ ወጥነታቸው፡ ታውቆ፡ ከትትሉ፡ ለሚመለከተው፡ የቅርንጫፍ፡ አባሎቻችን፡ ክፍል፡ እንዲታወቅና፡ እንዲጋለጥ፡ ከመሆኑም፡ በላይ፡ ለአምዶቻችን፡ የዲሲፕሊንና፡ ለሕግ፡ አስከባሪዎቻችን፡ ምርመራ፡ ክፍል፡ ተገቢው፡ ሕጋዊ፡ ክትትልና፡ እርምጃ፡ እንዲወሰድ፡ ይታዘዝ፡ ዘንድ፡ ያስተላለፈልንን፡ የዘውድ፡ ምክር፡ ቤታችን፡ ውስኔ፡ በአክብሮት፡ ወዶን፡ ስናጸድቅ፤

ስለዚህም፣ የውስጥ፡ አስተዳደር፡ የሥርዓትና፡ የዲሲፕሊን፡ ጥበቃ፡ "የጥቁር፡ አንበሳ፡" ሕግ፡ አስተናባሪዎች፡ ልዩ፡ የቴክኒክ፡ አምድ፡ ክፍል፣ በጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤታችን፡ ቀጥተኛ፡ ቁጥጥር፡ ሥርዓት፡ ተቋቁመው፡ ለንቅናቄያችን፡ የሰላምና፡ የደህንነት፡ ሐዋርያ፡ በመሆን፣ ለ"መብት"ና፡ ለ"አንድነት"፡ አምዶች፡ ሕጋዊ፡ ግልጋሎት፡ የጦር፡ ኃይላችን፡ የክብር፡ ኮከብ፡ በመሆን፡ እንዲሠሩ፡ በጥብቅ፡ አዘናል፡፡

ኟኛ፡ በኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ በደረሰበት፡ ከፍተኛ፡ የጦርና፡ በጣም፡ የሚያሰቅቀው፡ የተደጋገመ፡ የረሃብና፡ የድርቀት፡ አደጋ፡ ከመሠረቱ፡ ሁኔታው፡ ሳይሻሻል፡ በተጨማሪ፡ አስከፊ፡ የግፍና፡ የጭቆና፡ ጭፍን፡ የኮሚኒስት፡ ኢምፔሪያሊስት፡ አምባ፡ ገነናዊ፡ የከሠረ፡ የሰሻል፡ የኢኮኖሚና፡ የግዴታ፡ ሥሪት፡ ይዘት፡ ችግሩን፡ በትምክህተኝነት፡ ይሉኝታ፡ በሌለው፡ ጉበኝነትና፡ ማናአለኝህነት፡ ስላባባሱት፡ ረሃቡ፡ ጋብ፡ ሳይልለት፡ ከትውልድ፡ ሃገሩ፡ ካለውዴታው፡ በተንኰል፡ የሠፈራ፡ የሚባል፡ የፖለቲካ፡ ቁጥጥር፡ ስውር፡ ፕሮግራም፡ በግፍ፡ የተፈናቀለውና፡ በየውጭ፡ ሃገሩ፡ የተሰደደው፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ቁጥር፡ ብዛት፡ በየግዜው፡ እየባሰና፡ እየጨመረ፡ ከአፍሪካ፡ ምናልባትም፡ ከዓለም፡ ታዳጊ፡ መንግሥታት፡ ውስጥ፡ በድህነትም፡ ጭምር፡ አንደኛውን፡ ደረጃ፡ ይዞ፡ ይገኛል፡፡

እንኳን፡ ላልተራበው፡ በኢኮኖሚው፡ አመራር፡ ጭራሽ፡ ውድቀት፡ የተነሳ፡ በብዛት፡ ለደኸየውና፡ ለተራበው፡ ሠራተኛ፡ ሰላማዊ፡ ሕዝባችን፡ ያልሆነ፡ እንኳን፡ ለሥራ፡ አጡ፡ ካለዕድሜው፡ ተገዶ፡ በጡረታ፡ የባከነው፡ እንኳን፡ በሽተኛው፡ ጤነኛው፡ በጭንቀት፡ ዕረፍትና፡ ጤና፡ ያጣው፡ ኮብልሉ፡ በበረሃ፡ የቀረው፡ ከሞቀ፡ ቤቱ፡ ተሰዶ፡ በጐረቤት፡ ሃገሮች፡ ሥራና፡ ጠለላ፡ እያጣ፡ የውርደት፡ ማቅ፡ ለብሶ፡ ለሚንገላታው፡

በማያቋርጥ፡ የጦር፡ አለንጋ፡ በቀበሮ፡ ጉድጓድና፡ አካለ፡ ጐደሎ፡ ሆኖ፡ ለቀረው፡ ጀግና የፈረደበት፡ ጐበዝ፡ ወገናችን፡ በሙሉ፡ የሚቻለውንና፡ የሚያስፈልገውን፡ ማንኛቸውንም፡ ዓይነት፡ እርዳታ፡ ሳይቋረጥ፡ ለማድረግና፡ ሕዝባችን፡ ራሱን፡ በራሱ፡ ለመቻል፡ የሚያበቃውን፡ ስትራተጂክ፡ እርምጃዎች፡ ለመፈጸም፡

ሀ) ልዩ፡ ካቢኔአችን፡ በቀጥታና፡ በቅርንጫፍ፡ ድርጅቶቻችን፡ አማካኝ፡ በተለይም፡ በ"አንድነት፡" የጦር፡ ኃይላችን፡ የአምድ፡ ሕዋሳት፡ ድርጅቶች፡ ተገቢውን፡ ሰብአዊ፡ እርዳታ፡ እያደራጀ፡ በጦርና፡ በረሃብ፡ የተፈናቀሉትን፡ ወገኖቻችን፡ በሙሉ፡ እንዲረዱ፡ ይጥርበታል፡፡ የውድ፡ ሃገራችንም፡ ሕዝብ፡ ስቃይ፡ በቶሎ፡ መፍትሄውን፡ እንዲያገኝ፡ ይሠዋል፡፡

ለዚሁም፡ ተቀዳሚ፡ የሰብአዊ፡ መብት፡ ጉዳይ፡ ልዩ፡ የእርዳታ፡ ምንጮች፡ በአንድ፡ ራሱን፡ የቻለ፡ ጠቅላይ፡ የበጐ፡ አድራጐት፡ ነፃ፡ አካል፡ ድርጅት፡ መመሪያ፡ በ"ታቀፍ፡" "አ" "የኢትዮጵያ፡ ልጆች፡ ድርጅት፡" ፋውንዴሽን፡ ስም፡ በልዩ፡ እንደራሴው፡ የበላይና፡ ዋና፡ ኃላፊነት፡ ተቀናብረው፡የእርዳታ፡ ምንጭ፡ ከሆኑት፡ በዋና፡ ዋናዎቹ፡ የውጭ፡ ሃገሮች፡ ውስጥ፡ በከፍተኛ፡ ደረጃ፡ በሕግ፡ ተመዝግበው፡ በመብት፡ ጠቅላይ፡

ምክር፡ ቤታችን፡ ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡ አማካኝ፡ በየአምድ፡ ቅርንጫፍ፡ ጣቢያዎቻችን፡ ሁሉ፡ በተጨማሪ፡ ተደራጅተው፡ እንዲከፈቱና፡ ሥራው፡ በተቀላጠፈ፡ አመራር፡ ሁኔታ፡ በወዳጆቻችንና፡ በፍቃደኞች፡ የኢትዮጵያ፡ ልጆች፡ ትጋትና፡ የተቀደሰ፡ የበጐ፡ ሥራ፡ መስዋዕትነት፡ በኅብረት፡ በመሳተፍ፡ ብቁ፡ መስተዋጽዖ፡ ለማስገኘት፡ በከበሬታ፡ በማሳሰብ፡ የሰበአዊ፡ ድርጅቱ፡ አካል፡ ነፃ፡ ኦዲተሩ፡ ተገቢውን፡ የሂሳብ፡ ቁጥጥርና፡ ዓመታዊ፡ ሪፖርቱን፡ በተለየ፡ ሰነድ፡ ለድርጅቱ፡ ፋውንዴሽንና፡ ለጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤቱ፡ ልዩ፡ ተቆጣጣሪ፡ ወኪል፡ እንዲያቀርብ፡ አዘናል፡፡

ለ) በዚህም፡ አሳሳቢና፡ አጣዳፊ፡ ጉዳይ፡ በየውጭ፡ ሃገሩ፡ በስደት፡ ከሚኖሩት፡ ወገኖቻችንና፡ በዓላማችን፡ ተመሳሳይ፡ ሰብአዊ፡ የስደተኞች፡ ማኅበሮችም፡ ጋር፡ የማያቋርጥ፡ ግንኙነት፡ በማድረግ፡ ቋሚ፡ መፍትሔ፡ የሚገኝበትን፡ ስልትና፡ ለግዜውም፡ የሚረዱበትን፡ መንገድ፡ በቅርብ፡ እያጠና፡ የተቻለውን፡ ምክርና፡ እርዳታ፡ በመለዋወጥ፡ የእርዳታ፡ መምሪያውን፡ በቅድሚያ፡ በጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤታችን፡ ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡ አስተባባሪነት፡ እየተቀናበረ፡ ቋሚና፡ ዘላቂ፡

መፍትሔው፡ ግን፡ በአንድነት፡ የጦር፡ ኃይላችን፡ ልዩ፡ የሰብአዊ፡ መብት፡ የሕዝብ፡ ድርጅት፡ ክፍል፡ በየአምዶቹ፡ እንዲቀናበሩ፡ ይደረጋል፡፡ በሃገር፡ ቤታችንም፡ መሣሪያቸውን፡ አውርደው፡ የሚንገላቱትን፡ የኢትዮጵያ፡ የጦር፡ ኃይል፡ ባልደረቦችንም፡ አሰባስቦ፡ እንደፍቃዳቸው፡ መሠረት፡ ወደ፡ ቀናው፡ የተቀደሰ፡ አንድነት፡ የትግላችን፡ ሕዝባዊ፡ ሠራዊት፡ አምድ፡ ይመራል፡፡

ስለዚህም፡ ማንኛችንም፡ ኢትዮጵያውያን፡ ስደተኞች፡ በሚደርስብን፡ የቤተሰብና፡ የሥራ፡ ችግር፡ በሚገጥመን፡ የኑሮ፡ ጉስቁልና፡ የመንፈስና፡ የናፍቆት፡ ጭንቀት፡ ሁሉ፡ ለተረፉት፡ ትውልዶቻችን፡በውድ፡ ሃገራችን፡ በዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነታችን፡ መብት፡ ከበሬታ፡ ተመልሰን፡ ለመመሥረት፡ በአንድነታችን፡ ተባብረን፡ ለእውነተኛ፡ ታሪካችን፡ ለመልካም፡ ብሔረሰብነታችን፡ ክብር፡ ለሃገራችን፡ ፍቅር፡ በየቤታችን፡ መብታችንን፡ ጥሶ፡ የገባብንን፡ የምንወዳትን፡ ሃገራችንና፡ ዘመዶቻችንን፡ ያስጣለንን፡ አምባ፡ ገነናዊ፡ የጭቆናና፡ የግድያ፡ ሥርዓት፡ ፈጽሞ፡ እንዲጠፋ፡ የጐበዝ፡ ያለህ፡ እየተባባልን፡አለቆቻችንን፡ በሥርዓት፡ በማቆም፡ ተባብረን፡ ቀንና፡ ሌሊትም፡ ተደራጅተን፡

በአምነታችን፡ አንፃር፡ ተግተን፡ ለመሥራት፡ እንነሳ፣ በወደቀብን፡ የግድያና፡ የግዴታ፡ ኃይል፡ ተጽእኖ፡ የተነሳ፡ ቁጥራችን፡ ቢያንስም፣ ነገ፡ በብልህነትና፡ በጀግኖቻችን፡ መስዋዕትነት፡ እንበዛለን፣ እንተርፋለን፣ ተነገ፡ ወዲያም፡ ሕዝባችንን፡ በነፃነቱ፡ ከበሬታ፡ እንመራለን።

ለእውነት፣ ለነፃነታዊ፡ መብት፣ ለዲሞክራሲያዊ፡ ልዕልናህ፣ ለአንድነትህ፣ ለኢትዮጵያዊነትህ፡ ክብር፣ ለሚያከራን፡ ታሪካችንና፡ ወገናችን፡ አንተም፡ ስደተኛው፡ ወገኔ፣ በአለህ፡ ኃይል፡ ባገኘኸው፡ መለስተኛ፡ የነፃነትህ፡ እድል፡ አይዞህ፡ ተባበር! ሠልፍህም፡ ይመር።

ታ ቀ ፍ
T.A.C.E.F.
እ
የኢትዮጵያ ልጆች ድርጅት።
The "N" Children of Ethiopia
Foundation

ኗኖ፡ ለብዙ፡ ዓመታት፡ በምስጢራዊ፡ ስትራተጂ፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ነፃነታዊ፡ መብት፡ ወደ፡ እውን፡ ተግባር፡ የሚሸጋገርበትን፡ ሂደትና፡ ስልት፡ በትዕግሥት፡ ሲመራና፡ እንደነቱን፡ ሲያስተባብር፡ የቆየውን፡ የመብት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት፡ ጽሕፈት፡ ቤታችን፡ የመንግሥታዊ፡ የሥራ፡ አካሉን፡ በልዩ፡ ካቢኔአችንና፡ በዲሞክራሲያዊ፡ የሕዝብ፡ ድርጅት፡ ኑባሬዎች፡ በተግባር፡ እንዲተረጐሙ፡ በማድረግ፡ አሁንም፡ ለማንኛቸውም፡ የንቅናቄያችን፡ ሕዋሳት፡ ተፈላጊውን፡ የሥራና፡ የድርጅታዊ፡ የጽሕፈት፡ ቤት፡ ቁሳቁሶች፡ እንዲሁም፡ የንጉሠ፡ ነገሥቱንና፡ የንቅናቄአችንን፡ መመሪያዎች፡ በየግዜው፡ በከበሬታ፡ በማስተባበር፡ በዚህ፡ መመሪያ፡አዋጅ፡ መሠረት፡ የተጠቀሱትን፡ ተግባሮች፡ በመከታተል፡ በትጋት፡ እንዲፈጽም፡ ማንኛቸውንም፡ የተቻለ፡ ጥረት፡ ለማድረግና፡

ሀ) በተለይም፡ ለመንግሥት፡ ኑባሬዎቻችንና፡ ለሕዝብ፡ ድርጅታዊ፡ አካሎች፡ በአንድ፡ ዲሲፕሊን፡ አመራር፡ ስልት፡ ተዋህደው፡ እንዲቀናበሩ፡ ትክክለኛ፡ የጽሕፈት፡ ቤቶቹን፡ መታወቂያ፡ አርማቸውንና፡ ማሕተሞች፡ እንዲሁም፡ የውስጣዊ፡ አስተዳደርና፡ የሥራ፡ አፈፃፀም፡ መመሪያዎችንና፡ የንብረትና፡

የእርዳታ፡ምንጮች፡የሚቀናበሩበተን፡ አንድ፡ ዓይነት፡ አመራርን፡ የያዘ፡ ሥነ፡ ሥርዓትና፡ ከዋናው፡ አካል፡ የመብት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ቤት፡ ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡ ጋር፡ የሚደረገውን፡ የሥራ፡ ግንኙነት፡መስመሮች፡በኅብረት፡እየቀየሰና፡እያስተባበረ፡ለጠቅላላው ሂደት፡ የሥራ፡ አፈፃፀም፡ ስልትና፡ ዲሲፕሊን፡ እንዲይዝ፡ በመቆጣጠር፡የድርጅታዊ፡ አካሎችን፡ ይመራ፡ ዘንድ፡ አዘናል።

ለ) ዓመታዊውን፡ ጠቅላላ፡ ኅቡዕ፡ ጉባዔና፡ እንዲሁም፡ ወቅታዊ፡ ስብሰባዎችን፡ በማደራጀት፡ የእርዳታና፡ የድጋፍ፡ የባሕላዊና፡ የፀሎት፡ ሰሚናሮችንም፡ እያዘጋጀ፡ ይመራል።

ሐ) የዋናውን፡ የኦዲተር፡ ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡ በማደራጀት፡ የኦዲተሩ፡ ተግባር፡ የሚሟላበትንና፡ ፍፁም፡ ነፃነታዊ፡ ሥልጣኑ፡ እንዲከበር፡ የሚደረግበትን፡ ተገቢውን፡ የሥራ፡ እንክብካቤ፡ የሥራ፡ ሁኔታ፡ ያቀናብራል።

መ) የርዕሰ፡ ብሔሩንና፡ የንጉሣዊ፡ ቤተሰባቸውን፡ የክብር፡ ጥበቃ፡ እንክብካቤ፡ በማሟላት፡ የሲቪል፡ ሊስት፡ በማውጣትና፡ በማደራጀት፡ በግቢ፡ ሚኒስትሩ፡ ኃላፊነት፡ ጥበቃውን፡ በሥርዓት፡ ያስተዳድራል።

ሠ) ለዘውድ፡ ምክር፡ ቤት፡ አባሎችና፡ የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ ተጠሪ፡ ርዕሳን፡ መማክርት፡ ለልዩ፡ ካቢኔው፡ ከፍተኛ፡ ባለሥልጣኖች፡ የጦር፡ አዛዦች፡ ለእንደራሴዎችና፡ ለ"መብት"ና፡ የ"አንድነት፡" አምዶች፡ ተጠሪዎች፡ ለንቅናቄአችን፡ የክብር፡ ኃይል፡ ኮከብ፡ ባልደረባዎችና፡ የልዩ፡ ካቢኔው፡ ልዑካኖች፡ ለሥራ፡ አፈፃፀም፡ ተፈላጊውን፡ ፕሮቶኮልና፡ ሎጂስቲክስ፡ በማሟላት፡ የከበሬታ፡ ሥራቸውን፡ ያከማቻል።

ረ) የልዩ፡ ካቢኔውና፡ የጦር፡ ኃይል፡ ጠቅላይ፡ መምሪያው፡ የሚገለገሉበትን፡ ቁሳቁስና፡ ተዘዋዋሪ፡ ሎጂስቲክስ፡ በሙሉ፡ በማስተባበር፡ ያደራጃል።

ሰ) የንቅናቄውን፡ ኃላፊዎች፡ ቋሚ፡ ሠራተኞችና፡ አስተዳዳሪዎች፡ እንዲሁም፡ ለጠቅላይ፡ ጽሕፈት፡ ቤቱ፡ የሥራ፡ ማስኪያሄጃና፡ ማስፈፀሚያ፡ በተፈቀደው፡ በጀት፡ መሠረት፡ በመቆጣጠር፡ ያስተዳድራል።

ሸ) የውስጥ፡ አስተዳደር፡ የሥርዓትና፡ የዲሲፕሊን፡ ጥበቃ፡ የኃይላችን፡ የክብር፡ ኮከብ፡ ሕግ፡ አስተናባሪዎች፡ "የጥቁር፡ አንበሳ፡" አምድ፡ ባልደረቦችን፡ በማቋቋም፡ ሕጋዊ፡ ግልጋሎታቸውን፡ በምስጢር፡ ስትራተጂ፡ በመቀየስና፡ በማቀናበር፡ የጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት፡ ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤታችን፡ ሥራውን፡ ይመራል፡፡ "የጥቁር፡ አንበሳ፡" የልዩ፡ ቴክኒክ፡ አምድ፡ ክፍል፡ ማመላለሻዎችንና፡ የንቅናቄውን፡ ግዜያዊ፡ መሥሪያ፡ ቤትንና፡ መሰብሰቢያ፡ አዳራሽና፡ ንብረቶችን፡ ሁሉ፡ በመቆጣጠር፡ በተጨማሪ፡ የድርጅቱን፡ ሰላሙንና፡ ደህንነቱን፡ በማንኛቸውም፡ ግዜ፡ በመጠበቅ፡ ያስከብራል፡፡

ቀ) የኢትዮጵያ፡ ታሪክ፡ የኢኮኖሚ፡ የሳይንስና፡ የቴክኖሎጂ፡ የጥናት፡ አካዳሚ፡ በእውቅ፡ ሊቃውንቶች፡ ቦርድ፡ የሚተዳደር፡ ሆኖ፡ በመቋቋም፡ ለኢትዮጵያ፡ ዘላቂና፡ መሠረታዊ፡ ጥቅም፡ የሚያስገኙትን፡ ጥናቶች፡ በማካሄድ፡ እንዲቀናበሩና፡ እንዲሁም፡ መሠረታዊ፡ የሕዝባችን፡ የባሕልና፡ የጥንታዊ፡ ታሪካችን፡ ቅርስና፡ ልማዶች፡ የሚጠበቁበትንና፡ ትምህርት፡ እንዲሆኑ፡ ሰሚናርና፡ የጥበብ፡ ጉባዔ፡ ለማዘጋጀት፡ ይቻል፡ ዘንድ፡ የጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤታችን፡ ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡ በሃዲሱ፡

አካዳሚ፡ አማካይ፡ ጥናቶችንና፡ ሊቃውናቶችን፡ አሰባስቦ፡ እንዲያስተባብር፡ አዘናል፡፡

ስለዚህም፡ ስለ፡ ብሔረሰባችን፡ ጥንታዊ፡ የባሕልና፡ ድርጅታዊ፡ ታሪክና፡ ልማዶችን፡ የሕዝብ፡ መብት፡ የሚከበርበት፡ የሕግጋት፡ ክዶችና፡ ሥርዓቶችን፡ የልማትና፡ በእርሻ፡ ግንባታ፡ ጥረት፡ የውሃና፡ የደን፡ ማዕድን፡ ጥበቃዎችና፡ በረሃን፡ ማልሚያዎች፡ ጥበቦችን፡ እንዲሁም፡ ኢትዮጵያ፡ የኑክሊየር፡ ነፃ፡ ዞን፡ በመሆን፡ በተፈጥሮ፡ የነዳጅ፡ ኃይሏ፡ ራስዋን፡ የምትችልበትን፡ ጥናቶችንና፡ ጉባዔዎችን፡ ለማካሄድ፡ ይቻል፡ ዘንድ፡ ሊቃውንቱንና፡ ተመራማሪዎችን፡ ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤታችን፡ ይጋብዛል፡፡

በ) ጥንታዊው፡ የኢትዮጵያ፡ ታሪክና፡ የባሕላችን፡ የቋንቋና፡ የሃይማኖታችን፡ ጽኑ፡ ቅርስና፡ ሥርዓት፡ ለአፍሪካና፡ በዓለም፡ ላይ፡ ለተበተኑት፡ ለጠቅላላው፡ የጥቁሮች፡ ወገኖቻችን፡ ሁሉ፡ የታሪክ፡ ምንጭና፡ መሠረት፡ ሆኖ፡ ከመኖሩም፡ በላይ፡ ኢትዮጵያችን፡ በነፃነት፡ ጮራዋ፡ ከባርነትና፡ ከኮሎኒያሊስት፡ ቀንበር፡ ለመላቀቅ፡ የሚታገሉትን፡ የብሔራዊ፡ ነፃ፡ አውጪ፡ ድርጅቶች፡ የፈለቁባትና፡ መሪዎቹም፡ የዳበሩባት፡ የታሪክ፡ እናት፡ የነበረችው፡ ኢትዮጵያችንን፡ዛሬ፡ የጥንት፡ ባሕሏንና፡

የሃይማኖት፡ ቅርስና፡ ሥርዓቷን፡ በሰው፡ ልጅ፡ የባርነት፡ ኢሰብአዊ፡ የወንጀል፡ ነጋዴዎች፡ብዝበዛ፡ ጊዜና፡ የአውሮፓ፡ ኮሎኒያሊስቶችና፡ የድሮው፡ ፋሺስቶች፡ እንኳን፡ ሊያጠፉት፡ ያልቻሉትን፡ የዘንድሮው፡ የኮሚኒስት፡ ኢምፔሪያሊስቶች፡ የጭቆናና፡ የእጅ፡ አዙር፡ ቅኝ፡ ግዛት፡ የግድያ፡ ቅጥረኞች፡ የባዕድ፡ ውራጅ፡ ሥርዓታቸውን፡ በምንኮራባት፡ ጥንታዊት፡ የኢትዮጵያ፡ ታሪካዊ፡ ገጽ፡ ላይ፡ ለመተካት፡ እንኳንስ፡ የታሪክ፡ ቅርሳችን፡ ቀርቶ፡ ሕዝባችንን፡ በመደብ፡ ትግል፡ በሚሉት፡ ሳቢያ፡ ከመደብ፡ በታች፡ የድህነት፡ ማቅ፡ መከረኛ፡ ወገናችንን፡ አልብሰውት፡ በጦርና፡ በጭፍን፡ የጭቆናና፡ የከሰረ፡ የኢኮኖሚ፡ ሂደት፡ በረሃብና፡ በስቃይ፡ አለንጋ፡ ሳያቋርጥ፡ ከአሥራ፡ አራት፡ ዓመታት፡ በላይ፡ በጥፋት፡ ማገዱት።

በጥንት፡ የባርነት፡ ወንጀለኞች፡ ጊዜ፡ ተጠልፈው፡ ከሃገራቸው፡ ከአፍሪካ፡ ወጥተው፡ ከቀሩት፡ ወገኖቻችን፡ የቁጥር፡ መጠን፡ በስተቀር፡ ከውድ፡ ሃገራችን፡ እስኮብልለው፡ ያሰደዱትና፡ የጠፉት፡ የወገኖቻችን፡ ብዛት፡ በዓለም፡ ላይ፡ አንደኛ፡ ደረጃን፡ ሊይዝ፡ ባለማቋረጥ፡ እየጨመረ፡ ነው። አንዳንድ፡ የአረመኔዎቹ፡ ግብረ፡ አበሮቹም፡ ድንገት፡ በተገኘ፡ በሕሊና፡ ጭንቀት፡ እየለቀቁ፡ በነፃው፡ የስደት፡ ዓለም፡

በመኮብለል፡ ጭፍን፡ የማንአለኝህነት፡ የጭቆናና፡ የግድያ፡ ሥርዓት፡ በውድ፡ አገራችን፡ ላይ፡ ያደረሱባት፡ መሆኑን፡ በራስ፡ መስካሪነት፡ የአረመኔዎቹን፡ ግፍ፡ ሂደትና፡ ኢሰብአዊ፡ የወንጀል፡ ተግባራቸውን፡ በመጠኑ፡ አጋልጠውታል።

በስደት፡ ዓለም፡ በጭንቀት፡ ያለነው፡ ኢትዮጵያውያንም፡ የኑሮአችን፡ የችግር፡ ሁኔታ፡ ዛሬ፡ በዓለም፡ ላይ፡ በዘር፡ ልዩነት፡ ተፅዕኖ፡ ከሰው፡ ልጆች፡ የእኩልነት፡ መብት፡ ሚዛን፡ በታች፡ በሁለተኛና፡ በሦስተኛ፡ ደረጃ፡ ከሚኖሩት፡ ወንድሞቻችንና፡ እኅቶቻችን፡ የጥቁር፡ ሕዝብ፡ ብሶት፡ ጋር፡ አጣምሮን፡ እኩል፡ ተካፋይ፡ በበለጠ፡ ሲያደርገን፡ የቱን፡ ያህል፡ የአፍሪካ፡ የአንድነት፡ ድርጅት፡ መሪዎች፡ የጥቁር፡ አፍሪካን፡ ተወላጆቻችንን፡ በሰብዓዊና፡ በእኩልነት፡ መብታቸው፡ ከበሬታ፡ በነፃነት፡ ተመሥርተው፡ በመረጡት፡ እናት፡ ሃገራቸው፡ ተመልሰውና፡ በእኩልነት፡ እንዲኖሩ፡ ያህል፡ እድል፡ እንዲሰጣቸው፡ እንኳን፡ እስከዛሬ፡ ድረስ፡ አለማድረጋቸው፡ ሲያሳዝን፡ ለብዙ፡ ግዜ፡ የተፈጥሮ፡ ወንጀል፡ የተፈፀመባቸው፡ አፍሪካውያን፡ የጥቁር፡ ወገኖቻችን፡ መፍትሄ፡ ማግኘቱ፡ የአፍሪካውያን፡ በሙሉ፡ የትውልድና፡ የታሪክ፡ ግዴታችን፡ ቢሆንም፡ በዚህ፡ ሁኔታ፡ የቆየው፡ የጥቁሮች፡

የእኩልነት፡ የተፈጥሮ፡ መብት፡ አንገብጋቢ፡ ጥያቄ፡ አጀንዳ፡ ላይ፡ ድርጅቱ፡ ባለመቆርቆር፡ የተኛበት፡ መሆኑን፡ በበለጠ፡ ያስገነዝባል።

ስለዚህም፡ እኛም፡ ኢትዮጵያውያን፡ ለመሠረታዊው፡ ጥንታዊት፡ የኢትዮጵያ፡ ታሪክና፡ የባሕላችን፡ ቅርስ፡ ከበሬታ፡ በክብካቤ፡ እንዲጠበቁ፡ ለምናደርገው፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነታችን፡ መብቶች፡ የአንድነት፡ ትግልና፡ በትውልድ፡ ሃገራችን፡ በሰላምና፡ በነፃነት፡ ተመልሰን፡ ለመኖር፡ ባለን፡ ተመሳሳይ፡ የመጨረሻ፡ ዓላማችን፡ በተለይ፡ የዓለም፡ ሕዝብ፡ የጥቁር፡ ወገኖቻችን፡ ለታሪካዊና፡ ለዲሞክራሲያዊ፡ እንቅስቃሴያችን፡ በወንድማማችነት፡ እኩል፡ ተቆርቋሪና፡ ደጋፊዎች፡ ሆነው፡ የኅብረት፡ ድጋፍ፡ ጥሪያችንንም፡ በበለጠ፡ ዳግም፡ እንደሚያስተጋቡ፡ አንጠራጠርም።

የዚህንም፡ ጥንታዊ፡ የወንድማማቾች፡ የድጋፍ፡ ምንጭ፡ በማስተባበር፡ የመብት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤታችን፡ ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡ ከጠቅላላው፡ የዓለም፡ የጥቁር፡ ሕዝብ፡ ኅብረተሰብ፡ በተለይም፡ የአፍሪካ፡ ትውልዶቻችን፡ ጋር፡ ለትግላችን፡ ድጋፍና፡ እርዳታ፡ ለማስገኘትና፡ ለማስተባበር፡ ግልጽ፡ የሆነ፡ ቀጥተኛ፡ ግንኙነትና፡ የኅብረት፡ ፕሮግራም፡ እያወጣ፡ እንዲመራ፡ አዘናል።

ተ) በየጊዜው፡ ታትመው፡ የሚወጡ፡ የእንቅስቃሴያችንና፡ የኢትዮጵያ፡ ሃገራችን፡ የዜናና፡ የማስታወቂያ፡ መሰራጫ፡ መጽሔቶች፡ "ነፃነታዊ፡ መብት፡ በአንድነት፡" ወይም፡ "መብት፡" ብቻ፡ በሚል፡ አርዕስት፡ እየተቀናበሩ፡ በመታተም፡ ለ"መብት"ና፡ ለ"አንድነት፡" ባልደረባዎቻችንና፡ ደጋፊዎቻችን፡ ሁሉ፡ እንዲሰራጩ፡ ለማድረግ፡ በመብት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤታችን፡ ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡ አማካኝ፡ የዜናና፡ የማስታወቂያ፡ ክፍል፡ የርዕሰ፡ አንቀጽ፡ ቦርድ፡ ተቋቁሞ፡ በትጋት፡ እንዲሠራና፡ እንዲሁም፡ የሬዲዮና፡ የቪዲዮ፡ ዜናና፡ የባሕላዊ፡ ትምህርት፡ ማሰራጫ፡ ክፍል፡ በተጨማሪ፡ በማደራጀት፡ ሥራውን፡ የጽሕፈት፡ ቤታችን፡ እንዲያስተባብር፡ አዘናል፡፡

ይህንንም፡ የተቀደሰ፡ የንቅናቄያችንን፡ ተግባር፡ ለማገዝ፡ የመብትና፡ በሃገር፡ ቤት፡ ያላችሁ፡ የአንድነት፡ ባልደረባዎቻችንና፡ ደጋፊዎቻችን፡ ሁሉ፡ ለሥራው፡ ቅኑነትና፡ ወቅታዊ፡ መሟላት፡ የሚቻላችሁን፡ መረጃ፡ ጽሑፍና፡ ድርሰቶች፡ እንዲሁም፡ ፎቶግራፎችና፡ ቴፖች፡ ከሙሉ፡ ድጋፋችሁ፡ ጋር፡ እንዳታበረክቱ፡ በአክብሮት፡ እንጠይቃለን፡፡

የባሕልና፡ የሙዚቃ፡ ኪነ፡ ጥበብ፡ የጽሑፍ፡ ደራሲያንም፡ መዝሙርና፡ የባሕል፡ እንጉርጉሮ፡ ድምፅ፡ የተቀረጸበትን፡ መስተውጽየአችሁን፡ በታወቀው፡ ብሔራዊ፡ ስሜታችሁ፡ የእውነት፡ ሕሊናችሁን፡ እንጋብዛለን፡፡

ወገኔ፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፤

ለኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ሰላምና፡ ልማት፡ ሕብረቱና፡ ባሕላዊ፡ ሥርዓቱ፡ በአንድነቱና፡ በዲሞክራሲያዊ፡ መብቱ፡ እንዲታነጽ፡ ታላቅ፡ ቋሚ፡ ዋስትናው፡ ናቸው፡፡

በጭንቀትህና፡ በችግርህ፡ ዘመን፡ በሰውነት፡ ብንርቅህ፡ በመንፈስና፡ በሃሳብ፡ በጐንህ፡ ቆመን፡ እንከተልሃለን፡፡

የተሸከምከው፡ የጭቆና፡ እና፡ የረሀብ፡ ቀምበር፡ ከትከሻህ፡ የሚወርድበት፡ ጊዜ፡ መጥቷልና፡ **በርትተህ፡ በሕብረትህ፡ ቁም፡፡**

ኢትዮጵያ፡ በነፃነቷ፡ ለዘለዓለም፡ ትኑር፡፡

RIGHT

ለኢትዮጵያ ኅብረተ ብሔር (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ የዘውድ መንግሥት
የኢትዮጵያ ሕዝብ የነፃነት መብት መሸጋገሪያ
የተባበሩት የኢትዮጵያ ብሔሮች አንድነት ጠቅላይ ምክር ቤት ።

ልዩ ጽሕፈት ቤት ።

ኟኖ: ማንኛቸውም: የንቅናቄው: ቋሚና: ተንቀሳቃሽ: ንብረቶች: በመብት: የጠቅላይ: ምክር: ቤታችን: ልዩ: ጽሕፈት: ቤት: አማካኝ: የተቋቋመው: ሀብት: ሁሉ:

ሀ) በበጐ: ሥራ: አገልግሎት: የኢትዮጵያ: ልጆች: "ታቀፍ" ተብሎ: በመሰየም: የተመዘገበው: የፋውንዴሽኑ: የውርስ: ንብረቶች: ሲሆኑ: ለማንም: ሰው: ወይም: ሕጋዊ: አካል: የማይሸጥ: የማይወረስና: የማይተላለፍ: ዘለዓለማዊ: ሆነው: በውጭ: ሃገር: ለሚኖሩት: ዲሞክራሲያውያን: የኢትዮጵያ: ሕዝብ: ግልጋሎት: ብቻ: የሚውሉ: መሰብሰቢያ: አዳራሽና: ጽሕፈት: ቤቶች: እንዲሁም: ለብሔረሰቡ: መወያያና: መማከሪያ: ከተቻለም: መፀለያ: መዳሪያና: መዝናኛ: ማዕከል: (ሴንተር) ወዘተ... በመሆን: ሕንፃው: ወይም: ቢሮው: የ"ዲሞክራሲ: ቤት:" በመባል: ለ"መብት:" አምዶች: ጥቅምና: የኢትዮጵያ: ዲሞክራሲያዊ: የነፃነት: መብት: በስደት: እስከኖረች: ድረስ: የመብት: ጠቅላይ: ምክር: ቤት: ልዩ: ጽሕፈት: ቤት: ለሚመራው: ተግባር: ብቻ: የሚውሉ: ንብረቶች: ሁነው: ይኖራሉ::

"ታቀፍ:" በበጐ: ሥራ: አገልግሎት: የኢትዮጵያ: ልጆች: ሰብዓዊ: ነፃ: ድርጅት:(ፋውንዴሽን:) በቋሚ: ቦርድ: (ትራስቲስ:) ይተዳደራል:: ቋሚ: የሕጋዊ: አካሉን: ማለትም: ለምሳሌ: ንብረቶቹ: "የዲሞክራሲ: ቤት:" በመሆን: በስደት: ለኢትዮጵያ: ሕዝብ: ሰብአዊና: ዲሞክራሲያዊ: ግልጋሎት: የቆመበትን: ቋሚ: ዓላማ: መለወጥ: አይችልም::

ለ) በዘውድ: ምክር: ቤታችን: ውሳኔ: መሠረት: የሥራውን: አመራር: በሚመለከት: ማንኛቸውም: የሥራ: ጉዳይ: የወቅቱ: የኢትዮጵያ: ተጨባጭ: ሁኔታ: ስለሚያስገድድ:

ካለጠቅላይ: ምክር: ቤታችን: ልዩ: ጽሕፈት: ቤትና: እንዲሁም: ካለ"መብት"ና: የ"ታቀፍ:" አምዶች: ሕዝባዊና: ሰብአዊ: ድርጅቶቻችን: በስተቀር: የልዩ: ካቢኔውና: የንቅናቄውን: የጦር: ኃይል: አካሎችና: የበላይ: ኃላፊዎቻችን: ስምና: የሥራ: መድብ: ዝርዝር: ለኦፊሴል: የሥራ: አገልግሎት: ጉዳይ: ካላስፈለገ: በስተቀር: በቁጥር: ቃል: ምስጢራዊ: ስትራተጂ: ተጠብቆ: እንዲሠራበት: የተላለፈውን: ውስኔና: እንዲሁም:

ሐ) በማንኛቸውም፡ ግዜ፣ የዘውድ፡ ምክር፡ ቤታችን፣ ልዩ፡ ካቢኔውና፡ የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኞች፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ ጠቅላይ፡ መምሪያ፡ የሥራ፡ እቅዶችና፡ ሰነዶች፣ የሥራ፡ አፈፃፀም፡ ትዕዛዞችና፡ ሪፖርቶች፣ በጥብቅ፡ ምስጢር፡ ተጠብቀው፡ እንዳይባዙ፡ በክብርና፡ በጥንቃቄ፣ በልዩ፡ ካቢኔው፡ ኃላፊነት፡ ብቻ፡ እንዲኖሩ፡ ሲሆን፤

መ) ለሕዝብ፡ አገልግሎት፡ እንዲታወቁ፣ በልዩ፡ ካቢኔው፡ ተፈቅደው፡ በሥርዓት፡ ከተወሰኑት፡ መግለጫዎችና፡ መጠይቆች፡ በስተቀር፡ ማንኛቸውም፡ ሥራና፡ እቅድ፡ በሚስጢር፡ እንዲጠበቁ፡ በማለት፡ የቀረቡልንን፡ የሥራውን፡ አመራር፡ በሚመለከት፡ አጠቃላይ፡ ጉዳዮች፡ የዘውድ፡ ምክር፡ ቤታችንን፡ ጠቅላላ፡ ውሳኔዎች፡ በሙሉ፣ ወደን፡ በመቀበል፡ በከበሬታ፡ አጽድቀናል::

ነፃነታዊ፡ መብት፡ በአንድነት!
ግርማዊ፡ ቀዳማዊ፡ አምሃ፡ ሥላሴ፡
ሞዓ፡ አንበሳ፡ ዘእምነገደ፡ ይሁዳ፡
ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ዘኢትዮጵያ፡
የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኞች፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡
ሕዝባዊ፡ ሠራዊት፡ ጠቅላይ፡ የጦር፡ አዛዥ::

ግርማዊ ቀዳማዊ አምሃ ሥላሴ
ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።



ግርማዊ ቀዳማዊ አምሃ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ፡፡

ለኢትዮጵያ ኅብረተ ብሔር (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ የዘውድ መንግሥት

የበላይ ጠባቂ

ግርማዊ ቀዳማዊ አምሃ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ፡፡

የተቀደሰ፡
የጥሪ፡ መልዕክት፡ አዋጅ፡

ለመላው፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ በሃገራችንና፡ በስደት፡ ዓለም፡ በታላቅ፡ ስቃይና፡ ችግር፡ ላይ፡ ለምትገኘው፡ ጅግናው፡ ወገኔ፡ በሙሉ!

የኢትዮጵያን፡ ሕዝብ፡ መሠረታዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ በተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኞችህ፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ ሕዝባዊ፡ ሠራዊትህ፡ የኅብረት፡ ትግል፡ ለማስገኘትና፡ በዲሞክራሲያዊ፡ ኑባሬዎችህ፡ ልዕልና፡ የኅብረተ፡ ብሔር፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የሕዝብ፡ ሸንጎ፡ እግዝዕናህን፡ አጽድቀህ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል፡) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥትህን፡ ለማቆም፡ የተሰለፈውን፡ ጀግናው፡ የኢትዮጵያን፡ ሕዝብ፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ ሠራዊት፡ በመደገፍ፡ የወገኖቻችንን፡ መስዋዕትነት፡ በሃገራችን፡ ታሪካዊ፡ ከበሬታ፡ ስም፡ በሚቻልህ፡ ሁኔታ፡ ሁሉ፡ አብረህ፡ በመካፈል፡ ተባብረህ፡ ተነስ! ይህንን፡ የጥሪ፡ መልዕክት፡ አዋጃችንን፡ እያስተጋባህ፡ ላልሰማው፡ አሰማ፡፡

እያንዳንዱ፡ የኢትዮጵያ፡ **ዜጋ፡ በሙሉ፡** በሰብአዊ፡ ከበሬታው፡ ሰላሙንና፡ ነፃነቱን፡ በመሠረታዊ፡ መብቱ፡ ልዕልና፡ በኅብረተ፡ ብሔሩ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ ሸንጎ፡ እግዝዕና፡ የሕዝብ፡ መንግሥቱን፡ በሰላምና፡ በፍጹም፡ ዲሞክራሲያዊ፡ ሂደት፡ ብዙሃን፡ የፖለቲካ፡ ፓርቲዎቹን፡ አቋም፡ ለሃገሩና፡ ለሕዝቡ፡ ብልጽግና፡ በመልካሙና፡ በገናናው፡ አዛኝ፡ ጥሩ፡ ባሕርይው፡ ለታሪኩ፡ ከበሬታ፡ ለሃይማኖቱ፡ ቅድስና፡ የትውልዱን፡ ሙሉ፡ የትምህርትና፡ የጤናማ፡ እድገት፡ የተሟላ፡ የወደፊት፡ እድሉን፡ የአዛውንቱንና፡ የጃግኖቹን፡ ብቁ፡ ኑሮ፡ ንብረቱንና፡ እርስቱን፡ በጥንቃቄ፡ አስከብሮ፡ ጠብቆና፡ አሟልቶ፤

በራሱ፡ ኃይልና፡ በራሱ፡ ፈቃድ፡ በነፃ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የሕዝብ፡ ጠቅላላ፡ ምርጫ፡ ውሰኔ፡ ሰላማዊ፡ መንግሥቱን፡ በእውን፡ እስከ፡ አስገኘና፡ የሃገሩን፡ ድንበርና፡ አንድነት፡ በቆራጥነትና፡ በመስዋዕትነት፡ ነፃነቱን፡ እስከ፡ አስከበረ፡ ድረስ፡ መቼም፡ እንደማይተኖና፡ ምንጊዜም፡ እንደማይቸነፍ፡ አኩሪ፡ የታሪኩ፡ ጠባይ፡ መስከሩ፡ ነው።

ከአንግዲህ፡ ወዲህ፡ ኢትዮጵያችን፡ ለምንም፡ ዓይነት፡ ጊዜያዊም፡ ሆነ፡ ወታደራዊ፡ የአምባ፡ ገነኖችና፡ የባዕድ፡ ስውር፡ የቅኝ፡ ግዛት፡ ቅጥረኞች፡ ኃይል፡ ብዝበዛና፡ ጭፍን፡

የአረመኔዎችና፡ የነፍሰ፡ ገዳዮች፡ የብቸኝነት፡ ይዘት፡ እንዳትመች፡ የግልና፡ የኅብረት፡ የሕሊና፡ መሀላ፡ በማድረግ፡ የተቀደሰውን፡ ብሔራዊ፡ ግዳጃችንንና፡ ግዴታችን፡ ተገንዝበነው፡ ይህችን፡ የዛሬዋን፡ የውል፡ ቀን፡ የካቲት፡ ፳፮ ቀን፡ ፲፱፻፹ ዓ ም፡ ለኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ ልዕልና፡ በተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኞች፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ ሕዝባዊ፡ ሠራዊት፡ የትግል፡ ኅብረት፡ እዮሀ፡ የድል፡ ችቦ፡ የበራበት፡ አዲስ፡ ምዕራፍ፡ ሆና፡ በመቆጠር፡ "የኅብረት፡ ቀን፡" ተብላ፡ በመጠራት፡ በየዓመቱ፡ እንድታከብሩዋት፡ ስናሳስባችሁ፡ጥልቅ፡ የሆነ፡ ደስታና፡ ኩራት፡ ይሰማናል፡፡

የምሥራቹንም፡ ዜና፡ በያለበት፡ ለኢትዮጵያውያን፡ ወገኖቻችን፡ ሁሉ፡ እንዲደርሳቸው፡ ያህል፡ በሃገራችን፡ ዘዴና፡ ልማድ፡ መሠረት፡ እንዲነገርና፡ እንዲታወቅ፡ ስንፈቅድ፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኞች፡ የአንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ ጀግኖች፡ ሁሉ፡ በበኩላችሁ፡ ያልተቆጠበ፡ ትብብራችሁን፡ የተቀደሰውን፡ የብሔራዊ፡ ግዳጅችሁንና፡ መስዋዕትነታችሁን፡ በገናናው፡ የኢትዮጵያ፡ ታሪካችን፡ ስም፡ እንድትፈጽሙ፡ በኃያሉ፡ የኢትዮጵያ፡ አምላካችን፡ ረዳትነት፡ እናሳስባችኋለን፡፡

ለኢትዮጵያ: ሕዝብ: ዲሞክራሲያዊ: የነፃነት: ልዕልና: ለተባበሩት: የኢትዮጵያ: አርበኞች: አንድነት: የጦር: ኃይል: የሕዝብ: ሠራዊታችን: የድል: ቀን: ከገናናው: ወገናችን: ጋር: ሁላችንንም: እንዲያበቃን: የክብር: ኃይል: ኮከብ: የጦር: ባልደረባችን: ቅዱስ: ጊዮርጊስ: ኃይልና: መከታ: ይሁናችሁ:: ኃያሉ: እግዚአብሔርም: በግፍ: የፈሰሰውን: ደም: ቆጥሮ: እንደሚረዳን: አንጠራጠርም::

ግርማዊ ቀዳማዊ አምሃ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።
ለኢትዮጵያ ኅብረተ ብሔር (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ የዘውድ መንግሥት
የበላይ ጠባቂ

የተባበሩት የኢትዮጵያ አርበኞች

RIGHT

SOLIDARITY

POWER – WITH – HONOUR

አንድነት የጦር ኃይል

ለኢትዮጵያ፡ የጦር፡ ኃይልና፡ የፖሊስ፡ ሠራዊት፡ ባልደረባ፡ ሁሉ፡

ከሁሉ፡ አስቀድሞ፡ የውድ፡ ሃገራችንን፡ አንድነት፡ የወሰንዋን፡ ከበሬታና፡ የሕዝባችንን፡ ደህንነት፡ ጠንክረህ፡ በማንኛቸውም፡ ጊዜ፡ ጠብቅ፡፡

ዛሬ፡ በአደባባይ፡ እራሳቸውን፡ በበላይህ፡ ተሿሹመው፡ ወደ፡ የማይጠፋ፡ እሳት፡ የሚነዱህ፡ ጥቂት፡ አምባ፡ ገነን፡ ወንበዴዎች፡ በግዜያዊ፡ ብለውም፡ በጉልታዊ፡ የሥልጣን፡ ጥቅም፡ ሽሚያ፡ ውድ፡ ሃገራችንን፡ በከባድ፡ የባርነት፡ ቀንበርና፡ በእጅ፡ አዙር፡ የባዕድ፡ ቅኝ፡ ግዛት፡ የኮሚኒስት፡ ወጥመድ፡ ስር፡ በመጣል፡ የሞትከላትን፡ ውድ፡ ሃገርህን፡የነገይቱን፡ የኢትዮጵያ፡ ትውልድህን፡ የነፃነት፡ እድልና፡ ሰላማዊ፡ ሕይወት፡ ጭምር፡ በአረመኔ፡ ይዘት፡ በግፍ፡ ወገንህንና፡ እራስህንም፡ ስለጨፈጨፉት፡ በተለይም፡ ገናና፡ ባሕልህንና፡ የግል፡ ሃይማኖት፡ እምነትህን፡ በማራከስና፡ በማፈን፡ ብሔራዊ፡ ንቃተ፡ ሕሊናህን፡ በማቃለል፡ የኢትዮጵያን፡ ሕዝብ፡ በሙሉ፡ የሕይወቱን፡ አለኝታና፡ ሕጋዊ፡ ሰላሙን፡ በማሳጣት፡ ፈጽመው፡ ስላደኸዩት፤

አንተንም፡ ከኋላህ፡ በሃሴት፡ መለከት፡ ወደ፡ ጥፋት፡ የሚገፋፋህ፡ እጅህ፡ ውስጥ፡ ያሉት፡ ጥቂት፡ ወንበዴዎች፡ ዘላቂውን፡ የኢትዮጵያን፡ ሕዝብ፡ የጋራ፡ ጥቅምና፡ እድገት፡ በከሰረ፡ የኢኮኖሚ፡ ፕሮግራም፡ በከረረ፡ ሂደት፡ በእብሪተኛነትና፡ በማን፡ አለኝህነት፡ ጭፍን፡ የበቀልና፡ የጥፋት፡ ማዕበል፡ ውስጥ፡ በመጣል፡ የአንድ፡ እናት፡ ልጆች፡ የሆኑትን፡ የኢትዮጵያውያንን፡ ታሪካዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ አፍነው፡ የሃገራችንን፡ ብሔረሰቦች፡ የታሪክና፡ የአንድነት፡ ሕልውና፡ በማቆሰል፡ መንፈሱን፡ አውከው፡ ፡ የሕዝባችንን፡ የከበሬታ፡ ይዘቱንና፡ ሰላሙን፡ እያደሙ፡ ጤና፡ በማሳጣት፡ አንድ፡ አትዮጵያችንን፡ በኃይልና፡ በግዴታ፡ ከፋፍለው፡ በመግዛት፡ በሰላምና፡ በባሕላችን፡ ነፃነታዊ፡ መብት፡ በዲሞክራሲያዊ፡ ልዕልና፡ ከበሬታ፡ በፍቅርና፡ በመተማመን፡ ለመመሥረት፡ ያገዱዋት፡ የመጀመሪያው፡ ትልቁ፡ ጠላቶችህ፡ እነሱው፡ ናቸውና፡ ከቅጥር፡ የግድያ፡ የባዕድ፡ ግብረ፡ አበሮቻቸው፡ ጋር፡ አንተው፡ እራስህ፡ የምታውቃቸው፡ እስከአሁንም፡ ዋናው፡ የኃይላቸው፡ ምንጭ፡ ሆነህ፡ ባንተው፡ ትከሻ፡ ያቆየሃቸው፡ ስለሆነ፡ የሃገሬ፡ጉበዝ፡ በኢትዮጵያ፡ የውስጥ፡ ጠላትና፡

በሽብርና፡ በግድያ፡ መሣሪያ፡ ባድር፡ ባዮች፡ አጥፊዎችህ፡ አትመራ! ሳትጠራጠር፡ በቆራጥነትና፡በጥንታዊ፡ የኢትዮጵያ፡ ገናና፡ ታሪክህ፡ ከበሬታ፡ ተነስ! ትከሻህን፡ አዙር!

የሚሰቃየው፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ወገንህ፡ ነውና፡ እዘን፤ እጅህንም፡ ከወገንህ፡ ከሕዝቡ፡ ላይ፡ አንሳ፡ ይብቃህ! የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ እርግጠኛ፡ ፍጹም፡ የነፃነት፡ ምሥራች፡ የአንተም፡ ስለሆነ፡ በጀግናው፡ የኢትዮጵያዊነትህ፡ መንፈስ፡ ተባብረህ፡ ተነስ! ለኢትዮጵያ፡ ብለው፡ የሚሞቱትን፡ የተረፉትን፡ አለቆችህንም፡ ፈጽሞ፡ በተራ፡ በተራ፡ በወንበዴዎቹ፡ መሠረታዊ፡ የአመራር፡ ውድቀት፡ ምክንያትና፡ የዘወትር፡ ሰበብ፡ ጨርሶ፡ ሳያጠፋቸው፡ በተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኞች፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ ሕዝባዊ፡ ሠራዊት፡ ስም፡ የጐበዝ፡ አለቆችህን፡ በሥርዓት፡ መርጠህና፡ ደግፈህ፡ በማቆም፡ ከሕዝባችን፡ ጋር፡ በመዋሀድ፡ በአንድነት፡ ተባብረህ፡ ተነሳ!

ለዚሁም፡ ታማኝነትህን፡ በማስመስከር፡ በቁርጠኛ፡ ብሔራዊ፡ ግዳጅህ፡ የተቀደሰ፡ ተግባርህን፡ በቶሎ፡አሳውቀን፡፡ ገናናው፡ ጀግና፡ የኢትዮጵያ፡ ወገኔ፡ አለሁ፡ በለኝ! ለኢትዮጵያችን፡ ቋሚ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነትዋ፡ መብት፡ ልምላሜ፡

ለብሔራችን: የአንድነት: ሕልውና: ፈጽሞ: የጥፋት: ምክንያት: አትሁን: በገናናው: ታሪክህ: ሙሉ: እምነት: ተነስ! የነፃነትህን: መብት: የዲሞክራሲያዊ: ልዕልናህን: ለማስከበር: ከተባበሩት: የኢትዮጵያ: አርበኞች: አንድነት: የጦር: ኃይል: ሕዝባዊ:ሠራዊት: ጋር:የተቀደሰ: ብሔራዊ: ግዳጅህን: ለመፈጸም: ጐን: ለጐን: አብረህ: በመቆም: በአንድነት: ተሰለፍ:: ሕዝባችንና: የጦር: ሠራዊቱ: አንድ: አካል: ስለሆነ: የኢትዮጵያ: ሕዝብ: በዲሞክራሲያዊ: ነፃ: ሥርዓቱ: ሕዝቡን: የማስተዳደሪያ: ሕገ: መንግሥቱን: በፈቃዱ: እስከአቆመ: ድረስ: በምንም: ሁኔታ: ወይም: ሰበብ: ሳትነጣጠል: በማንኛቸውም: ጊዜ: አንድ: ላይ: ሆነህ: የትግሉን: ሥራ: አብረህ: ተሳተፍ!

እውነትስ: ከሆነ: ዛሬ: በገሀድ: ይሉኝታ: እንኳን: ቀርቶ: ገደብ: በሌለው: አምባ: ገነናዊ: የፈላጭ: ቆራጭ: የወንበዴነት: ኃይላቸው: በወታደሩ: ጉልበትና: ድጋፍ: በየሰበቡ: አማሃኝተው: በሥልጣናቸው: በዘረፋት: በደሀው: የኢትዮጵያውያን: የግል: ሀብት: የሚንደላቀቁትና: በማን: አለኝህነትና: በጠብ: መንጃ: አፈሙዝ: በሕዝባችን:

ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነቱ፡ መብትና፡ በአንድነቱ፡ ሕልውና፡ በብቸኝነት፡ሂደት፡ የሚያፌዙት፡ አንሶአቸው፡ እነኚህ፡ የኢትዮጵያንና፡ የወገንህን፡ ሕይወት፡ ሰላሙንና፡ የእድገት፡ እርምጃውን፡ አጥፊዎች፡ በራስ፡ መስካሪነት፡ አሁን፡ ገና፡ በይፋ፡ ታውቆ፡ በተጋለጠው፡ ስርቆታቸው፡ በወኪሎቻቸው፡ የእጅ፡ አዙር፡ ስውር፡ ሥርዓት፡ አማካይ፡ ሠራተኛውና፡ ድሀው፡ በስንት፡ ዓመታት፡ ልፋትና፡ ጥረት፡ ደም፡ ተፍቶ፡ ጥሮ፡ ግሮ፡ ያፈራውን፡ ሀብት፡ አግበስብሰው፡ በውጭ፡ ሀገር፡ በማሸሽ፡ ቀድመው፡ ባሰናዱት፡ የጥቅም፡ ግብረ፡ አበሮቻቸው፡ ምሬት፡ ካባ፡ ለውጠው፡ ለመቀማጠል፡ ኮብልለው፡ ጨርሰው፡ ሳያመልጡህ፡ በቶሎ፡ ይዘህ፡ ለትክክለኛው፡ የሕዝብ፡ ፍርድ፡ አቅርባቸው፡፡

በተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኞች፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ ስም፡ በጦር፡ ኃይላችን፡ ሕዝባዊነት፡ ሥርዓት፡ ወታደሩና፡ የሲቪሉ፡ ሠራዊት፡ አንድ፡ አካል፡ ሆኖ፡ ለሰላም፡ ኑሮው፡ ግንባታና፡ ለአንድነቱ፡ የጋራ፡ መከታ፡በመሆን፡ በሰላምና፡ በኅብረት፡ ቆሞ፡ በዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነቱ፡ መብት፡ ልዕልና፡ በአንድነት፡ የጦር፡ ኃይሉ፡ ኅብረት፡ የትውልዱን፡ የረጅም፡ ግዜ፡ ጥቅምና፡ ብለጽግና፡ ለማስገኘትና፡ የኢትዮጵያን፡ ኅብረተ፡ ቢሔር፡ (ፌዴራል፡) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥትህን፡ ለማጽናት፡ በታሪክህ፡ ከበሬታ፡ ታላቁ፡ እድል፡ በይበልጡኑ፡ አሁንም፡ የአንተው፡ ስለሆነ፡ ሳታመነታ፡ ተጠቀምበት፤

ሕዝባችንን፡ አርበኞቻችንን፡ ሠራተኛውን፡ ገበሬውን፡ ነጋዴውን፡ ምሁሩን፡ ወጣቱን፡ አዛውንቱን፡ የመንፈሳዊ፡ መምህሩን፡ የጐበዝ፡ አለቃውን፡ በጠቅላላው፡ ትውልዳችንን፡ ሁሉ፡ ተነስተህ፡ እርዳ! የሕዝባችንን፡ ሰላሙን፡ መልስ! ገናናው፡ ስምህ፡ ይትረፍ!

እውነተኛ፡ የኢትዮጵያ፡ ወዳጆች፡ የሆናችሁ፡ በታሪክና፡ በባሕል፡ በሃይማኖትና፡ በቋንቋ፡ እንዲሁም፡ በምድረ፡ ገጽ፡ አንድ፡ አካል፡ ፍጥረት፡ በመሆን፡ ከጥንት፡ ጀምሮ፡ የተዋሃድነው፡ ከአንድ፡ የወንዝ፡ ምንጮች፡ የምንጠጣው፡ የጐረቤት፡ ሃገር፡ ወንድሞቻችን፡ ወዳጆቻችንና፡ ወገኖቻችን፡ እንዲሁም፡ የነፃው፡ ዓለም፡ ዲሞክራሲያን፡ ሕዝብ፡ ሆይ!

በተቀዳሚ፡ በጦርና፡ በጭቆና፡ በትር፡ በድርቅና፡ በረሃብ፡ አለንጋ፡ ለተሰደደው፡ ለወገኖቻችን፡ ኢትዮጵያውያን፡ ሁሉ፡ ጠለላ፡ በመስጠት፡ ያላችሁን፡ በማካፈል፡ በሰብዓዊ፡ ርሕራሄና፡ በእንግዳ፡ ተቀባይነታችሁ፡ ባላችሁ፡ አቅም፡ አስተናግዳችሁ፡ በሰላም፡ ያቆያችሁን፡ ወንድሞቻችን፡ እህቶቻችንና፡ ወዳጆቻችን፡ ሁሉ፡ ታላቅ፡ ክብርና፡ ምስጋና፡ ይገባችኋል፡፡ ውለታችሁንም፡ አጸፋውን፡ ለመመለስ፡ ኃያሉ፡ እግዚአብሔር፡ ያብቃን፡፡

በታሪካችን፡ ከዚህ፡ በፊት፡ ማንኛውም፡ አደጋም፡ ሆነ፡ ጠላት፡ ያላደረሰብንን፡ በደል፡ ዛሬ፡ በኢትዮጵያ፡ ሕዝባችን፡ ላይ፡ እጥፍ፡ ድርብ፡ የግፍ፡ እልቂትና፡ ሞት፡ ስለደረሰብን፡ በታጋሽነትና፡በታወቀው፡ርኅሩህነታችሁ፡ መንፈስ፡ የኢትዮጵያን፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነታችንን፡ መብት፡ ልዕልና፡

በተባበሩት፡የኢትዮጵያ፡አርበኞቻችን፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ ሕዝባዊ፡ ሠራዊት፡ የኅብረት፡ ትግል፡ የማያጠራጥር፡ ድል፡ ለማስገኘት፡ በምናደርገው፡ ታላቅ፡ የሕዝባችን፡ መስዋዕትነትና፡ ለተቀደሰው የትግላችን፡ እርምጃ፡ በሙሉ፡ መንፈስና፡ ኃይላችሁ፡ እንድትረዱን፡ በገናናው፡ ሕዝባችን፡ ስም፡ በአክብሮት፡ እንጠይቃለን፡፡

በመልካም፡ ጉርብትናችን፡ በነፃነትና፡ በሰላም፡ ወዳድነታችን፡ በፍቅርና፡ በወንድማማች፡ አክባሪነታችን፡ ከዚህ፡ በፊት፡ ፋሺስቱን፡ የኮሎኒያሊስት፡ ቀንበር፡ ለመጣል፡ አብረን፡ ተሰልፈን፡ የተሰዋንበት፡ የአባቶቻችንና፡ የእናቶቻችንን፡ አጥንትና፡ ደም፡ የተከሰከሰበትና፡ የፈሰሰበት፡ አኩሪ፡ የጋራ፡ ታሪካችን፡ ሐውልት፡ እንደመሆኑ፡ እውቅ፡ ነው፡፡ ከዚያም፡ በከበሬታ፡ ተባብረን፡ ሰላምና፡ ሥልጣኔ፡ በሃገራችንና፡ እንዲሁም፡ በዓለም፡ላይ፡ እንዲሠፍን፡ በትዕግሥት፡ በትጋትና፡ በመስዋዕትነት፡ የሠራንበት፡ የመሠረትነው፡ ቋሚ፡ ታሪካችን፡ ምስክራችን፡ ነው፡፡

በተለይ፡ ዛሬ፡ በአምባ፡ ገነኑ፡ ራሱን፡ በራሱ፡ በኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ላይ፡ የሾመው አረመኔ፡ ኢሰብዓዊ፡ ፀረ፡ ዲሞክራሲ፡ ፀረ፡ ሃይማኖት፡ የጭቆናና፡ የክህደት፡ ሥርዓት፡ በኮሚኒስት፡

ኢምፔሪያሊስት፡ ሚና፡ በሶቪየት፡ ያው፡ የድሮው፡ ፋሹስታዊ፡ የአውሮፓውያን፡ የኮሎኒያሊስት፡ የስውር፡ ቅኝ፡ ግዛት፡ ሂደት፡ የእጅ፡ አዙር፡ የግድያ፡ ቅጥረኞቻቸውና፡ ግብረ፡ አበሮቻቸው፡ ጋር፡ አብሮ፡ በማሴር፡ ነፃነቱንና፡ አንድነቱን፡ ወዳድ፡ የተከበረውን፡ ጀግና፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝባችንን፡ ሰላማዊ፡ ሕይወቱንና፡ እድገቱን፡ በማናጋት፡ የምታውቁትን፡ ገናናው፡ የታሪካችንን፡ አቋም፡ የጋራ፡ የባሕላችንና፡ የሃይማኖት፡ ቅርሳችንን፡ እንዲሁም፡ የሰብዓዊ፡ መብታችንና፡ ጠቅላላውን፡ የሕዝባችንን፡ ሕይወቱንና፡ ሰላማዊ፡ ኑሮውን፡ ጨርሰው፡ በማውደም፡ ፍፁም፡ ስላደኸዩት፡

በዚች፡ ቀውጢ፡ ጊዜያችን፡ በበለጠ፡ ወንድማማችነት፡ የተፈተነውን፡ በጥንት፡ ወዳጅነታችን፡ ከበሬታ፡ የተመሠረተውን፡ ሙሉ፡ እርዳታችሁንና፡ ድጋፋችሁን፡ በዲሞክራሲያዊት፡ ኢትዮጵያ፡ ስም፡ በአምላካችን፡ ጽኑ፡ እምነት፡ በኅብረት፡ ቆመን፡ በአክብሮት፡ እንጠይቃለን።

እንዲሁም፡ የኢትዮጵያ፡ ወዳጆችና፡ ለሕዝባችን፡ ደህንነት፡ ተቆርቋሪ፡ የሆናችሁት፡ የነፃው፡ ዓለም፡ ኅብረተ፡ ሰብ፡ ደጋፊዎቻችን፡ የመንግሥት፡ ኃላፊዎች፡ ድርድቶችና፡ ግለሰቦች፡ በሙሉ፡

ምንም፡ ሳታመነቱ፡ በሕዝባችን፡ ንጹሕ፡ ደም፡ የተጠመቁትን፡ በኮሚኒስት፡ ኢምፔሪያሊስት፡ ቅጥረኞች፡ ኃይል፡ የኢትዮጵያን፡ ሕዝብ፡ አጥፊዎችና፡ ነፍሰ፡ ገዳዮች፡ የፈሪሃ፡ እግዚአብሔር፡ እምነትና፡ የሀገር፡ ፍቅር፡ በሌላቸው፡ በግል፡ ጥቅምና፡ በሥልጣን፡ ጥማት፡ ተሳክረው፡ በቂምና፡ በቀል፡ በጠባብ፡ አስተሳሰብ፡ ማን፡ አለኝህነት፡ አገራችንንና፡ ሕዝባችንን፡ ያወደሙትን፡ የሰብአዊ፡ ወንጀል፡ የፈጸሙትን፡ አረመኔዎች፡ ዛሬ፡ መልካቸውን፡ ለውጠው፡ በሀሰተኞች፡ ፕሮፓጋንዳ፡ በሰለጠኑ፡ ሁሉ፡ ገብ፡ አስመሳዮች፡ ተሳስታችሁ፡ የአረመኔውቹን፡ ሃላፊዎችና፡ አታላይ፡ አቋም፡ በምንም፡ ሁኔታ፡ በስህተት፡ በመደገፍ፡ በኮሚኒስት፡ ኢምፔሪያሊስት፡ ወጥመድ፡ ወድቃችሁ፡ የኢትዮጵያን፡ ሕዝብ፡ ጠላትነት፡ እንዳታተርፉ፡ በመጠንቀቅ፤ ይልቁንስ፡ በሚቻላችሁ፡ መንገድ፡ ሁሉ፡ በዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ ዓላማና፡ በኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ እምነት፡ በአንድነት፡ ጠንክሮ፡ የቆመውን፡ የሕዝባችን፡

እነሆ፡ የኅብረት፡ ኃይል፡ ዲሞክራሲያዊ፡ ንቅናቄ፡ እንድትረዱን፡ ያህል፡ ሙሉ፡ የፖለቲካና፡የሞራል፡ትብብራችሁን፡ በከበሬታ፡ ስንጠይቅ፡ ተጨባጭ፡ የማቲሪያል፡ እርዳታችሁን፡ በመቀጠል፡ ከምንም፡ ግዜ፡ በይበልጥ፡ ዛሬ፡ ነገ፡ ሳትሉ፡ ታደርጉልን፡ ዘንድ፡ በኢትዮጵያ፡ ነፃነትና፡ በሕዝባችን፡ ዲሞክራሲያዊና፡ መሠረታዊ፡ መብት፡ ልዕልና፡ በአርበኞቻችን፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ ሀቀኛና፡ ቁርጠኛ፡ ሕዝባዊ፡ ሠራዊት፡ የኅብረት፡ እንቅስቃሴ፡ ስም፡ ለእውነተኛው፡ ለሃይማኖተኛው፡ ሰላሙን፡ ደህንነቱንና፡ ነፃነቱን፡ ለተጠማው፡ የሰብአዊ፡ ክብሩን፡ ለተነፈገው፡ በግፍ፡ በረሃብ፡ በጦርና፡ በግዴታ፡ በትር፡ ደጋግሞ፡ ለሚሰቃየው፡ ቆራጥና፡ ጀግና፡ በታሪኩ፡ ከበሬታ፡ አቋመምና፡ በባሕሉ፡ ጽኑ፡ እምነት፡ ለአንድነቱ፡ ዘወትር፡ ለሚሰዋው፡ ውለታውን፡ መቼም፡ ለማይረሳው፡ ወዳጁን፡ ዘወትር፡ ለሚያከብረው፡ ትልቅ፡ የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡ ስም፡ እርዳታችሁን፡ በታላቅ፡ አክብሮት፡ እንጠይቃለን፡፡

የሃገሬ፡ ጉ-በዝ!

ይኸንን፡ የተቀደሰ፡ የጥሪ፡ መልዕክት፡ አዋጅ፡ በማክበር፡ ለኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ መሠረታዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ ዲሞክራሲያዊ፡ ልዕልና፡ በአርበኞቻችን፡ የአንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ ቆራጥ፡ የኅብረት፡ ትግል፡ ሙሉ፡ ተሳትፎ፡ የሚያስገኘውን፡ የኢትዮጵያን፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥትህን፡ እስከ፡ አቆምክ፡ ድረስ፡

ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ በአንድነት!

በሚል፡ መፈክር፡ ተባብረህ፡ ተነስ! ገናናዋ፡ ኢትዮጵያ፡ ሃገራችን፡ ብሔራዊ፡ ግዳጃችሁን፡ በአክብሮት፡ ትጠይቃለች፡፡

በዲሞክራሲያዊው፡ የነፃነትህ፡ መብት፡ ማንኛቸውም፡ ኢትዮጵያዊ፡ ብሔረሰብ፡ የፈቀደበት፡ ለመኖር፡ ለመሥራት፡ ለመዘዋወር፡ ለመሰብሰብ፡ ለመመሥረት፡ በነፃ፡ መብቱ፡ በእኩልነት፡ በሰላም፡ በራሱ፡ ፍላጐትና፡ ጥረት፡ ዳግም፡ ንብረቱን፡ እርስቱን፡ ንግዱን፡ ለማዳበር፡ ለመግዛት፡ ለመሸጥ፡ ለመለወጥ፡ ለማቅረብ፡ ለመላክ፡ እንዲሁም፡ ለመጠቀም፡ ለማውረስ፡ ለመስጠት፡ በሕግ፡ ፍፁም፡ የተከበረለት፡ የሕይወቱን፡ ኑሮ፡ ደረጃ፡ ለማሻሻል፡ ለመበልፀግ፡ የማይለየው፡ ሰብአዊ፡ ነፃነታዊ፡ መብቱ፡ ነው፡፡

እንዲሁም፡ ለመናገር፡ ለመፃፍ፡ ለመምረጥ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የብዙሃን፡ የፖለቲካ፡ ፓርቲ፡ ውስጥ፡ ካለአንዳች፡ ተጽዕኖ፡ እኩል፡ ለመሳተፍ፡ በቋንቋው፡ በሃይማኖቱ፡ በባሕሉ፡ ከበሬታ፡ ቤተሰቡን፡ ትውልዱን፡ ብሔሩን፡ ኅብረተ፡ ብሔሩን፡ በሰላም፡ ለማቆምና፡ ለመደገፍ፡ ሁሉ፡ የማይሻር፡ ቋሚ፡ መብቱና፡ መሠረታዊ፡ ነፃነቱ፡ ሲሆን፤

በነፃነታዊ፡ መብት፡ በአንድነት፡ ሥርዓት፡ የሚጸናው፡ የሕዝብ፡ መንግሥት፡ ሃላፊነት፡ አቅማቸው፡ ወይም፡ ጤናቸው፡ የታወከ፡ ለተጥዋሪ፡ ዕድሜ፡ ለደረሱት፡ ሥራ፡ ላጡት፡ ሁሉ፡ ሙሉ፡ ክብካቤ፡ በማድረግ፡ የብሔረሰቡን፡ ጤና፡ የትምህርት፡ ዕድል፡ የፍትህ፡ ሥርዓትና፡ ሰብዓዊ፡ መብቱን፡ በመጠበቅና፡ በማስገኘት፡ ነፃ፡ የሆነውን፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔረ፡ ሰብአዊነቱን፡ ዓላማ፡ ያስከብራል፡፡

እንግዲህ፡ የነፃነት፡ መብት፡ ዋጋው፡ የሚታወቀው፡ አስተውሎ፡ በቅድሚያ፡ ላላመዛዘነው፡ ሲታጣ፡ ሲከለከል፡ በልዩ፡ ፍቃድ፡ በአምባ፡ ገነናዊ፡ የሥልጣን፡ ቀማኞች፡ ሲጫረቱባት፡ መሆኑን፡ ተረዳኸው፡፡

የግፉ፡ ግፍ፡ ልጅህን፡ አባትህን፡ እንዲሁም፡ ወገንህን፡ በፀሎተ፡ ቅዳሴ፡ አስፈትተህ፡ ለመቅበር፡ እንኳን፡ ስትከለከል፡ አዝነህ፡ ለማልቀስ፡ ስትሸማቀቅ፡ ታዲያ፡ ሌላ፡ ምን፡ ቀረህ? የኢትዮጵያችንን፡ ነፃነታዊ፡ መብት፡ በአድማ፡ ጠልፎ፡ የአንድነት፡ ዲሞክራሲያዊ፡ መፍትሔዋን፡ በእውነተኛ፡ ሰላማዊ፡ የፍትህ፡ መንገድ፡ እንዳመሻት፡ በጦርና፡ በግድያ፡ ብቻ፡ እየማገዳት፡ በማይጠፋ፡ እሳት፡ ብዙሃን፡ ወገኖቻችን፡ ኢትዮጵያውያንን፡ አስጨረሳቸው፡፡ ጉበዝ! ኢትዮጵያችንን፡ ከመቃብሯ፡ አፋፍ፡ ያደረስዋትን፡ የጦርህ፡ ኃይል፡ አዛዦች፡ ነን፡ እያሉ፡ አዝማቾችህንም፡ ጭምር፡ የራሳቸውን፡ ስሕተቶች፡ ለመሸፈን፡ በየጊዜው፡ በማፈን፡ የራሳቸውን፡ ውድቀት፡ በትምክህተኛነታቸው፡ ብዛት፡ ፈጽሞ፡ የማያምኑትን፡ ጥጋበኛ፡ ደመኞችህን፡ መጀመሪያ፡ ከነ፡ ግብረ፡ አበሮቻቸው፡ አስወግደህ፡ ስመ፡ ጥሩና፡ ታማኝ፡ የጉበዝ፡ አለቃ፡ አዛዦችህን፡ አቁመህ፡ ይህንን፡ እሳት፡ በገናናው፡ የአንድነተህ፡ ኃይል፡ ማዳፈን፡ አለብህ! አለበለዚያ፡ አንተም፡ ብዙ፡ ጥፋት፡ ሳያቋርጥ፡ ይደርስብሃል፡፡ ላድር፡ ባይነትም፡ ትርፉ፡ የቁም፡ ሞት፡ ነውና፡ በተራህ፡ ሳትሞት፡ ሳትወረስ፡ ወገኔ፡ ሆይ፡ ተነስ!

አንተስ፡ ስንቴ፡ ትሞታለህ? እስከ፡ ስንት፡ ግዜስ፡ ትጨነቃለህ?

ቆርጠህ፡ በመነሳት፡ ስምህን፡ አስከብር፡ አረመኔዎች፡ ጭራሹን፡ አያጥፉህ! የምትወዳትን፡ አገርህን፡ ኢትዮጵያችንን፡ ጭራሹን፡ አያውድሟት፡ ነፃነት፡ ማለት፡ ወደህ ስትመርጥ፡ ነውና፡ ታዲያስ፡ ወገኔ፡ ምን፡ ትመራጣለህ? ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብትህን፡ በአንድነት፡ እንዳምትመርጥ፡ አንጠራጠርም፡፡

ገናናው፡ ወገኔ! የጐበዝ፡ አለቃህን፡ መርጠህ፡ እነኚህን፡ ነፍሰ፡ ገዳዮቹን፡ እጅ፡ እጁን፡ ይዘህ፡ ለኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ትክክለኛ፡ ፍርድ፡ አቁማቸው፡፡ አይምሽብህ! የገናናው፡ ታሪክህ፡ ባለቤት፡ የሕዝባችን፡ ነፃነታዊ፡ መብት፡ አለኝታ፡ ያለኸው፡ አንተው፡ ወገኔ፡ ነህና፡ በአምላካችን፡ ኃይል፡ ፅኑ፡ እምነት፡ በኅብረትህ፡ ቆመህ፡ በአንድነትህ፡ ሕልውና፡ ከሕዝባችን፡ ሠራዊት፡ ጋር፡ በትግላችን፡ ተባበር! የእያንዳንዱ፡ ኢትዮጵያውያን፡ መብት፡ ሰላሙንና፡ ነፃነቱን፡ በአንድነትህ፡ አስከብር፡፡ አይዞህ፡ የሃገሬ፡ ጐበዝ፡ ምንም፡ አይጎልብህም፡ በትውልዳችን፡ ፍቅርና፡ ቆራጥ፡ መስዋዕትነት፡ በሚገኘው፡ የነፃነት፡ ዲሞክራሲያዊ፡ ጸጋ፡ እኩል፡ ለመሳተፍ፡ ከጆግኖቹ፡ ወገኖችህ፡ ጋር፡ አብረህ፡ ተሰለፍ፡፡

ለዲሞክራሲያዊት፡ ኢትዮጵያ፣ ለሕዝባችን፡ ነፃነታዊ፡ መብት፡ ልዕልና፡ የአርበኞቻችን፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ ሕዝባዊ፡ ሠራዊት፡ ኅብረት፣ በታሪካችን፡ ቅርስ፡ ከበሬታ፣ የጀግኖቻችን፡ ልጆች፡ ስመ፡ ጥሩው፡ ገናናው፡ ወገናችን፡ ይትረፍ!

የጀመርነውን፡ የተቀደሰ፡ የአርበኞቻችን፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ የኅብረት፡ ትግል፣ መልካም፡ ፍጻሜ፡ ያገኝ፡ ዘንድ፣ ኃያሉ፡ የኢትዮጵያ፡ አምላክ፡ ይርዳን፡፡

"እምነትህ፡ በእግዚአብሔር፡ ይሆን፡ ዘንድ፣
ለአንተ፡ ዛሬ፡ እነሆ፡ አስታወቅሁህ፡፡"

መ፡ ም፡ ፳፪/፲፱፡፡

መ ብ ት
አንድነት
SOLIDARITY
Liberty In Our Nation
RIGHT



ለዲሞክራሲያዊት፡ ኢትዮጵያችን፤

መልካም፡ "የኅብረት፡ ቀን" !

መጋቢት፡ ፳፰፡ ቀን፡፡

ግርማዊ ቀዳማዊ አምሃ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

ለኢትዮጵያ ኅብረተ ብሔር (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ የዘውድ መንግሥት

የበላይ ጠባቂ

ግርማዊ፡ ቀዳማዊ፡ አምሃ፡ ሥላሴ፤
ሞዓ፡ አንበሳ፡ ዘእምነገደ፡ ይሁዳ፡
ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ዘኢትዮጵያ፤
የጦር፡ ኃይሎች፡ ጠቅላይ፡ አዛዥ፡፡

ግርማዊት፡ እቴጌ፡ መድፈሪያሽ፡ ወርቅ፤
የዘውድ፡ ምክር፡ ቤት፡ የክብር፡ ፕሬዚዳንት፡፡

መብት

አንድነት

Liberty In Our Nation

ግርማዊት እቴጌ መድፈሪያሽ ወርቅ

መብት

አንድነት

Liberty In Our Nation

ልዑል ዘርአ ያዕቆብ አምሃ ሥላሴ

የኢትዮጵያ ን ነ መንግሥት አልጋ ወራሽ ።

ግርማዊ ቀዳማዊ አምሃ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

ለኢትዮጵያ ኅብረተ ብሔር (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ የዘውድ መንግሥት

የበላይ ጠባቂ

ዘርያዕቆብ፡ኣስፋ፡ወሰን

ልዑል፡ ዘርአ፡ ያዕቆብ፡ አምሃ፡ ሥላሴ፣
የኢትዮጵያ፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡ መንግሥት፡
አልጋ፡ ወራሽ፡
ተጠባባቂ፡ የጦር፡ ኃይሎች፡ ጠቅላይ፡ አዛዥ፡፡

ማርያም፡ ስና፡ አስፋ፡ ወሰን።

ልዕልት፡ ማርያም፡ ስና፡ አስፋ፡ ወሰን፣
የዘውድ፡ ምክር፡ ቤት፡ ሰብሳቢ፡ ዳኛ፡፡

መብት

አንድነት

Liberty In Our Nation

ልዕልት፡ ማርያም፡ ስና፡ አስፋ፡ ወሰን፣
የዘውድ፡ ምክር፡ ቤት፡ ሰብሳቢ፡ ዳኛ፡፡

ግርማዊ ቀዳማዊ አምሃ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

ለኢትዮጵያ ኅብረተ ብሔር (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ የዘውድ መንግሥት

የበላይ ጠባቂ

ሹመት፡፡

እኛ፡ ግርማዊ፡ ቀዳማዊ፡ አምሃ፡ ሥላሴ፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ዘኢትዮጵያ፡ የጦር፡ ኃይሎች፡ ጠቅላይ፡ አዛዥ፡ ባለቤታችን፡ እቴጌ፡ መድፈሪያሽ፡ ወርቅ፡ የዘውድ፡ ምክር፡ ቤታችን፡ የክብር፡ ፕሬዚዳንት፡ ልጃችን፡ አልጋ፡ ወራሻችን፡ ልዑል፡ ዘረአ፡ ያዕቆብ፡ አምሃ፡ ሥላሴ፡ የጦር፡ ኃይላችን፡ ተጠባባቂ፡ ጠቅላይ፡ አዛዥ፡ እንዲሁም፡ የዘውድ፡ ምክር፡ ቤታችን፡ ሰብሳቢ፡ ዳኛና፡ ርዕሳነ፡ መማክርት፡ ልዩ፡ እንደራሴውና፡ የልዩ፡ ካቢኔአችን፡ አባሎች፡ በተገኙበት፤

ዛሬ፡ የካቲት፡ ፳፯፡ ቀን፡ ፲፱፻፹ ዓ፡ም፡ በዘውድ፡ ምክር፡ ቤታችንና፡ በተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ ርዕሳነ፡ መማክርት፡ አሳሳቢነት፡ የውሳኔ፡ ቁጥር፡ ፲፪/፮/፲፱፻፹/ መሠረትና፡ በሕግ፡ መንግሥታዊ፡ የንጉሠ፡ ነገሥት፡ ሥልጣናችን፡ ምዕራፍ፡ ፩፡ አንቀጽ፡ ፳፱ እና፡ ፴፮ ቁጥር፡ መሠረት፡ በመከላከል፡ የጦር፡ አዋጅ፡ አጽድቀን፡ በአንቀጽ፡ ፫/ሀ፡ በአወጅነው፡ የልዩ፡ ካቢኔ፡ አስተዳደር፡ ሥርዓት፡ መሠረት፡

በልዩ፡ እንዳራሴአችን፡ አማካኝ፡ የቀረበልንን፡ ባለሥልጣኖችና፡ ከፍተኛ፡ ኃላፊዎች፡ በተዘረዘሩት፡ የሥራ፡ ክፍሎች፡ ትይዩ፡ እንዲቋቋሙ፡ ባዘዝነው፡ እርምጃ፡ መሠረት፡ ለንጉሠ፡ ነገሥቱ፡ ታማኝ፡ መሆናኘውን፡ ፊታችን፡ ቀርበው፡ በመሃላ፡ ያረጋገጡልንን፡

በምንወዳት፡በኢትዮጵያ፡ ሃገራችንና፡ ለኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ የዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፡ የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኞች፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ ሕዝባዊ፡ ሠራዊት፡ የኀብረት፡ እንቅስቃሴ፡ ስም፡ ኃያሉ፡ አምላክ፡ የተቀደሰውን፡ ብሔራዊ፡ ተግባራችንን፡ እንዲባርክልን፡ በመማፀን፡ ከልባችን፡ በማመስገን፡ ወደን፡ ሹመናል፡፡

በዚሁ፡ ውሳኔ፡ መሠረት፡ የንጉሠ፡ ነገሥቱ፡ ልዩ፡ ካቢኔው፡ ከፍተኛ፡ አስፈጻሚነት፡ ሥልጣን፡ ሲኖረው፡ ልዩ፡ እንዳራሴአችን፡ በሙሉ፡ ኃላፊነት፡ ሥራውን፡ ይመራል፡፡ ዝርዝር፡ የሹመት፡ ደብዳቤዎችንም፡ በማቅረብና፡ በማጽደቅ፡ ተገቢውን፡ ማዐረግና፡ ሃላፊነት፡ ይሰጣል፡፡

በቁጥር፡ ቃል፡ አንቀጽ፡ ፫/ሀ፡ ፲፪፡ ዋና፡ ዋናዎቹ፡ የካቢኔው፡ የሥራ፡ ክፍል፡ ተከፍተው፡ ዛሬ፡ ሰባት፡ የበላይ፡ ሹማምንት፡ የመሃላ፡ ሥርዓታቸውን፡ ፈጽመዋል፡፡ ዝርዝሩን፡ በቁጥር፡ ቃል፡ ፳፬/፯/፷፡ የንጉሠ፡ ነገሥት፡ ትዕዛዝ፡ ፫/ ቁጥር፡ አዋጃችን፡ ተመልከት፡፡

የመመሪያው፡ አዋጅ፡
ይዘት፡ ማውጫ፡፡

- መግቢያ፡ ስለ፡ የኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል፡) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት፡ መቋቋም፡ ውሳኔ፡ አቋም፤

- ስለ፡ ዘውድ፡ አወራረስ፡ ስለ፡ የንግሥና፡ ሥርዓት፡ አፈፃፀም፡ ውሳኔ፤

- ስለ፡ የዘውድ፡ ምክር፡ ቤት፡ በቋሚ፡ ርዕሰ፡ መማክርት፡ መመሥረትና፡ ዓመታዊ፡ የመብት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት፡ ጉባዔ፡ (ኮንግሬስ) መጠራት፡

- ስለ፡ የክብርና፡ የማዕርግ፡ ስም፡ የክብር፡ ኒሻን፡ መሾምና፡ መሸለም፡ እንዲሁም፡ "የጀግኖች፡ የክብርና፡ የሹመት፡ ልዩ፡ ማኅደር፡" ማቀናበር፡

- ስለ፡ የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡ መብት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤትና፡ ርዕሳነ፡ መማክርት፡ ባስገኙት፡ የአርበኞች፡ አንድነት፡ የትብብር፡ ጦር፡ ኃይል፡ የውል፡ ስምምነት፡ በከፍተኛ፡ ደረጃ፡ ስለልዩ፡ ካቢኔው፡ መቋቋም፡

- ልዩ፡ ካቢኔው፡ የርዕሰ፡ ብሔሩን፡ እንደራሴዎችና፡ አምባሳደሮች፡ በየሃገሩ፡ በመሾም፡ የጽሕፈት፡ ቤቶችና፡ ቆንሲላዎች፡ ስለመክፈት፡

- ስለ፡ "ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ በአንድነት" ዓላማ፡ ደጋፊዎች፡ በኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ የ"መብት፡" አምድ፡ ቅርንጫፎችና፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የሕዝብ፡ ድርጅቶች፡ መደራጀት፡

- ስለ፡ ቅዱስ፡ ሲኖዶስ፡ ነፃ፡ ጉባዔ፡ እንዲካሄድ፡ ትዕዛዝ፡

- ስለ፡ ነፃ፡ "የጠቅላላ፡ የሕዝብ፡ ምርጫ፡ ወሳኙነት፡" የተላለፈ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የኅብረት፡ ጥሪ፡

- ስለ፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፡

"የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኞች፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡" እና፡ "የአንድነት፡" አምዶች፡ በሃገር፡ ቤት፡ ተዘርግተው፡ በጠቅላይ፡ የጦር፡ ኃይል፡ መምሪያ፡ ትዕዛዝ፡ በሕዝባዊ፡ ሠራዊት፡ ሂደት፡ ስለመደራጀት፡

- የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኞች፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ ሠራዊት፡ ሕዝባዊነቱን፡ በማረጋገጥ፡ ኢትዮጵያውያን፡ ሁሉ፡ የጦሩ፡ ኃይል፡ ባልደረባ፡ እንደመሆናቸውና፡ ለኢትዮጵያ፡ የአንድነት፡ ሕልውና፡ በመቆም፡ ለኅብረተ፡ ብሔራቸው፡ በዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብታቸው፡ ልዕልና፡ እንዲመሠረቱ፡ የተሰጠ፡ ጥሪ፡

- ስለ፡ ንቅናቄው፡ እርዳታና፡ ድጋፍ፡ መሰባሰብና፡ የቁጥጥር፡ ሥርዓት፡ መቆም፡

- ስለ፡ ጠቅላይ፡ ኦዲተር፡ ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡ ሥልጣንና፡ ድርጅታዊ፡ ሥርዓት፡

- ስለ፡ ሥነ፡ ሥርዓትና፡ የዲሲፕሊን፡ ጥበቃ፡ "የጥቁር፡ አንበሳ፡" ሕግ፡ አስተነባባሪዎች፡ ልዩ፡ የቴክኒክ፡ አምድ፡ ክፍል፡ የክብር፡ ኃይል፡ ኮከቦች፡ ማቋቋምና፡ መደራጀት፤

- ስለ፡ የመብት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት፡ ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡የአስተባባሪ፡ተግባሮቹንና፡ማንኛቸውንም፡የጽሕፈት፡ ቤቶች፡ቁሳቁስና፡ተፈላጊውን፡መመሪያ፡ የመስጠት፡ ኃላፊነት፡

- ስለ፡ ሕዝብና፡ ድርጅታዊ፡ አካሎች፡ በአንድ፡ ዲሲፕሊን፡ አመራር፡ ሥነ፡ ሥርዓት፡ መደራጀት፡

- ስለ፡ ጠቅላላ፡ ጉባዔና፡ ልዩ፡ ስብሰባዎች፡ መቀናበር፡

- ስለ፡ ርዕሰ፡ ብሔሩ፡ ጥበቃ፡ ስለ፡ ዘውድ፡ ምክር፡ ቤት፡ ልዩ፡ ካቢኔና፡ የጦር፡ ኃይል፡ መምሪያ፡ ድርጅታዊ፡ ሎጂስቲክስ፡ መሟላት፡

- ስለ፡ ቋሚ፡ ሠራተኞች፡ መተዳደሪያ፡ ደንብና፡ ስለዲሲፕሊን፡ ማስከበር፡

- ስለ፡ በጐ፡ አድራጐት፡ ማእከላዊ፡ ድርጅት፡ የ"ታቀፍ፡" ፋውንዴሽን፡ መቀናበርና፡ ስለ፡ የኢትዮጵያ፡ የጥናት፡ አካዳሚ፡ መቋቋም፡

- ስለ፡ ዓለም፡ አቀፍ፡ የጥቁር፡ አፍሪካ፡ ተወላጆች፡ ድጋፍ፡ መደራጀት፡

- ስለ፡ "ነፃነታዊ፡ መብት፡ በአንድነት፡" መጽሔት፡ መደራጀት፡

- ስለ፡ ጠቅላላ፡ የሥራ፡ አመራር፡ ምስጢራዊ፡ ስትራተጂ፡ አያያዝና፡ መመሪያ፡ ሕጐች፡

- ስለ፡ ንብረቶች፡ ሕጋዊ፡ አካልና፡ ጥቅም፡ በፋውንዴሽኑ፡ ባለአደራነት፡ ለኢትዮጵያውያን፡ ፍፁም፡ ዲሞክራሲያዊና፡ ባሕላዊ፡ ጥቅም፡ ብቻ፡ እንዲውሉ፡ የተደረገው፡ ውሳኔ፡

- ስለ፡ ነጋሪት፡ ጋዜጣና፡ ልዩ፡ መግለጫዎች፡ መጠበቅ፡

- ስለ: ግርማዊ: ቀዳማዊ: አምሃ: ሥላሴ: ሞዓ: አንበሳ: ዘእምነገደ: ይሁዳ: ንጉሠ: ነገሥት: ዘኢትዮጵያ: የተቀደሰ: የጥሪ: መልዕክት: አዋጅ:

- ስለ: ካቢኔውና: የከፍተኛ: ባለሥልጣኖች: መሾምና: ቋሚ: መሥሪያ: ቤቶች: መደራጀት::

O

ግርማዊ ቀዳማዊ አምሃ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ፡፡

ለኢትዮጵያ ኅብረተ ብሔር (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ የዘውድ መንግሥት

የበላይ ጠባቂ



ለማንኛውም ግንኙነት መለስተኛ የአድራሻ ማስታወቂያ፤
SHORT MAILING LIST

ግቢ፤
"CHANCERY" - 82 PORTLAND PLACE,
SUITE 0,
LONDON W 1.
ENGLAND - U.K.

"መብት"፤ P.O.BOX. 360,
"RIGHT" - CROYDON CR9-6JX,
ENGLAND - U.K.

"ታቀፍ"-
"TACEF"- 89 CEDAR RD.,
CROYDON CR0-6UJ.,
ENGLAND - U.K.

የምዕራብ እዝ አምዶች፤ WESTERN BRANCH COLUMNS.

P.O.BOX. 980,
215 WEST 104 ST.,
NEW YORK N.Y. 10025,
U.S.A.

P.O.BOX. 523,
OXON HILL,
MARYLAND 20745,
U.S.A.

1223, WILSHIRE BL.,
SUITE 188, SANTA MONICA,
CA. 90403 U.S.A.

91, COSBURN AVE.,
SUITE 804, TORONTO,
ONTARIO M4K-2G2.

"አንድነት"
በ"ጠቅላይ መምሪያ" በኩል፤

"UNITY"
THROUGH "HIGH COMMAND".

መ ዝ ት

አንድነት

SOLIDARITY

Liberty In Our Nation

RIGHT

ለኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት፣
የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፣
የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ አንድነት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት፣
ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡፡

የሕዝባችንን፡ ሞራል፡ ለመስበርና፡ በፋሽስት፡ የኮሙኒስት፡ ቅጥረኞች፡ አረመኔ፡ በትር፡ ኢትዮጵያችንን፡ ምሳሌና፡ መቀጣጫ፡ እንድትሆን፡ በአደባባይ፡ ምስጢር፡ ሁሉም፡ አድመውብሃልና፡ የሃገሬ፡ ጐበዝ!

በሃያሉ፡ የኢትዮጵያ፡ አምላካችን፡ እምነት፡ ፀንተህ፡ ከጥንት፡ ታሪካችን፡ ጊዜ፡ ጀምሮ፡ በፈሰሰውና፡ በተከሰከሰው፡ የጀግናዎቹ፡ አባቶቻችንና፡ እናቶቻችን፡ ደምና፡ አጥንት፡ በኢትዮጵያዊነትህ፡ ታላቅነትና፡ ክብር፡ ኮርተህ፡ በመቆም፡ በራስህ፡ ብቻ፡ በመተማመን፡ አንተው፡ የውስጥ፡ ጠላትህን፡ በገዛ፡ እጅህ፡ አውድመህ፡ ባለህ፡ የደሃ፡ አቅምህም፡ ቢሆን፡ ለዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነትህ፡ መብት፡ በአንድነትህ፡ ኃይል፡ እምነት፡ አብረህ፡ ከህዝባችን፡ ጋር፡ ጠንክረህ፡ ከቆምክ፡ እራስህንና፡ ታሪክህን፡ ካለማንም፡ ረዳት፡ ታስከብራለህና፡ አይዞህ፡ ጐበዝ! ቅስምህንና፡ ወኔህን፡ አይሰበሩት፤

የጀግና፡ ሕዝብ፡ ትውልድ፡ ነህና፡ ተነስ! ተባበር! ተጋገዝ! በያለህበት፡ ተማምለህ፡ ኢትዮጵያዊ፡ ግዳጅህን፡ ፈጽም! ሃያሉ፡ የኢትያጵያ፡ አምላክ፡ ወገንህ፡ ነውና፡ ካለጥርጥር፡ ቀጣፊዎቹንና፡ላድርባዮቹንም፡ ጭምር፡ ታቸንፋለህ! ተነስ፡ የሃገሬ፡ ጐበዝ፡ መክት!

RIGHT

ለኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት፣
የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፣
የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ አንድነት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት፣
ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡፡

ረ) የሚሰቃየውም፡ የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡ ወገንህ፡ነውና፡ እዘን፤ እጅህንም፡ ከወገንህ፡ ከሕዝቡ፡ ላይ፡ አንሳ፡ ይብቃህ! የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ እርግጠኛ፡ ፍጹም፡ የነፃነት፡ ምሥራች፡ የአንተም፡ ስለሆነ፡ በጀግናው፡ የኢትዮጵያዊነትህ፡ መንፈስ፡ ተባብረህ፡ ተነስ! ለኢትዮጵያ፡ ብለው፡ የሚሞቱትን፡የተረፉትን፡ አለቆችህንም፡ ፈጽሞ፡ በተራ፡ በተራ፡ በወንበዴዎቹ፡ መሠረታዊ፡ የአመራር፡ ውድቀት፡ ምክንያትና፡ የዘወትር፡ ሰበብ፡ ጨርሶ፡ ሳያጠፏቸው፡ በተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኞች፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ ሕዝባዊ፡ ሠራዊት፡ አንድነት፡ ስም፡ የጐበዝ፡ አለቆችህን፡ በሥርዓት፡ መርጠህና፡ ደግፈህ፡ በማቆም፡ ከሕዝባችን፡ ጋር፡ በመዋሀድ፡ በአንድነት፡ ተባብረህ፡ ተነስ!

ለኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ታማኝነትህን፡ በማስመስከር፡ በቍርጠኛ፡ ብሔራዊ፡ ግዳጅህ፡ የተቀደሰ፡ "ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ በአንድነት"፡ ተግባርህን፡ በቶሎ፡ አሳውቀን!

ገናናው፡ ጀግና፡ የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡ ወገኔ፡ አለሁ፡ በለኝ!

ለኢትዮጵያችን፡ ቋሚ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነትዋ፡ መብት፡ ልምላሜ፡ ለኅብረተ፡ ብሔራችን፡ የአንድነት፡ ሕልውና፡ ሙትላት፡ እንጂ፡ ፈጽሞ፡ ለመጥፊያዋ፡ ምክንያት፡ አትሁን፡

RIGHT

ለኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት፤
የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፤
የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ አንድነት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት፤
ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡፡

በገናናው፡ ታሪክህ፡ ሙሉ፡ እምነት፡ ተነስ! የነፃነትህን፡ መብት፡ የዲሞክራሲያዊ፡ ልዕልናህን፡ ለማስከበር፡ ከተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኞች፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ ሕዝባዊ፡ ሠራዊት፡ ጋር፡ የተቀደሰ፡ ብሔራዊ፡ ግዳጅህን፡ ለመፈጸም፡ ጐን፡ ለጐን፡ አብረህ፡ በመቆም፡ በአንድነት፡ ተሰለፍ፡፡ ሕዝባችንና፡ የጦር፡ ሠራዊቱ፡ አንድ፡ አካል፡ ስለሆነ፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ በዲሞክራሲያዊ፡ ነፃ፡ ሥርዓቱ፡ ሕዝቡን፡ የማስተዳደሪያ፡ ሕገ፡ መንግሥቱን፡ በፈቃዱ፡ እስከአቆመ፡ ድረስ፡ በምንም፡ ሁኔታ፡ ወይም፡ ሰበብ፡ ሳትነጣጠል፡ በማንኛቸውም፡ ጊዜ፡ አንድ፡ ላይ፡ በኅብረት፡ ቆመህ፡ የሕዝባችንን፡ የነፃነት፡ ትግል፡ ጽዋ፡ አብረህ፡ ተካፈል!

ሰ) እውነትስ፡ ከሆነ፡ መንተ፡ ህፍረት፡ እንኳን፡ በሌለው፡ ፍፁም፡ የሀሰት፡ ወንጀል፡ ትልቁን፡ የኢትዮጵያን፡ ባለውለታ፡ ግርማዊ፡ ቀዳማዊ፡ ኃይለ፡ ሥላሴ፡ ክርስቲያኑን፡ አባታችንን፡ የተመፃደቁባቸው፡ የግፍ፡ ግፍ፡ በደል፡ ቀርቶ፤ ዛሬ፡ ይሉኝታ፡ እንኳን፡ የሚባል፡ ገደብ፡ በሌለው፡ አምባ፡ ገነናዊ፡ የፈላጭ፡ ቆራጭ፡ የወንበዴነት፡ ሥልጣናቸው፡ በወታደሩ፡ ኃይልና፡ ድጋፍ፡ በየሰበቡ፡ አማሃኝተው፡ በጉልበታቸው፡ በወረሱትና፡

መብት

አንድነት

SOLIDARITY

Liberty In Our Nation

RIGHT

ለኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት፣
የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፣
የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ አንድነት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት፣
ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡፡

በዘረፉት፡ በደሀው፡ የኢትዮጵያውያን፡ የግል፡ ሀብት፡ የሚንደላቀቁትና፤ በማን፡ አለኝህነት፡ በጠመንጃ፡ አፈሙዝ፡ እያስፈራሩ፡ የሕዝባችንን፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነቱን፡ መብትና፡ የአንድነቱን፡ ሕልውና፡ በብቸኝነት፡ ሂደት፡ በዱሮው፡ የፋሽስቶች፡ ካኪ፡ ዩኒፎርም፡ የሚያፌዙብህ፡ አንሶአቸው፡

እነኚህ፡ የኢትዮጵያንና፡ የወገንህን፡ ሕይወት፡ ሰላሙንና፡ የእድገት፡ እርምጃውን፡ አጥፊዎች፡ በራስ፡ መስካሪነት፡ አሁን፡ ገና፡ ባደባባይ፡ በይፋ፡ ታውቆ፡ በተጋለጠው፡ ስርቆታቸው፡ በወኪሎቻቸው፡ የእጅ፡ አዙር፡ ስውር፡ ሥርዓት፡ አማካይ፡

ሠራተኛውና፡ ድሀው፡ በስንት፡ ዓመታት፡ ልፋትና፡ ጥረት፡ ደም፡ ተፍቶ፡ ጥሮ፡ ግሮ፡ ያፈራውን፡ ሀብት፡ በየሰበቡ፡ ዘርፈውና፤ እንዲሁም፡ ለተቸገረው፡ ህዝባችን፡ የተዋጣውን፡ የምዕራብ፡ ሃገር፡ እርዳታ፡ በየጊዜው፡ አግበስብሰው፡ በባዕድ፡ ሀገር፡ በማሸሸ፤ ቀድመው፡ ባሰናዱት፡ በጥቅም፡ ግብረ፡ አበሮቻቸው፡ ምሬት፡ ካባ፡ ለውጠው፡ ለመቀማጠል፡ ኮብልለው፡ ጨርሰው፡ ሳያመልጡህ፡ በቶሎ፡ ይዘህ፡ ቢያንስ፡ ቢያንስ፡ ለትክክለኛው፡ የሕዝብ፡ ፍርድ፡ አቅርባቸው፡፡

መብት
አንድነት
SOLIDARITY
Liberty In Our Nation

RIGHT

ለኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት።
የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ።
የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ አንድነት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት።
ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡፡

በተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኞች፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ ስም፡ በጦር፡ ኃይላችን፡ ሕዝባዊነት፡ ሥርዓት፡ ወታደሩና፡ የሲቪል፡ ሠራዊቱ፡ በእውነት፡ አንድ፡ አካል፡ ሆኖ፡ ለሰላም፡ ኑሮው፡ ግንባታና፡ ለአንድነቱ፡ የጋራ፡ መከታ፡ በመሆን፡ በፍትህ፡ በሰላምና፡ በኅብረት፡ ቆሞ፡ "በዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነቱ፡ መብት፡ ልዕልና፡ በአንድነት፡ የጦር፡ ኃይሉ፡ ኅብረት"፡ የትውልዱን፡ የረጅም፡ ግዜ፡ ጥቅምና፡ ብለጽግና፡ ለምስገኘትና፡ የኢትዮጵያን፡ ኅብረተ፡ ቢሔር፡ (ፌዴራል፡) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥትህን፡ በራስህ፡ ታሪክ፡ ከበሬታ፡ ለማጽናት፤
ታላቁ፡ እድል፡ አሁንም፡ በይበልጡኑ፡ የአንተው፡ ስለሆነ፡ ተጠቀምበት! መለዮ፡ ለባሹ፡ የሃገሬ፡ ጉበዝ፡ ሳታመነታ፡ በስርአትና፡ በቆራጥነት፡ በቶሎ፡ ለወገንህ፡ ድረስለት!

ሕዝባችንን፡ አርበኞቻችንን፡ ሠራተኛውን፡ ገበሬውን፡ ነጋዴውን፡ ምሁሩን፡ ወጣቱን፡ ጡረተኛውን፡ አዛውንቱን፡ የመንፈሳዊ፡ መምህሩን፡ የጉበዝ፡ አለቃውን፡ በጠቅላላው፡ ትውልዳችንን፡ ሁሉ፡ ተነስተህ፡ እርዳ! የሕዝባችንን፡ ሰላሙንና፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነቱን፡ መብት፡ መልስ! ገናናው፡ ስምህ፡ ይትረፍ!" በማለት፡

RIGHT

ለኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት፣
የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፣
የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ አንድነት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት፣
ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት::

፮ኛ፡ <u>ለዘለቄታውም፡ የኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት፡ በሕዝቡ፡ ፍፁም፡ ነፃ፡ ፍቃድና፡ ዲሞክራሲያዊ፡ ምርጫ፡ እስከተቋቋመ፡ ድረስ</u>፡ የተባበሩትን፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኞች፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ ሕዝባዊ፡ሠራዊትን፡ በኅብረትና፡በአንድ፡ መሠረታዊ፡ ዓላማ፡ በማስማማትና፡በማሰባሰብ፡ ገናናዋን፡ ኢትዮጵያችንን፡ ለማዳንና፡ የነፃነት፡ ትግሉን፡ በከፍተኛ፡ ደረጃ፡ ይመሩት፡ ዘንድ፡ ሙሉ፡ የበላይነት፡ ኃላፊነቱን፡ በመቀበል፡ በዘውድ፡ ምክር፡ ቤት፡ ከፍተኛ፡ አደራ፡ በፀደቀው፡ ውሳኔ፡ መሠረት፡ በተቀዳሚ፡
ሀ) ነጋሚው፡ ከዚህ፡ በፊት፡ በጥቅምት፡ ፳፫፡ ቀን፡ በ፲፱፻፳፫ ዓ፡ም፡ በቅባ፡ መንግሥት፡ ቁርባን፡ መሃላ፡ የፈፀሙበትን፡ ታሪካዊ፡ ሕገ፡ መንግሥታዊና፡ የተቀደሰ፡ ብሔራዊ፡ የዘውድ፡ ወራሴነታቸውን፡ ተግባር፡ በታላቅ፡ ኃላፊነት፡ ተቀብለው፡ ሙሉ፡ ሥርዓተ፡ ከበሬታውን፡ በሕገ፡ መንግሥቱ፡ ምዕራፍ፡ ፩፡አንቀጽ፡፩፡እስከ፡፳፫፡መሠረት፡ በመፈፀም፡ ቅባ፡ መንግሥት፡ በመቀባት፡ በታላቅ፡ ኃላፊነት፡ ትግሉን፡ በኅብረት፡እንዲመሩት

በግርማዊ፡ ቀዳማዊ፡ አምሃ፡ ሥላሴ፡ ሥያሜ፡ በመጠራት፡ የንጉሠ፡ ነገሥቱን፡ ዘውድ፡ እንዲቀዳጁና፡

መ ብ ት

አንድነት

ነጻነት ለሕዝባችን
SOLIDARITY
Liberty In Our Nation

RIGHT

ለኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት፣ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፣ የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ አንድነት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት፣ ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡፡

ባለቤታቸው፡ ልዕልት፡ መድፈሪያሽ፡ ወርቅ፡ አበበም፡ የእቴጌነቱን፡የክብር፡ስምና፡ሙሉ፡የሹመት፡ሥርዓቱን፡በመቀበል፡

እንዲሁም፡ በቋሚው፡ ሕገ፡ መንግሥት፡ አንቀጽ፡ ምዕራፍ፡ ፩፡ እስከ፡ ፳፮፡ አንቀጽና፡ በተለይም፡ ስለዙፋኑ፡ የዘውድ፡ አወራረስ፡ በወጣው፡ የግርማዊ፡ ቀዳማዊ፡ ኃይለ፡ ሥላሴ፡ አዋጅ፡ ትዕዛዝ፡ ቁጥር፡ ፭፩/፲፱፻፷፮፡ መሠረት፡

ልዑል፡ ዘርአ፡ ያዕቆብ፡ አስፋ፡ ወሰን፡ የአልጋው፡ ተጠባባቂነት፡ የፀደቀላቸው፡ በሙሉ፡ የአልጋ፡ ወራሽነት፡ ሥልጣን፡ በመሾም፡ አብረው፡ ቅባ፡ መንግሥት፡ በመቀባትና፤

ሁሉም፡ ቃል፡ ኪዳናቸውን፡ በኢትዮጵያ፡ ታሪካችን፡ ሙሉ፡ ከበሬታ፡ ሥርዓት፡ በኢትዮጵያ፡ ኦርቶዶክስ፡ ተዋህዶ፡ ሃይማኖት፡ ሙሉ፡ እምነት፡ ፀንተው፡ ቃለ፡ መሃላቸውን፡ በመፈፀም፡ <u>መጋቢት፡</u> ፳፯፡ <u>ቀን፡</u> ፲፱፻፹<u>፡ ዓ፡ ም፡ የዘውድ፡ ምክር፡ ቤታቸውን፡ ታላቅ፡ ታሪካዊ፡ ውሳኔ፡ በከበሬታ፡ በማጽደቅ</u>፡ የዚህንም፡ መለስተኛ፡ ክብረ፡ በዓል፡ በተወሰነ፡ የሚያመች፡ ጊዜና፡ ሥፍራ፡ በኦፊሴል፡ እንዲያከብሩ፡ ሲወሰን፡

መብት
አንድነት
SOLIDARITY
Liberty In Our Nation

RIGHT

ለኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት፣
የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፣
የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ አንድነት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት፣
ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡፡

ለ) የንግሥና፡ ሥርዓታቸውን፡ ግን፡ ጃንሆይ፡ በተቀዳሚ፡ ነፃነቱንና፡ አንድነቱን፡ ወዳድ፡ ጀግናው፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ በመሠረታዊ፡ የነፃነት፡ መብቱ፡ በመጠቀም፡ ዲሞክራሲያዊ፡ ነፃ፡ ኑባሬዎቹን፡ አቁሞ፡ በሰላም፡ የነፃነቱን፡ አርማ፡ በሚቀዳጅበት፡ ዕለት፡ በኢትዮጵያ፡ አምላክ፡ ፍቃድና፡ ቸርነት፡ የንግሥና፡ ሥርዓቱን፡ በሃገራቸው፡ በኢትዮጵያ፡ መሬት፡ ላይ፡ ብሔራዊ፡ ተግባራቸውን፡ በሙሉ፡ ከበሬታ፡ እንፈጽማለን፡ በማለት፡ ግርማዊ፡ ቀዳማዊ፡ አምሃ፡ ሥላሴ፡ ሞዓ፡ አንበሳ፡ ዘእምነገደ፡ ድሁዳ፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ዘኢትዮጵያ፡ ንጉሣዊ፡ ቃላቸውን፡ ሰጥተዋል፡፡

ሐ) እስከዛውም፡ ድረስ፡ ለኢትዮጵያ፡ ሕዝብና፡ ለአርበኞችዋ፡ የአንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ ሕዝባዊ፡ ሠራዊት፡ ንቅናቄዎች፡ ጥቅም፡ ሙሉ፡ የንግሥና፡ የማዕርግ፡ ስማቸው፡ አዋጁ፡ ከወጣበት፡ ቀን፡ ጀምሮ፡ በከበሬታ፡ ሥርዓት፡ ለኢትዮጵያ፡ የአንድነት፡ አርማ፡ ሆኖ፡ እንዲሠራበት፡ በታላቅ፡ አክብሮት፡ ወደው፡ በመፍቀድ፡

መብት

አንድነት

SOLIDARITY

Liberty In Our Nation

RIGHT

ለኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት፣
የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፣
የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ አንድነት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት፣
ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡፡

መ) እንዲሁም፡ በጥንታዊት፡ ኢትዮጵያ፡ ገናናው፡ የጦር፡ ኃይል፡ ሕዝባዊ፡ ሠራዊት፡ ታሪክ፡ መሠረት፡ የክብር፡ ኮከብ፡ ምልክት፡ የነበረውን፡ የቅዱስ፡ ጊዮርጊስ፡ አርማቸውን፡ ለጦሩ፡ ኃይል፡ መምሪያና፡ ለተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኞች፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ አምድ፡ የሕዝብ፡ ሠራዊት፡ ሁሉ፡ መለያቸው፡ አርማና፡ የሰንደቅ፡ ዓላማቸው፡ ሆኖ፡ እንዲሠራበት፡ በከበሬታ፡ አዘዋል፡፡

ጂና፡ ግርማዊ፡ ቀዳማዊ፡ አምሃ፡ ሥላሴ፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ዘኢትዮጵያ፡ በመጀመሪያ፡ ንጉሣዊ፡ ትዕዛዛቸው፡ ግርማዊ፡ ቀዳማዊ፡ ኃይለ፡ ሥላሴ፡ አባታቸውን፡ ለኢትዮጵያ፡ በፋሺስት፡ ጦርነት፡ ግዜም፡ ሆነ፡ በረጅም፡ የሰላም፡ ንግሥና፡ ዘመናቸው፡ ለሃገራችን፡ ነፃነት፡ ሰላምና፡ አንድነት፡ ለሃይማኖት፡ ነፃነትና፡ የግል፡ ክብር፡ ለሕዝቡም፡ ታላቅ፡ የሥልጣኔ፡ እርምጃ፡ ውለታቸውና፡ በተለይም፡ ለዓለም፡ ፀጥታ፡ የኮሌክቲቭ፡ ሴኩሪቴ፡ ጥበቃና፡ ለአፍሪካ፡ የፀረ፡ ኮሎኒያሊስት፡ ብሔራዊ፡ የነፃነት፡ ትግልና፡ ለአፍሪካውያን፡ ትውልድ፡ ሰብዓዊ፡ መብት፡ የእኩልነት፡ ከበሬታ፡ ከዛም፡ በኅብረት፡ የአፍሪካን፡መንግሥታት፡በማሰባሰብ፡አንድነቱንና፡ እግዝዕናውን፡ ለመጠበቅ፡ ባደረጉት፡ ታላቅ፡ ጥረትና፡ መስተዋጽዖ፡

RIGHT

ለኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት፣
የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፣
የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ አንድነት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት፣
ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡፡

እንዲሁም፡ በአስታራቂነት፡መሪ፡ አባትነታቸው፡ የታወቁትን፡ ውድ፡ አባታቸውን፤

ሀ) ግርማዊ፡ ቀዳማዊ፡ "ታላቁ"፡ ኃይለ፡ ሥላሴ፡ ብለው፡ በክብር፡ የሹመት፡ ማዕርግ፡ በመሠየምና፡ በመጥራት፡ ስማቸውና፡ እውነተኛ፡ የተቀደሰ፡ መስዋዕትነታቸው፡ ተገቢውን፡ የኢትዮጵያ፡ ታሪክ፡ የክብር፡ ቦታ፡ እንዲይዝ፡ በታላቅ፡ አክብሮትና፡ ምስጋና፡ በገናናው፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብና፡ በተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኞች፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ የሕዝብ፡ ሠራዊታቸው፡ ስም፡ ሲያስታውቁ፡

ለ) ለዳግማዊ፡ ፋሽስቱ፡ ለአምባገነናውያን፡ ሕገ፡ ወጥ፡ ሴረኞች፡ አንገዛም፡ በማለት፡ እንደ፡ ጥንት፡ አባቶቻችንና፡ እናቶቻችን፡ የቆራጥነት፡ ጠባይ፡ በታላቅ፡ ጀግንነት፡ ለተሰዉትና፡ስቃይ፡ለተቀበሉት፡"ታላቅ፡ የኢትዮጵያ፡ ልጆች"፡ ወገኖቻችንና፡ለኢትዮጵያ፡ነፃነትና፡አንድነት፡ በጐጡና፡በዋሻው፡ በበረሃውና፡በጦር፡ሜዳው፡ እንዲሁም፡ በመኖርያ፡ ቤታቸውና፡ በሥራ፡ ገበታቸው፡ ሙሉ፡ መሥዋዕታቸውን፡ የከፈሉትንና፡

መብት

አንድነት

SOLIDARITY

Liberty In Our Nation

RIGHT

ለኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት፤
የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፤
የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ አንድነት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት፤
ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡፡

በኢትዮጵያ፡ ሰላማዊ፡ የፍትህ፡ ሥርዓት፡ ፍፁም፡ እምነት፡ በከፉ፡ ቀን፡ የወገናቸውን፡ ሕጋዊ፡ አመዛዛኝ፡ ሕሊና፡ በማመን፡ በሕግ፡ አከባሪነታቸው፡ ሳያምፁ፡ ካለፍርድ፡ በእሥር፡ ቤት፡ የተሰዉትን፡ የጠፉትንና፡ የተሰቃዩትን፡ ጀግኖች፡ ኢትዮጵያውያን፡ ወገኖቻችንና፡ ተሰደው፡ በባዕድ፡ ሃገር፡ የሞቱትና፡ የሚንከራተቱትን፡ ጉበዝ፡ሁሉ፡ በታላቅ፡ ከበሬታ፡ እንዲታወሱና፡እንዲከበሩ፡ መላው፡ ወገናቸውን፡ የኢትዮጵያን፡ ሕዝብ፡ በታላቅ፡ ከበሬታ፡ አሳስበዋል፡፡

ለዲሞክራሲያዊት፡ ኢትዮጵያችን፡ ለአንድነቷና፡ ለነፃነቷ፡ ሕልውና፡ ከበሬታ፡ በቆራጥነት፡ ላገለገሉትና፡ በተለይም፡ መስዋዕት፡ ለሆኑት፡ ጀግኖች፡ የኢትዮጵያ፡ ወገኖቻችንና፡ እንዲሁም፡ የኢትዮጵያ፡ ባለውለታዎችና፡ የጭንቀት፡ ግዜ፡ ወዳጆችዋ፡ ሁሉ፡ የስም፡ ዝርዝራቸው፡ በፕሮቶኮል፡ ማዕርግ፡ በከበሬታ፡ ታውቆ፡ በመመዝገብ፡ "የጀግኖች፡ የክብርና፡ የሹመት፡ ልዩ፡ ግህደር"፡ በወግና፡ በማዕርግ፡ ሙሉ፡ ታሪካዊ፡ ከበሬታው፡ ተሟልቶ፡ እንዲሠራበት፡ ታዟል፡፡

መብት

አንድነት

SOLIDARITY

Liberty In Our Nation

RIGHT

ለኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት፣
የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፣
የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ አንድነት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት፣
ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡፡

፭ኛ በ"ዲሞራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት በአንድነት፡" ዓላማ፡ የተሠለፉትን፡ የተባበሩትን፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኞች፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ ሕዝባዊ፡ ሠራዊት፡ የትግሉን፡ ምዕራፍ፡ በአዲስ፡ መንፈስ፡ ትዕዛዝ፡ በመክፈት፡ ለኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡የተቀደሰ፡የጥሪ፡መልዕክት፡ አዋጃቸውን፡ በማስተላለፍ፡

ሀ) መጋቢት፡ ፳፯፡ ቀን፡ የኢትዮጵያውያን፡ "የኅብረት፡ ቀን፡" ተብሎ፡ በመጠራት፡ በየአመቱ፡ በመላው፡ የኢትዮጵያውያን፡ ቤተሰብና፡ በኢትዮጵያ፡ ወዳጆች፡ ሁሉ፡ በሥርዓት፡ ተከብሮ፡ በመዋል፡ ለዲሞክራሲያዊት፡ ኢትዮጵያችን፡ የተቀደሰ፡ ዓላማ፡ ፅኑ፡ ኅብረታችንና፡ ፍፁም፡ ድጋፋችንን፡ በይፋ፡ በመግለጽ፡ የሰብዓዊና፡ የባሕል፡ ጠቀስ፡ የዕርዳታ፡ማስገኛ፡ሥራዎችን፡ በወር፡አንድ፡ ግዜ፡ በቅዳሜና፡ እሁድ፡ዕለቶች፡ በያለበት፡ እንዲካሄድ፡ በከበሬታ፡ሲያሳውቁ፤

ማንኛቸውም፡ አይነት፡ አምባገነናዊ፡ ግራም፡ ሆነ፡ ቀኝ፡ ክንፍ፡ፋሽስታዊ፡የብቸኝነት፡ አረመኔ፡ ሥርዓት፡ እስኪወድምና፡ ገናናው፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ በ"ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነቱ፡ መብት፡ በአንድነት፡" አላማው፡ ከበሬታ፡ በድል፡ አድራጊነት፡ የነፃነቱን፡ አርማ፡ እስተቀዳጀ፡ ድረስ፡ እየተደጋገመ፡ እንዲሠራበት፡ ኢትዮጵያውያን፡ ወገኖቻቸውን፡ በሙሉ፡ በከበሬታ፡ አሳስበዋል፤

መብት

አንድነት

SOLIDARITY

Liberty In Our Nation

RIGHT

ለኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት፣
የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፣
የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ አንድነት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት፣
ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡፡

ለ) እንዲሁም፡ የኢትዮጵያ፡ ወዳጆችንና፡ ለሕዝባችን፡ ደህንነትና፡ ጥቅም፡ ተቆርቋሪና፡ የነፃው፡ ዓለም፡ ኅብረተሰብ፡ ደጋፊዎች፡የተባሉትን፡የመንግሥት፡ኃላፊዎች፡ድርጅቶችና፡ ግለሰቦች፡ በሙሉ፡ እርዳታቸውን፡ ሲጠይቁ፡ የጊዜውን፡ አሳሳች፡ ሁኔታ፡ በማብራራት፡ ባጭሩ፡ ከዚህ፡ በታች፡ እንደተገለጠው፡ አሳስበዋል።

የዲሞክራሲያዊት፡ ኢትዮጵያችን፡ ደጋፊዎችና፡ ነፃነቱን፡ ወዳድ፡ የሕዝባችን፡ ወዳጆች፡ ሁሉ።

"ምንም፡ ሳታመነቱ፡ በሕዝባችን፡ ንጹሕ፡ ደም፡ የተጠመቁትን፡ በኮሚኒስት፡ ኢምፔሪያሊስት፡ የተጽእኖ፡ ቅጥረኞች፡ ኃይል፡ የኢትዮጵያን፡ ሕዝብ፡ አጥፊዎችና፡ ነፍሰ፡ ገዳዮች፡ የፈሪሃ፡ እግዚአብሔር፡ እምነትና፡ የሀገር፡ ፍቅር፡ በሌላቸው፡ በግል፡ ጥቅምና፡ በሥልጣን፡ ጥማት፡ ተሳክረው፡ በቂምና፡ በቀል፡ በከረረ፡ የርዕዮት፡ ማን፡ አለኝሀነት፡ አገራችንንና፡ ሕዝባችንን፡ ያወደሙትን፡ የሰብአዊ፡ ወንጀል፡ የፈጸሙትን፡ ፋሽስቶች፡ ዛሬ፡ መልካቸውን፡ ለውጠው፡ በሀ ሰተኞች፡ ፕሮፓጋንዳና፡ በሰለጠኑ፡ ሁሉ፡ገብ፡ አስመሳዮች፡ ተሳስታችሁ፡ የአረመኔውቹን፡ ሃላፊዎችና፡ አታላይ፡ አቋም፡

RIGHT

ለኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት፣
የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፣
የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ አንድነት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት፣
ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት።

በምንም፡ ሁኔታ፡ በስህተት፡ በመደገፍ፡ በኮሚኒስት፡ ኢምፔሪያሊስት፡ ወጥመድ፡ ተጠልፋችሁ፡ የኢትዮጵያን፡ ሕዝብ፡ ጠላትነት፡ እንዳታተርፉ፡ በመጠንቀቅ። ይልቁንስ፡ በሚቻላችሁ፡ መንገድ፡ ሁሉ፡ በዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ ዓላማና፡ ለኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡(ፌዴራል) የሕዝብ፡ ነፃ፡ አስተዳደር፡ እምነት፡ በአንድነት፡ጠንክሮ፡ የቆመውን፡ የሕዝባችን፡ እነሆ፡ የኅብረት፡ ኃይል፡ ዲሞክራሲያዊ፡ ንቅናቄ፡ እንድትረዱልን፡ ያህል። ሙሉ፡ የፖለቲካና፡ የሞራል፡ ትብብራችሁን፡ በከበሬታ፡ ስንጠይቅ፡ ተጨባጭ፡ የማቲሪያል፡ እርዳታችሁን፡ በመቀጠል፡ ከምንም፡ ግዜ፡ በይበልጥ፡ ዛሬ፡ ነገ፡ ሳትሉ፡ ታደርጉልን፡ ዘንድ፡ በኢትዮጵያ፡ ነፃነትና፡ በሕዝባችን፡ ዲሞክራሲያዊና፡ መሠረታዊ፡ መብት፡ ልዕልና፡ በአርበኞቻችን፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡ ሀቀኛና፡ ቁርጠኛ፡ ሕዝባዊ፡ ሠራዊት፡ የኅብረት፡ እንቅስቃሴ፡ ስም።

ለእውነተኛው፡ ለሃይማኖተኛው፡ ሰላሙን፡ ደህንነቱንና፡ ነፃነቱን፡ ለተጠማው፡ የሰብአዊ፡ ክብሩን፡ ለተነፈገው፡ በግፍ፡ በረሃብ፡ በጦርና፡ በግዴታ፡ በትር፡ ደጋግሞ፡ ለሚሰቃየው፡ ቆራጥና፡ ጀግና።

RIGHT

ለኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት፣
የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፣
የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ አንድነት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት፣
ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡፡

በታሪኩ፡ ከበሬታ፡ አቋምና፡ በባሕሉ፡ ጽኑ፡ እምነት፡ ለአንድነቱ፡ ዘወትር፡ ለሚሰዋው፡ ውለታውን፡ መቼም፡ ለማይረሳው፡ ወዳጁን፡ ዘወትር፡ ለሚያከብረው፡ ሰላማዊ፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ስም፡ እርዳታችሁን፡ በታላቅ፡ አክብሮት፡ እንጠይቃለን" በማለት፡ አጥብቀው፡ ሲያሳስቡ፤
ሐ) በተለይ፡ አደራቸውን፡ ለጀግናው፡ ሕዝባችን፡ ለገናናው፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኞች፡ አሻውንቱና፡ ወጣቱ፡ በሙሉ፤ ሲያስተጋቡ፤

"የሃገሬ፡ ጉበዝ!

ይኸንን፡ የተቀደሰ፡ የጥሪ፡ መልዕክት፡ አዋጅ፡ በማክበር፡ ለኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ መሠረታዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ ዲሞክራሲያዊ፡ ልዕልና፤

በአርበኞቻችን፡ የአንድነት፡ የጦር፡ኃይል፡ ቆራጥ፡ የኅብረት፡ ትግል፡ ሙሉ፡ ተሳትፎ፤ የሚያስገኘውን፡ የኢትዮጵያን፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥትህን፡ እስከ፡ አቆምክ፡ ድረስ፤

RIGHT

ለኢትዮጵያ፡ ኅብረተ፡ ብሔር፡ (ፌዴራል) ዲሞክራሲያዊ፡ የዘውድ፡ መንግሥት፡
የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ መሸጋገሪያ፤
የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ ብሔሮች፡ አንድነት፡ ጠቅላይ፡ ምክር፡ ቤት፤
ልዩ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡፡

ዲሞክራሲያዊ፡ የነፃነት፡ መብት፡ በአንድነት!

በሚል፡ መፈክር፡ ተባብረህ፡ ተነስ! ገናናዋ፡ ኢትዮጵያ፡ ሃገራችን፡ ብሔራዊ፡ ግዳጃችሁን፡ በአክብሮት፡ ትጠይቃለች"! በማለት፡ ታሪካዊ፡ መልዕክት፡ አዋጃቸውን፡ ለጠቅላላው፡ ጀግና፡የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡ወገናቸው፡ በሙሉ፡ አስተላልፈዋል፡፡

ኢትዮጵያችን፡ በነፃነትዋ፡ መብት፡ ዲሞክራሲያዊ፡ ልዕልና፡
በተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኞች፡ አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል፡
ሕዝባዊ፡ ሠራዊት፡ ኅብረት፡

በተቀደሰው፡ የልጆችዋ፡ የፍቅርና፡ የደም፡ መስዋዕትነት፡
ለዘለዓለም፡ በአንድነትዋ፡ ትኑር!

ዲሞክራሲያዊ፡የነፃነት፡ መብት፡ በአንድነት!

በአንድነት፡ ተባበር !

ግርማዊ፡ ቀዳማዊ፡ አምሃ፡ ሥላሴ፡
ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ዘኢትዮጵያ።
የተባበሩት፡ የኢትዮጵያ፡ አርበኞች፡
አንድነት፡ የጦር፡ ኃይል።
ጠቅላይ፡ አዛዥ፡፡

ወርቅነህ፡ ሚካኤል፡
ልዩ፡ እንደራሴ፡፡





ለዲሞክራሲያዊት፡ ኢትዮጵያችን፤

መልካም፡ "የኅብረት፡ ቀን" !

መጋቢት፡ ፲፱፡ ቀን፡፡

RIGHT

ለማንኛውም ግንኙነት መለስተኛ የአድራሻ ማስታወቂያ።
SHORT MAILING LIST

ግቢ።
"CHANCERY" - 82 PORTLAND PLACE,
SUITE 0,
LONDON W 1.
ENGLAND - U.K.

"መብት"።
"RIGHT" - P.O.BOX. 360,
CROYDON CR9-6JX,
ENGLAND - U.K.

"ታቀፍ"-
"TACEF"- 89 CEDAR RD.,
CROYDON CRO-6UJ.,
ENGLAND - U.K.

የምዕራብ እዝ አምዶች። WESTERN BRANCH COLUMNS.

P.O.BOX. 980,
215 WEST 104 ST.,
NEW YORK N.Y. 10025,
U.S.A.

P.O.BOX. 523,
OXON HILL,
MARYLAND 20745,
U.S.A.

1223, WILSHIRE BL.,
SUITE 188, SANTA MONICA,
CA. 90403 U.S.A.

91, COSBURN AVE.,
SUITE 804, TORONTO,
ONTARIO M4K-2G2.

"አንድነት"
በ"ጠቅላይ መምሪያ" በኩል።

"UNITY"
THROUGH "HIGH COMMAND".

ለኢትዮጵያ፡ ሕዝብ፤